

በአዲስ አበባ ፣ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »




መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ

- ከሃያ አራት አብያተ ክርስቲያናት በላይ ያሠሩና የሠሩ ምእመን
- በጠበል ፮ ጠጠር የወጣላቸው መነኵሴ የእግዚአብሔርን ሥራ አደነቁ
- ከረኸም ፎቅ የወደቀው ሰው በመድኃኔ ዓለም ቸርነት ዳነ

ቍጥር ፲፩፣ ፲፱፻፹፮ ዓ/ም
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ታሪክና ባሕል ፤የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርብ ስለሆነ ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» ተብሎ ተሠይሟል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ እየተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

ዋና አዘጋጅ ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም

ረዳት አዘጋጅ መ/ ኤፍሬም በየነ

ስልክ 11 26 63

የመልእክት ሣጥን ቍጥር 1283

አዲስ አበባ


| ተ.ቍ. | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ በበዓለ ትንሣኤ ያስተላለፉት ቃለ ምእዳን | ፫ |
| ፪ | (ርእሰ አንቀጽ) ሞትን ድል አድርጐ ተነሣ | ፬ |
| ፫ | ምሥጢረ ቍርባን | ፭ |
| ፬ | አባት ሆይ ይቅር በላቸው | ፮ |
| ፭ | ቅዱስ ፓትርያርኩ ባሌ ጉባን ጐበኙ | ፰ |
| ፮ | ሦስቱ መስቀሎች በጎልጎታ | ፲፩ |
| ፯ | የሕማማት ሳምንት | ፲፭ |
| ፰ | ሆሣዕና በአርያም | ፲፯ |
| ፱ | ከሃያ አራት አብያተ ክርስቲያናት በላይ ያሠሩና የሠሩ ምእመናን | ፲፰ |
| ፲ | የትግራይ ሀ·ስብከትና ልማቱ | ፳ |
| ፲፩ | « ገዳማዊ ሕይወት » | ፳፪ |
| ፲፪ | የሊቃውንት ዓምድ | ፳፮ |
| ፲፫ | « ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ » | ፳፰ |
| ፲፬ | ታማኝ አገልጋይ | » |
| ፲፭ | የሴቶች ዓምድ | ፳፱ |
| ፲፮ | ዕረፍቱ ለጊዮርጊስ ሰማዕት | ፴ |
| ፲፯ | ከረጅም ፎቅ ላይ የወደቀው በመድኃኔ ዓለም ቸርነት ዳነ | ፴፪ |
| ፲፰ | ወንጌላዊ ማርቆስ | ፴፫ |
| ፲፱ | በጦበል ፮ ጠጠር የወጣላቸው አባ አሥራተ ገብርኤል ተሰማ | ፴፬ |
| ፳ | «እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም » | [illegible] |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በበዓለ ትንሣኤ

# ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን

### በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፡ - አሜን

«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኩር ሆኖ ከሙታን ተነስቷል » (፩ ቆር ፲፭ ፡ ፳)

የተወደዳችሁ ምእመናን ወዳጆቼና የመንፈስ ልጆቼ!

ከሁሉ አስቀድመን እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን ።

የትንሣኤ በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ከታወቁት ታላላቅ በዓላት አንዱ ነው ። የሕይወትና የነጻነት ቀን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ መንፈሳዊ ሥርዓትና በምሥጋና ታከብረዋለች ። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታንም በክርስቶስ በኩል ሆኖአልና ። በዓለ ትንሣኤ በክርስቶስ ላመኑና ለተጠመቁ ሁሉ የደስታ ቀን ነው ።

ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ በመባል በሚታወሰውና ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን አስቀድሞ በነበረው የጨለማ ዘመን የሰውን ዘር ሁሉ ከዲያብሎስ ግዛት ለማላቀቅ ፡ ከሲኦል ምርኮኛነት ፡ ነፃ ለማውጣትና ከኃጢአት እሥራት ለማስፈታት ፡ በፍፃሜውም ወደዚች የሕይወትና የትንሣኤ ብርሃን ለመድረስ አበውነቢያት ደማቸውን አፍስሰዋል ። ብዙ እንስሳትና አዕዋፍም በየቦታው ተሠውተዋል ። ሁሉም ዓለምን አላዳኑም ። ዓለም የዳነ ፡ በእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው ። በዓለ ትንሣኤ የዓለም መጥፋትን ያመጣውን ዲያብሎስን ፡ በኃጢአትና በጥፋት ወደ ዓለም የገባውን ሞት በሞቱ ደምስሶ ለትንሣኤያችን በኩር ሆኖ የተነሣበት ፡ ሰው ሁሉ ከዲያብሎስ ቁራኝነት የተላቀቀበት ፡ ከማዕሠረ ኃጢአት የተፈታበት የእርቅ የሰላምና የነፃነት ዕለት ዋነኛ በዓል ስለሆነ ለክርስቲያኖች ሁሉ ታላቅ ፡ በዓል ነው ።

በውነት ክርስቶስ ተነስቷል ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በመለኮታዊ ኃይልና ሥልጣን ተነስቷል ። በመቃብር ታፍኖ አልቀረም ። ከሞት በላይ ቅጣት ስለሌለ ሰቃዮቹ ሞቶ በመቃብር ተወስኖ ይቀራል መስሎአቸው ነበር ። ግን ሞትን በሞቱ ደምስሶ በመነሳቱ ጠላቶቹ ተበተኑ ፡ የሚጠሉትም ሁሉ ከፊቱ ሸሹ የትንሣኤውን ብርሃን ማየት አልተቻላቸውምና ።

ዓለም ብዙ ጊዜ ከስሕተቱ አይማርም ። የትንሣኤን ኃይል ለማፈን፡ የእግዚአብሔርን ስም ቀብሮ ለማስቀረትና በማን አለብኝነት ብቻውን ለመኖር ይፈልጋል ። በዚህም በዓለም ላይ ብዙ ሙከራና ትግል ተደርጓል ። ሰውና እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ታግለዋል ። እግዚአብሔር ግን በአሸናፊነቱ ይኖራል ። ከእግዚአብሔር ጋር የተጣሉና የታገሉ (የእግዚአብሔርን ኃይል የተዳፈሩ ሁሉ) ወድቀዋል ተሸንፈዋል ተበትነዋል ። ጠፍተዋል ። በዚህ ፈንታ ግን የሰው ልጅ ሕይወቱን ከሱ በላይ ለሆነውና መልካሙን ነገር ለሚያስብለት አምላክ ቢሰጥ ፈቃዱንም ለሱ ቢያስገዛ ፡ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለሱ ነጻነት የተፈጸመ መሆኑን ይረዳል ። የትንሣኤውንም ብርሃን ለማየት ይችላል የትንሣኤ ብርሃን ሕይወትነቱና ክብሩ በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ ነው ። ለማያምኑ ግን የብርሃኑ ጸዳል የሚያስፈራና የሚያብረከርክ ፡ እንደመቃብሩ ጠባቂዎችም የሞት እንቅልፍ የሚያመጣ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን የትንሣኤ ድል ላልሰሙ ሁሉ እያሰማች ፡ ላላወቁ እያሳወቀች ሐዋርያዊ አገልግሎቷን ስትፈጽም ትኖራለች ። ክርስቶስ ለሰውልጆች ሕይወትን የሚሰጥ ፡ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስን የሚያድል ሰማያዊ ንጉሥ እንጂ በሞት ሥልጣን ታስሮ መቃብር ተቆልፎበት የሚኖር ደካማ አምላክ አለመሆኑን በዐደባባይ ስትሰብክ ትኖራለች ።

የክርስቶስን ትንሣኤ በየዓመቱ የምናከብረው ያለፈውን ድርጊት በታሪካዊ ይዘቱ በማስታወስ ብቻ አይደለም ። ከሙታን ተለይቶየተነሣው ክርስቶስ ትናንት የነበረ ፡ ዛሬ ያለና ነገም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነግሦ የሚኖር ሕያው ባሕርይ አምላክ መሆኑን በማመን የትንሣኤውን ብርሃን ለመቀበል ተዘጋጅተን ነው ።

የትንሣኤን በዓል በምናከብርበት ብዙ ዝግጅት እናደርጋለን ። በጾም በጸሎትና በኃዘን የሰነበተውን ሰውነታችንንም ደስ ልናሰኘው እንወዳለን ። ነገሩ መልካምና የሚገባም ነው ። ነገር ግን አብረን ልናስበው የሚያስፈልግ ታላቅ በጎ ሥራ አለ ፤ ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሣኤው ዋዜማ ነፍሶቻቸው ታስረው ወደነበሩ ሰዎች እንደሄደና ነጻነትን እንደሰበከላቸው በማስተዋል ፡ እኛም የትንሣኤን በዓል በደስታ ስናከብር ከሲኦል ባልተሻለ ኑሮ የሚኖሩትን በኃጢአት ዓለም የታሠሩትን ፡ የማጣት ቀንበር የተጫናቸውን በተፈጥሮ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የሆኑትን ሁሉ በኀይነ ምሕረት ልንመለከታቸውና ልናስባቸው ይገባል ። ካለን በማካፈል ፋሲካውን ከነሱ ጋር ብናሳልፍ ክርስቶስ ማዕዳችንን ይባርካል ሕይወታችንን በትንሣኤው በረከት ያጠግባል ፤ ልቦናችንን በደስታ ይሞላል ። «ነዳያን ሁል ጊዜ ከናንተ ጋር ናቸው» ተብሎአልና ። ከዚህም ሁሉ ጋር ጌታችን በመስቀል ላይ በደላችንን ሁሉ ይቅር እንዳለን ፡ እርቅን ሰላምን እንዲሰጠን እኛም ከሱ በመማርና አርአያውን በመከተል ዘወትር ለእርቅና ለይቅርታ መዘጋጀት አለብን ። ይቅርታን ማግኘት የሚቻለው የተበደሉትን በመተው ለሌላው ይቅርታ ማድረግ ሲቻል ነውና ።

**የተወደዳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ በዓሉ የሰላም በዓል እንዲሆን የአምላካችን ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን አሜን ።**



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ

የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅ ነቢያትና ሐዋርያት በሞት ጥላ ሥር ተይዘው የነበሩትን ሰዎች ከሞት እንዳሥነሷቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ ይገኛል ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከነዚያ ሁሉ ፈጽሞ የተለየ ነው ። ምክንያቱም በነቢያትና ሐዋርያት ጸሎትና አማላጅነት የተነሡ በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ በራሳቸው ሥልጣንና መብት አይደለም መድኃኒታችን ክርስቶስ ግን ማንም ሳይጸልይለት የማንም ኃይልና ርዳታ ሳይታከልበት በለበሰው ሥጋ ፍጹም ሰው ሲሆን በእውነተኛ ተዋሕዶ ፍጹም አምላክ በመሆኑ ለሰው ልጆች መብትና ነፃነት ሲል በራሱ ፈቃድ ሞቶ ሦስት ቀን መቃብር ውስጥ ከቆየ በኋላ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ መግነዝ ፍቱልኝ ድንጋይ ፈንቅሉልኝ ሳይል በራሱ ሥልጣን በታላቅ ክብርና ሞገስ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ፍጹም አምላክነቱን አስመስክሯል ።

መድኅን ክርስቶስ ከመወለዱ ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት የነበረው ነቢዩ ዳዊት "ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም" እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ሰው ከሞት ተነሣ ሲል ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ ሞቶ በራሱ ሥልጣንና ኃይል እንደሚነሣ ተነግራል ልበ አምላክ ተብሎ የሚነገርለት ዳዊት ስለክርስቶስ ትንሣኤ የተነበየው ይህን ብቻ አልነበረም "ይእዜ እትነሣ ይቤ እግዚአብሔር" እግዚአብሔር ዛሬ እነሣለሁ አለ ሲል ተንብዮዋል ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ተወልዶ በዚህ ዓለም በሚያስተምርበት ወቅት እንደሚሞትና እንደሚነሣ ለደቀ መዛሙርቱ አስረድቶአል ማቴ ፲፮ ፥ ፳፩ ትንቢቱ ሲደርስ ክርስቶስ ምንም በደል ሳይኖርበት በአይሁድ አለቆችና ጭፍሮች ተይዞ በሽፍቶች መካከል ተሰቅሎ እንዲ፣ ተ ተደረገ ከብዙ መከራ በኋላ "ሁሉም ተፈጸመ" በሚል የመጨረሻ ቃል ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለይቶ ራሱን ለሞት ሰጠ ፣ የእኛን ደካማ ሥጋ ቢዋሐድም የኃያላን ኃያል የሆነ ፍጹም አምላክ ነውና በሦስተኛው ቀን በመንፈቀ ሌሊት ሞትን ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን ተነሥቶአል ።

የክርስቶስ መነሣት በትንቢት መነገሩ ብቻ ሳይሆን በሐዲስ ኪዳን በብዙ ቦታዎች ተረጋግጦአል። "እሑድ ጧት ማለዳ መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያም መቃብሩን ለማየት ሲሔዱ መልአኩ ከሰማይ ወርዶ መነሣቱን እንደነገራቸውና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲያበሥሩ ሲገሠግሡ ኢየሱስ በመንገድ አግኝቶ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ሲላቸው እነርሱ ቀርበው እግሮቹን ይዘው ሲሰግዱ ወደገሊላ ሒደው ለደቀ መዛሙርቱ እንዲነግሩ ታዝዘዋል ማቴ ፳፰ ፥ ፩ ፥ ፲ ።

ደቀ መዛሙርቱ ከትንሣኤው በኋላ በዝግ ቤት እንዳሉ በተከታታይ ሁለት ጊዜ እንደገናም በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ በግልጥ ታይቶና በቃሉ አነጋግሮ መነሣቱን በፍጹም እንዲያምኑ አድርጓል ዮሐ ፥ ፳ ፥ ፳፩ ።

ማርያም መግደላዊት ተስፋሳት ቆርጥ በመቃብሩ አጠገብ ቆማ ስታለቅስ የኢየሱስ ሥጋ አርፎበት በነበረው መቃብር አንዱ በራስጌ ሌላው በግርጌ የነበሩት መላእክት አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ ባሏት ጊዜ ጌታችን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም ስትላቸው ኢየሱስ ተገልጦ "ማርያም" ብሎ ጠርቶ እንዳነጋገራት ተጽፎአል ማር ፲፮ ፥ ፱-፲፱ ።

ቅዱሳት አንስት ሽቶ ይዘው ወደመቃብሩ በመጡ ጊዜ ልብሳቸው የሚያንፀባርቅ ሁለት ሰዎች ሕያው የሆነው ኢየሱስን በ ሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ ? እርሱ በዚህ የለም ተነሥቶአል በገሊላ በነበረበት ጊዜ የነገራችሁን አስታውሱ የሰው ልጅ ለኃጢአተኞች ተላልፎ መስጠት መሰቀልና በሦስተኛውም ቀን ከሞት መነሣት ይገባዋል ብሎአቸው ስነበር ሴቶችም የኢየሱስን ቃል አስታወሱ ፣ ከመቃብርም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለቀሩትም ነገሩአቸው ሉቃ ፳፬ ፥ ፩ ፥ ፲ ።

ሐዋርያ ቅ/ጳውሎስ በ፩ኛ ቆሮ ም ፲፭ ፥ ፫ - ፲፰ እንደተናገረውና "በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ሞቶ ተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ ለጴጥሮስ ታየ ኋላም ለአሥራ ሁለቱ ታየ ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ተከታዮቹም በአንድ ጊዜ ታያቸው ከእነርሱም አብዛኞዎቹ በሕይወት አሉ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ታየ ለሐዋርያትም በሙሉ ታያቸው ብሏል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ ለአሥራ አንድ ጊዜ ያህል ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች ከትንሣኤው ዕርገቱ ባሉት ቀናት በግልጽ ታይቷል ። ይህ ሁሉ ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል በአይሁድ ዘንድ መከራን ተቀብሎ እስከ ሞት ተላልፎ ተሰጥቶአልና ሞትንም ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን መነሣቱን አማናዊ የሆነን ሁሉ እናውቃለን ።

ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ "ትንሣኤከ ለእለ አመነ ብርሃነከፈነ ዲቤነ" ብሎ እንዳመሰገነ እኛም ትንሣኤህን ለምናምን ሁሉ ብርሃንህን ላክልን እያልን በራሱ ሥልጣን የተነሣውን ክርስቶስ ሁል ጊዜ ልናመሰግነው ይገባል ።

# ምሥጢረ ቁርባን

ምሥጢር ማለት ለሚወዱት ለሚያምኑትና ለሚያቀርቡት የሚገለጽ የረቀቀና የከበረ ተግባር ነው ፣ ቤተ ክርስቲያናችን ወስናና ደንግጋ የምታስተምራቸው ምሥጢራት ሰባት ሲሆኑ እነርሱም ምሥጢረ ጥምቀት ፣ ምሥጢረ ሜሮን ፣ ምሥጢረ ቁርባን ፣ ምሥጢረ ቀንዲል ፣ ምሥጢረ ንስሐ ፣ ምሥጢረ ክህነትና ምሥጢረ ተክሊል ናቸው ።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት ምሥጢራት የሚደገሙና የማይደገሙ አሉ ፣ የማይደገሙት ጥምቀት ሜሮን ተክሊልና ክህነት ናቸው ፣ ቁርባን ቀንዲልና ንስሐ ግን ይደገማሉ በዚህ ጽሑፍ ስለ ምሥጢራቱ በጠቅላላ ለመግለጽ ስለማይቻል በአጭሩ ለመግለጽ የምንፈልገው ስለምሥጢረ ቁርባን ነው ።

አዳምና ሔዋን የታዘዙትን ትእዛዝ አፍርሰው ከምድረ ገነት ወጥተው በተባረሩ ጊዜ በሠሩት ኃጢአት ተጸጽተው ቢያለቅሱ እግዚአብሔር አምላክ ልቅሷቸውንና ኃዘናቸውን ሰምቶ ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከድንግል ማርያም ተወልጄ ተሰቅየ ሙቼ ሥጋዬን ቆርሼ ደሜን አፍስሼ አድናችኋለሁ ሲል ተስፋ ሰጣቸው ።

ይህ የተሰጣቸው ተስፋ የሚፈጸምበት ጊዜ በፈጣሪ ዘንድ አምስት ቀን ተኩል ተብሎ ቢነገርም በሰው ዘንድ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ስለሆነ እጅግ በጣም ብዙ ዘመን ነበር ቃሉ የማይታበል የተናገረውን የማይረሳ አምላክ በተናገረው ቃል መሠረት ከዘመኑ ፣ ከወሩ ፣ ከዕለቱ አንዲት ቀን እንኳን ሳያጓድልና ሳይቀንስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ያለ ዘር ፣ ያለ ሩካቤ ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና ተወለደ ፣ አምላክ ነኝና ዕለቱን ልደግ ሳይል ቀስ በቀስ ጥቂት በጥቂት ካደገ በኋላ በ፴ ዘመኑ ተጠምቆ ሳይውልና ሳያድር ዕለቱን ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄደ ፣ በዚያም ከቆመ ሳይቀመጥ ከዘረጋ ሳያጥፍ ፀርባውን ቀን እንደ አንድ ቀን አድርጎ ከፆመና ከጸለየ በኋላ ዲያብሎስ በሦስት መንገዶች ሊፈትነው ቀረበ አንደኛ በስስት ፣ ሁለተኛ በትዕቢት ፤ ሦስተኛ በፍቅረ ንዋይ ነው ፣ በሦስቱም አቅጣጫ የመጣውን ዲያብሎስ ድል አድርጎ ከገዳም ተመለሰ ።

ከገዳመ ቆሮንቶስም እንደተመለሰ በስብከተ ወንጌል ለማገልገል የሚፋጠኑትን ፲፪ቱን ሐዋርያት ፸፪ቱን ቅዱሳት አንስት ፭፻ቱን አርድዕት መርጦ ወንጌልን ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተማራቸው ፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ለሰው ልጅ ሁሉ በጠቅላላ ድኅነትን የሚያቀዳጅበት ጊዜ ሲደርስ ዓርብ ሊሰቀል በዋዜማው ሐሙስ ማታ የመሰነባበቻ ራት ለማድረግ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ ፣ ለራት ካመጡ ለት ዳቦ መካከል ያላረረውንና ያልጠቆረውን ዳቦ መርጦ እንሥና ባርኮ አክብሮ ለውጦ ይህ ነገ በመልዕልተ መስቀል ላይ የሚሠዋው ሥጋዬ ነውና እንኩ ብሉ ይህንን ስትበሉ ሕማሜን መከራዬን ሞቴን እያሰባችሁ ተመገቡት አላቸው ወይኑንም ባርኮ አክብሮ ለውጦ ይህ በመስቀል ላይ ለኀጢአት ማስተሥረያ የሚፈሰው ደሜ ነውና እንኩ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ምሥጢረ ቁርባንን የሰጣቸው ከበሉና ከጠጡ በኋላ ሲሆን የበሉትንና የጠጡትን በተአምራት እንዳልበሉ እንዳልጠጡ በማድረግ ነው ። በዚያም መሥዋዕተ ኦሪትን ሽሮ አዲስ መሥዋዕተ ወንጌልን እንደሾመ ያስረዳል ።

በምሥጢረ ቁርባን የሚፈጸሙ ሁለት ነገሮች አሉ እነርሱም የማይታይ ጸጋና የሚታይ አገልግሎት ናቸው ፣ የሚታይ አገልግሎት ካህኑ ኅብስቱን በጸሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ ሲባርከውና ሲፈትተው ይታያል ፣ የማይታይ ጸጋ ደግሞ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ሲሆን ከበቃ ሰው በስተቀር ሳልበቃ ሰው አይታይም በቀኖና ቤተክርስቲያናችን አንድ ሰው ለመቁረብ ከምግብ መከልከል የሚገባው ፲፰ ሰዓት ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ሥጋውንና ደሙን ባርኮ ለውጦ አክብሮ ለሐዋርያት የሰጠበት አዳራሽ የስምዖን ቤት ነው የአልዓዛር ቤት ነው የኒቆዲሞስ ቤት ነው የሚል የተለያየ አስተሳሰብ አለ ይህንን ለመረዳት የሚቀጥለውን እንመልከት ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ተቀመጠ ይላል ነገር ግን የአልዓዛር ቤት መሆኑን የሚያመለክት ማርቆስ ፲፬ ፲፱-፲፯ ሉቃስ ፳፱ ፯-፲፬ የተጻፈውን ቃል መመልከት ነው ኤጲፋንዮስ የተባለው ሊቅ «ወረፈቀ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ቤተ አልዓዛር አርኩ» ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወዳጁ በአልዓዛር ቤት ተቀመጠ ይላል ጌታ በወዳጁ አልዓዛር ቤት በማዕድ ተቀምጦ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ሐዲስ ኪዳን የሚሠዋው ሥጋውን በኅብስት ስለኃጢአት ስርየት የሚፈስሰውን ደሙን በወይን መስሎ ገልጾላቸዋል አንዳንድ መጻሕፍት ማዕዱ የተዘጋጀው በአልዓዛር ቤት እንደሆነ ይናገራሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን የጸሎተ ሐሙስን ምሥጢር የፈጸመው ከሦስቱ አደራሾች በየትኛው ይሆን? እያሉ ስለሚያስቡ የሚከተለውን ማስረጃ በአጭሩ እንመልከት ሄድናክዮስ የሚባል አንድ ሰው በቢታንያ ነበር ለእርሱም ሦስት ወንዶች ሁለት ሴቶች ል፡ች ነበሩት ወንዶቹ አልዓዛር ስምዖን ኒቆዲሞስ ሲሆኑ ሴቶቹ ማርያምና ማርታ ይባላሉ ፣



www.ethiopianorthodox.org



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የራት ግብዣ ሲያደርግላቸው

ሄድኖክዮስም በቢታንያ በክፍል የተለያዩ ደርብና ምድር ቤት ያለው ታላቅ ሕንጻ መኖሪያ ቤት ነበረው ፤ ከዚህም ሌላ በዓለ ፋሲካን ፤ በዓለ ሰዊትን ፤ በሚያከብርበት ጊዜ የቤት ችግር እንዳይገጥመው በኢየሩሳሌም ዙሪያ የከተማ ቦታ ተመርቶ መጠነኛ ቤት ሠርቶ ይኖር ነበር ይኸው ሄድኖክዮስ በሚ ሞትበት ጊዜ በቢታንያ ያለውን ቤቱን ለአልዓዛር ፤ ለስምኦንና ለኒቆዲሞስ ፤ በኢየሩሳሌም የነበረውን ቤቱን ደግሞ ለማርያምና ለማርታ ሰጥቷቸው ሞተ ይባላል ።

ከዚህ በኋላ የዓለም መድኃኒት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ከቤታቸው ገብቶ ባዘጋጁ ሉት ማዕድ ላይ በመገኘት ከላይ እንደተገለጸው ራት ከበሉ በኋላ ካመጡለት ፤ ኅብስት አንዱን አንሥቶ ፤ ጽዋውንም ባርኮ ለውጦ ነገ ለቤዛ ብዙኃን ሆኖ በመልዕልተ መስቀል የሚሰዋው ሥጋዩ የሚፈሰው ደሜ ይህ ነውና ተቀበሉ ብሎ ለሐዋርያት ሲሰጣቸው ለሦስቱም ወንድማማቾች እግዚአብሔር የሰጠው ጸጋ ለማንም አልተሰጠም ።

ስለዚህ ቤተ አልዓዛር ቤተ ስምኦን ፤ ጽርሐ ኒቆዲሞስ ተብሎ በሦስት ተከፍሎ ይነገር እንጂ ቤቱ አንድነታቸውን አጽንተው ሳይለያዩ በፍቅርና በሃይማኖት ተመሥርተው የኖሩት ሦስት ወንድማማቾች አባታቸው ሄድኖክዮስ የሰጣቸው ያው አንድ ቤት ሲሆን በልዩ ልዩ ስም መጠራቱ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቧል ፤ ታሪኩን ለማወቅ ለሚፈልጉ ዘለግ አድርገን ገለጽነው እንጂ ታላቁ ቁም ነገር ከኃጢአት በንስሐ ነጽቶ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል በቀራንዮ አደባባይ የሠዋውን ሥጋውን ፤ ያፈሰሰውን ደሙን መቀበል ነው ።

ስለዚህ በአፍ ክርስቲያን ነኝ ማለቱ ብቻ አይጠቅምምና ክርስቶስ ያዘዘውን ትእዛዝ ሁሉ መፈጸም ያስፈልጋል ፤ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሕግና ትእዛዝ ከመፈጸም ጋር በሕግ ተወስኖ ከኃጢአትና ከበደል በንስሐ ነጽቶ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል ይገባል ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ የክርስቶስን ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ዘለዓለማዊ ሕይወት የላችሁም ተብሎ ተጽፏልና ።

ቀ-ሲ-ገ- ልሳኑ በዛብጎ

# "አባት ሆይ ይቅር በላቸው"

እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አርአያና ምሳሌ አድርጎ መፍጠሩ ፤ እግዚአብሔር ሰውን ከፍጡራን ሁሉ አብልጦ እንደ ወደደው ያመለክታል ። እግዚአብሔር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው መፍጠሩ ብቻ አልበቃውም ። እግዚአብሔር በአርአያውና በመልኩ አድርጎ የፈጠረውን ሰው የምድርና በምድር ላይ ላሉት ፍጡራን ሁሉ ጌታ አድርጎ ሾመው ፤ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን ፍጥረታት በሙሉ አርአያ እግዚአብሔር ለሆነው ለሰው ተገዥዎችና ግዛቶች እንዲሆኑ አደረጋቸው ። (ዘፍጥረት ፩ ፤ ፳፮-፴፩ ፤ መዝሙር ፰ ፤ ፩-፱) ። ነገር ግን ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር በመጠበቅ እስከ መጨረሻው ጸንቶ አልተገኘም ። በአንፃሩ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ ጥሶ ትእዛዙን አፍርሶ ተገኘ ። ይህ ብቻ አይደለም ሰው በትንኮል እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ሲጥር ተገኘ (ዘፍጥረት ፫ ፤ ፩-፯) ።

በዚሁ ምክንያት እግዚአብሔር ሰውን ካስቀመጠው ከገነት አስወጣው ፤ ገነትንም ሠይፈ ነበልባል በያዘው በመልአኩ በኪሩቤል አስጠበቃት ። እነሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው ወደ ባመጣው ቅጣት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣላ ፤ ማለት እግዚአብሔር ሰውን ጠላው ፤ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሱ ወደ በሠራው ኃጢአት በመርከሱ ፤ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ ። በዚሁ ምክንያት በመጀመሪያው ሰው ኃጢአት ምክንያት የሰው ዘር ሁሉ በኃጢአት ስር ወደቀ ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚሁ ሲያስተምር "ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ ፤ በኃጢአትም ምክንያት ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ" ብሎአል (ሮሜ ፤ ፭ ፤ ፲፪) ።

ስለሆነ ግን እግዚአብሔር ምሕረቱ የበዛ ፤ መዓቱ የራቀ አምላክ ስለሆነ ፤ የሰውን ልጅ ሊታረቀው ፈቀደ ፤ ዓለምንም ከኃጢአት ለማዳን ወደደ ስለዚህም የሚወደውን ልጁን ወደ ዓለም ሰደደ ። የእግዚአብሔር ፍቅር የሚታወጅበት የድኅንነት ዘመን በደረሰ ጊዜ ቃለ እግዚአብሔር ወልድከድ ንግል ማርያም ተወለደ ። የእግዚአብሔር ጠላቶች የነበሩ ሰዎች የእግዚአብሔር የፀጋ ልጆች ይሆኑ ዘንድ የአምላክ ልጅ የሰው ልጅ ሆነ (ገላትያ ፤ ፬ ፤ ፬)

ስለዚሁ ታላቅ ምሥጢር ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለምእመናን ሲጽፍ "ጠላቶቹ ሳለን እግዚአብሔር በልጁ ሞት ይቅር አለን ከእርሱም ጋር ታረቅን ፤ ከታረቅንም በኋላም በእርሱ (በልጁ) ሕይወት እንድናለን ፤ ይህም ብቻ አይደለም ፤ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ በኩል በእግዚአብሔር እንመካለን" ብሎአል (ሮሜ ፭ ፤ ፲-፲፩) ።

ይህ እውነተኛው ዕርቅ የተገኘው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ባደረገው ይቅርታ መሆኑ ግልጽ ነው ። ዕርቁ ከሁለቱም ወገን ማለት ከእግዚአብሔርና ከሰው የተገኘ አልነበረም ። እግዚአብሔር ይቅር ባይ ስለሆነ ሰውን ሊታረቀው ፈቀደ ። ስለዚህም ይቅር አለው ። በዚሁ ምክንያት ዕርቅ የተገኘው ከእግዚአብሔር ነው ። ዕርቅ የተገኘው ማለት ለሰው ልጅ የመጣለት ከእግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ ፤ ይቅርታም የተገኘው ከራሱ ከእግዚአብሔር ነው ። ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሱ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር ግን ይቅርታው የበዛ አምላክ ነውና በጠላትነት ጎራ የቆመውን ሰው ይቅር አለው ፤ ታረቀው፤ ማረውም ። ስለዚህ ዕርቅም ፤ ይቅርታም የተገኙት ከእግዚአብሔር ነው ።

የወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢር የተመሠረተው በዕርቅና በይቅርታ ነው ። ራሱ ክርስቶስ የመጣው ይቅርታንና ዕርቅን ለመመሥረት ነው ። የይቅርታና የዕርቅ ባለቤት የሆነው ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በየቦታው እየተዘዋወረ "ይቅር በሉ" እያለ ያስተምር ነበር ። "ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማይ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋል ፤ ነገር ግን እናንተ ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ሰማያዊው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም" እያለ ያስተምር ነበር ። (ማቴዎስ ፮ ፤ ፲፭) ።

የይቅርታና የዕርቅ ባለቤት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕግ አፍራሽ የሆነውን ሰው በበጎ ፈቃዱ ሊታረቀውና ይቅር ሊለው መምጣቱን ለዓለም ሲገልጽ እንዲህ እያለ ያስተምር ነበር ፤ "ወለክሙስ እብሰክሙ እለ ትሰምዑኒ አፍቅሩ ጸላእተክሙ ወግበሩ ሠናየ እለ ይፃረሩክሙ ። ወደኃርዎሙ ለእለ ይረግሙክሙ ፤ ወጸልዩ ዲበ እለ ይትኤገሉክሙ" እያለ ያስተምር ነበር ። ይህም ማለት "ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ፤ ስለሚበድሉአችሁ ጸልዩ" ሲል ጌታችን አስተምሮአል። (ሉቃ ፤ ፮ ፤ ፳፯)

አሁን እንዳነበብነው ፤ « ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፤ ስለሚበድሉአችሁ ጸልዩ ሲል ያስተማ



ማኅበረ ሰላሙ በመስቀሉ ፡ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ

ረው ጌታ ያስተማረውን ሁሉ በሥራ ሲገልጸው ማየት እጅግ ድንቅ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከኃጢአትና ከዳግም ሞት ለማዳን ሲል ራሱን ለመከራና ለመስቀል አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ፤ የጨለማ ሠራዊት የተባሉት አይሁድና ሮማውያን በአንድ ላይ ሆነው ጌታችንን ይዘው አሰሩት (ዮሐ ፤ ፲፰ ፤ ፲፪) ፤ በአደባባይ ገረፉት (ዮሐ ፤ ፲፱፡፩ "የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን» እያሉ ዘበቱበት ፤ ተፉበትም ፤ በመቃም ራሱን መቱት (ማቴ ፳፯ ፤ ፴ ) ፤ ለመዘባበት ቀይ ልብስ አለበሱት የእሾህ አክሊልም ጉንጉነው ደፉበት (ማር ፤ ፲፭፡ ፲፰) ፤ በፊቱም ተፉበት ጎሰሙትም ፤ በጥፊም መትተው ፤ ፊቱንም ሸፍነው እየቦረቦሙ "ክርስቶስ ሆይ ራስህን የመታህ ማነው ? ትንቢት ተናገርልን" እያሉ ዘበቱበት (ማቴ ፤ ፳፮ ፤ ፷፯ ፤ ማር ፲፬ ፤ ፷፭) ። እንደገናም መስቀሉን አሸክመው በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወሰዱት ፤ በዚያም ሰቀሉት ። የወንደበዴዎች አለቃ ነው ለማለት በግራውና በቀኙ ሁለት ወንበዴዎችን ሰቀሉ (ዮሐንስ ፲፱ ፤ ፲፯) ። ከዚያም በሐሞት የተደባለቀውን ሆምጣጣ (ወይን ጠጅ) እንዲጠጣ አቀረቡለት ፤ እሱም ቀምሶ ሊጠጣው አልወደደም (ቀምሶ ተወው) ማቴ ፤ ፳፯ ፤ ፴፬-፵፰

በዚህ ጊዜ ይህን ሁሉ መከራ ተቀብሎ በመስቀል ተሰቅሎ እያለ ላሰሩት ፤ ለገረፉት ፤ ለደበደቡት ፤ ለዘበቱበት ፤ለቸነከሩትና ለሰቀሉት በሙሉ፤ "አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ" "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው " ብሎ ጸለየላቸው እንደ ሰውነቱ ማለት ከኃጢአት በቀር ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ ጸለየላቸው ፤ ፍጹም አምላክ እንደ መሆኑ ደግሞ በደላቸውን ይቅር አላቸው (ሉቃስ ፳፫ ፤ ፴፬) ።

"አባት ሆይ ይቅር በላቸው" ብሎ ስለአሰሩትና ስለሙቱት ጸለየላቸው ፤ በፊቱ ላይ ለተፉበት ፤ ፊቱን እየሸፈኑ ለመቱት ፤ የእሾህ አክሊል ጎንጉ

ተከታዩን በ[illegible] ገጽ ይመልከቱ




www.ethiopianorthodox.org

## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

# ባሌ ጎባን ጎበኙ ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከየካቲት ፲ እስከ የካቲት ፲፪/፲፱፻፹፯ ዓ/ም አርሲ አሳሳ ገደብን ፣ ዶዶላን፣ ጎባንና ሮቢን ጎብኝተዋል ።

ቅዱስነታቸው የካቲት ፲/፲፱፻፹፯ ዓ/ም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና የክብር እንግዶችን በማስከተል ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ተኩል ከአዲስ አበባ ሲነሡ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ባለሥልጣናት አቃቂ ድረ ስ በመገኘት የክብር አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎ ስ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር እንግዶቻቸው ጋር ተጉዘው ለ፩ ሰዓት ሩብ ጉዳይ አርሲ አሳሳ ገደብ ወረዳ ከመድረሳቸው በፊት ከከተማው ፩ ኪ- ሜትር ያህል ወጣ ብለው የአሣሣ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል አስተዳዳሪ የደብሩ ሰበካ ጉባኤ አባላትና ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎች ምእመናን የደብሩ ካህናትና ሊቃውንት በማሰለፍ የሰንበት ት ቤት መዘምራን ወጣቶች «ቅዱስ አባታችን ፣ እንኳን ደህና መጡልን የሚለውን በማዘመር ቀቀብለዋቸዋል ። ከዚያም ከቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ የቤ ክርስቲያኑ ደወል አስተጋብቶ በቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረት ተሰብስቦ የቅዱስነታቸውን መምጣት ሲጠባበቅ የነበረው በብዙ ሺህ የሚቈጠር የከተማው ሕዝብ በቅዱስነታቸው መምጣት የተሰማውን ደስታ በሆ ታና በእልልታ ገልጾአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው አጭር የሕሊና ጸሉት ካደረሱ በኋላ በኅብረት ጸሉ ተ ኪዳን አድርሰዋል ። ይህ በዚህ እንዳበቃም ቅዱስነታቸው ወደዐውደ ምሕረቱ ወጥተው በተዘጋጀላቸው የክብር መንበር እንደተገኙ ሊቃውንቱ ለቅዱስነታቸው አቀባበል ያዘጋጁትን ግሥ ቃኝተው ለ፲፭ ደቂቃ ያህል አሸብሸበዋል ። የሰንበት ት ቤት መዘምራን ወጣቶችም ተመሳሳይ መዝሙር ዘምረዋል ።


አያይዘውም ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ንግግር አድርገዋል ። ብፁዕነታቸው ካደረጉት ንግግር «ቅዱስነትዎ ለምእመናን ልጆችዎ ያለዎት ፍቅር የቱን ያህል እንደሆነ በመላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ልብ በጥልቀትና በምልአት የታወቀ ነው ። ዛሬም ቅዱስነትዎ ባደረጉት ረዥም ጉዞ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ በዚህ ሃይማኖቱንና የሃይማኖት አባቱን ወዳድበሆነ ሕዝብ መካከል ተገኝተው የተቀደሰ ቡራኬዎ በመስጠትዎ ሕዝቡ የተሰማው ደስታ ከመጠን በላይ ነው ። ምእመኑ መንጋዎ በቅዱስነትዎ ላይ ያለው ፍቅር ከከተማው ወጥቶ በመዝሙር ፣ በሆታና በእልልታ ሲገልጽ ከብፁዓን አባቶች ጋር ያየሁት ስለሆነ ብዙ መናገር የሚያስፈልግ አይመስለኝም ። አሁን ቅዱስነትዎ ሌላ የሚጠብቅዎት ምእመናን ስላሉ እነዚያም እንዳይጉላሉ ለዚህ ምእመን መንጋዎ የተቀደሰ ቡራኬዎ ይሰጡልኝ ዘንድ አሳስባለሁ» የሚል ይገኝበታል ።

ከዚህ በኋላም ቅዱስነታቸው «ቤተ ክርስቲያናችን የብዙና የረጅም ዘመን ዕድሜ ያላት ናት ። ባሳለፈቻቸው ብዙ ዘመናትም የማይሰፈርና የማይቆጠር ፣ የማይለካና የማይመዘን ሠፊ ታሪክ ፣ ዕፁብ ድንቅና ብርቅ ንብረት ፣ ሀብት ቅርስ ክቡርና ውድ ንዋየ ቅድሳት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት ። እናንተም ከዚህች ታሪካዊትና ስመ ገናን ቤተ ክርስቲያን የተገኛችሁ ስለሆነ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል አባቶቻችሁ ይመጣሉ ብለው ስለነገሩአችሁ የእናታችሁ ፍቅር አስገድዶአችሁ ከጠዋት ጀምሮ በወርጭ በጸሐይ ስትንቃቁ በመዋላችሁ ምን ያህል የአባቶች ፍቅር እንዳደረባችሁ ለመረዳት አስችሎ ናል።

እንዲህ ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያንና የአባቶች ፍቅር ያለው ሕዝብ ራሱን የቻለ ጉብኝት የሚደረግለት እንጂ በአግረ መንገድ ታይቶ የሚታለፍ ሕዝብ አለመሆኑን ተገንዝቤአለሁ ፤ አሁንም እኔ መጥቼ በውሎና በአዳር ጉብኝት ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ ፤



ቅዱስነታቸው ለሕዝበ ክርስቲያኑ ቡራኬያቸውን ሲያስተላልፉ



ቅዱስነታቸውን በቤተ ክርስቲያኑ ዓውደ ምሕረት ተገኝተው ሲቀበሏቸው

በፈቀዳችሁት ቀን በአባታችሁ በአቡነ ናትናኤል አማካይነት ይድረሰኝ እፈጽማለሁ አሁን ግን ወደሚቀጥለው ጉብኝታችን ለመኼድ ፣ ግዴታ ነውና ፈቃዳችሁ ይሁን ካሉ በኋላ ሕዝቡን ባርከዋል በዚሁ ጊዜ ሕዝቡ ለቅዱስነታቸው ክብር ታላቅ ግብዣ አድርጎአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎ ስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከአሣሣ ተነሥተው ወደ ዶዶላ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጉዞ ሲያደርጉ ብፁዕ አቡነ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች ከዶዶላ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና ሰበካ ጉባኤያት ፣ ከሕንፃ አሠሪ ኮሚቴዎችና ከከተማው ነዋሪዎች ሆነው ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ድረስ በመምጣት ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። እንዲሁም የከተማው ሕዝብ በመኪና ፣ በሞተር ባይስክል በብስክሊትና በእግርም ሳይቀር ከዋቢ ሸበሌ እስከ ከተማው ግራና ቀኝ በመሰለፍ ልባዊና ፍቅር በተመላበት አባታዊ አቀባበሉን በሆታ፣በእልልታ፣በመዝሙርና በልዩ ልዩ ውዳሴ ለቅዱስነታቸው ደስታውን ገልጾላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎ ስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዚህ እፁብና ድንቅ አቀባበልና አጀብ ግራና ቀኝ እየባረኩ ከቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ ከቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረት ተሰብስቦ የቅዱስነታቸውን መምጣት ሲጠባበቅ የቆየው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በሆታና በእልልታ ደስታውን ሲገልጽላቸው ቅዱስነታቸውም በተቀደሰ ቡራኬአቸው ሕዝቡን እየባረኩ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ ። አጭር ጸሉ ት እንዳደረሱም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ጸሉ ተ ኪዳን አደረሱ ።

ቅዱስነታቸው በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ተገኝተው የክብር መንበራቸውን እንደያዙ ሊቃውንቱ መዘምራኑና የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ለቅዱስነታቸው አቀባበል ያዘጋጁትን ግሥ ቃኝተው በቅ ደም ተከተል ያሬዳዊ መዝሙር አስምተዋል ። ከዚያም ብፁዕ አቡነ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቅዱስነታቸውን እንኳን ደህና መጡልን የሚል የመግቢያ ንግግር አድርገው እንዳበቁ አንድ ተወካይ ። «ይህች ዕለት ታሪካዊት ናት ። ይኸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎ ስ የሐረርጌ ሊቀ ጳጳስ በሚባሉባት ጊዜ በባሌ ጎባ ወደዚሁ መጥተው የዚሁ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ያኖሩበት ጊዜ እንደዛሬ ቀን ስለነበረ ዛሬም ዳግ ም የመንፈስ ቅዱስ ልጃቸው የሆኑ ቅዱስነትዎ ከአ- አበባ መጥተው በመካከላችን በመገኘትዎ እኛ የመንፈስ ልጆችዎም ሲባርኩን ልዩ ስሜት አሳድሮብናል ። ደስታና መንፈሳዊ ኩራትም ተሰምቶናል ። » ስለዚህ ይህች ዕለት ታሪካዊት ናት ያልሁት ስለዚህ ነው ብለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎ ስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ባሰሙት ንግግር «ሕዝቡ ከጠዋት ጀምሮ እስካሁን ድረስ እኛን ሲጠብቅ በነፋስና በጸሐይ መጉላላቱ አሳዝኖናል ሆኖም ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ከአባቶቻችን ተያይዞ የመጣልን የእንግዳ አቀባበልና አከባበር የእርስ በርሳችን ፍቅርና መዋደድን የሚያመለክት ስለሆነ በጣም ደስታ ይሰማናል ። እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ፍቅራችን ከሌላው ሁሉ የተለየ ነው» እንፋቀራለን ፣ እንተዛዘናለን ፣ እንረዳዳለን ። ይህም ከአባቶቻችን ተያይዞ የመጣልን መሠረታዊ ትሩፋት ነው ።

ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከተገኙበት ጊዜ ጀምሮ በሀገራቸው በኢትዮጵያ ያስፋፉት (የመሠረቱት) እንደሌሎቹ አምልኮተ ጣኦት ሳይሆን አምልኮተ እግዚአብሐ ርን ነው ። ለዚሁም ማስረጃችን በዘመነ ነቢያት «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ተብሎ የተነገረው ትንቢታዊ ቃል ነው ።

ባሁኑ ጊዜ በሀገራችን በኢትዮጵያ ብዙ አዳዲስ ሁኔታዎችን ሲፈጠሩ እንደሚታዩ ሁሉ ቤ ክር



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኒቱን እንደነርሱ አድርገው ያዩአት ይሆናል ። ነገር ግን እንደሀሳባቸውና እንደምኞታቸው እውነት ሊሆን አይችልም ። እናት ቤተ ክርስቲያናችን ለእናት አገራችን ኢትዮጵያ ያበረከተችው የሥራ ፍሬ ፣ ያደረገችው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ከምንናገረው ቋንቋ ፣ ከምንተርከው ታሪክ ፣ ከምንመስለው ምሳሌ ፣ ከምንናገረውና ከምናሳየው ባሕልና ወግ ሁሉ ከፊደላችን ፣ ጀምሮ እስከ ቅዋያተ ቅድሳቶቻችን ድረስ የሚታዩት ብርቅና ድንቅ ቅርሶቻችን አስገኚ ይህች ባለታሪክ እናት ቤተ ክርስቲያን ናት ። ስለሆነም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መገኘት ወይም መወለድ ታላቅ ኩራት ነው ።

ይህች ቤተ ክርስቲያን በዓለም እንድትታወቅ ያደረጉአት አባቶቻችን ናቸው ። በምን ? ብለን የምንጠይቅ እንኖር ይሆናል መልሱ በሥራ ነው እኛ የታሪከኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን እያልን አንዳችም ሥራ ሳንሠራ ብንቀመጥ ከእውነት የራቅን ነን ። እውነተኞች ልጆችዋ መሆናችን የሚታወቀው እንደ አባቶቻችን አስደናቂ ሥራ ሠርተን ስንገኝ ነው ።

አሁን ገንዘብ ፣ ገንዘብ እንላለን ገንዘብ የምንለው ጉልበት ለመግዛት ነው ። እያንዳንዳችን በጉልበት ፣ በገንዘብ በሀሳብ አንድ ብንሆን ይበን ቤ/ክርስቲያን በጥቂት ጊዜ ውስጥ ልንሠራው እንችላለን ገንዘብ እዚህ ቢከመር ከልብ ካልተጠቀምንበት የገንዘብ ጥቅም ሊታወቅ አይችልም እዚህ ላይ ለመተባበር ፣ ለመሥራት ፈቃደኛ የማይሆን ሰው እንደማይኖር ማወቅ ያስፈልጋል ። አሁንም ቢሆን ለተቀደሰ ሥራ ፈቃደኛ የማይሆን አባት እንደማይገኝ የታመነ ነው ። ስለሆነም ይህን ቤተ ክርስቲያን ሁላችንም ተባብረን ፣ ሠርተን መጨረስ አለብን ፣ በአቡነ ሰላማ የሀ/ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አማካይነት የአ-አበባ አብያተ ክርስቲያናት ለዚሁ ቤ ክርስቲያን ማሠሪያ የተቻላቸውን ያህል ረድተዋል ። እኔም አሁን ከብፁዓን አባቶች ጋር ሁነን እዚህ ስንገኝ የግድ ጥቂት ገንዘብ መወርወር አስፈላጊ ስለሆነ ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ሰጥቼአለሁ ።» ብለዋል ። በመጨረሻም አባታዊ ቡራኬአቸውን ለምእመናን ልጆቻቸው አስተላልፈው ጉዞአቸውን ወደባሌ ሀገረ ስብከት አመሩ ። በየመንገዱም የቅዱስነታቸውን ፊት ለማየት የሚመኙትን ሁሉ በደስታና በእልልታ ይገልጹላቸው ነበር ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ላይ ባሌ ጎባ ደብረ መድኃኒት መ/ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ብፁዕ አቡነ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሀ/ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና ሠራተኞች የየአብያተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤያት ኃላፊዎች ልብሰ ተክህኖ የለበሱና መስቀል የያዙ ካህናትና ዲያቆናት፣ ጥንግ ድርብ የለበሱ ሊቃውንትና መዘምራን ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥት ተወካዮች በብዙ ሺህ የሚቆጠር የከተማው ሕዝብ በቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረት ተገኝተው በእልልታ ፣ በዝማሬና በጭብጨባ ደስታቸውን በመግለጽ ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው የሕሊና ጸሎት አድርሰው ወደ ቅድስቱ በመውጣት ጸሎተ ኪዳን አድርሰዋል ፣ ወደ ዐውደ ምሕረቱ በመውጣትም በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እንዲተገኙ ሊቃውንቱ ለቅዱስነታቸው አቀባበል ያዘጋጁትን ግሥ ቃኝተው ለ፳ ደቂቃ ያህል ሲያሸበሽቡ ተመልክተዋል ። እንደዚሁም የሰንበት ት ቤት መዘምራን ተመሳሳይ ዝማሬ አሰምተው እንዳበቁ ከልዩ ልዩ ሊቃውንት ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔዎች ተበርክተዋል ። የተበረከቱ ቅኔዎችም የጥንቱ መምህራን ሊቃውንት የሚመስል የሚስተካከል ረቂቅ ምስጢር ያዘለ ነበር ።

ከዚህ በማያያዝም ብፁዕ አቡነ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ስለ ቅዱስነታቸው የባሌ ጎባን ከተማና ሕዝበ ክርስቲያን ለመጎብኘት በጎባ ከተማ በመገኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ በጎባ ሕዝበ ክርስቲያን ስም ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበዋል ። ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎችም እጅግ በጣም ደስታ የተሰማቸው መሆኑን በንግግር ገልጸዋል እንዲሁም ከአዲስ አበባ ጀምሮ ባሌ ጎባ ድረስ ቅዱስነታቸውን ብፁዓን አባቶችና የክብር ተከታዮቻቸውን እግዚአብሔር በከንፈ ረድኤት ጠብቆ በሰላም ስላደረሳቸውም ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና አቅርበዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አቀባበል ላደረገላቸው ለባሌ ጎባ ሕዝበ ክርስቲያን አባታዊ ቃለ ምዕዳንና ቡራኬ አድርገውላቸዋል ።

ከቅዱስነታቸው ን ግ ግ ር «የእናን ተን የልጆቻችንን ዓይን ለማየት ከአዲስ አበባ ተነሥተን ስንመጣ በመንገድ እንደእናንተ ያሉ ልጆቻችን ፣ አባት እናቶቻችን አትለፉን ባርኩን እያሉ ስለጠየቁን የእናንተም ወንድሞችና እህቶችም ስለሆኑ አትቀየሙንም አታዝኑብንም ብለን ሰዓታትና ደቂቃዎች ስላሳለፍንባችሁ ቅር እንዳማትሰኙ ተስፋ እናደርጋለን ብለዋል ።

አያይዘውም ዛሬ የእናት ቤተ ክርስቲያናችሁን ታላቅነት አስመስክራችኋል ጥንታዊነት ዋንና ታሪካዊነትዋንም በተግባር አረጋግጣችኋል ። የኛ ሁነው በተግባራችው የኛ ያልሆኑ ይህን የመሰለ ባሕላችንና ታሪካችን ለማጥፋት ጥረት በማድረግ ላይ የሚራመዱ አሉ ። በአንዳንድ ጥቅም እየተነሣሡም እናት ቤተ ክርስቲያናችንን አርጅታለችና በቀለም ፣ በልዩ ልዩ ስዑሠራሽ ጌጥ አድሰን እናሳያችኋለን እያሉ እንዳያስቷችሁ ላስጠነቅቃችሁ እወዳለሁ ።

ቤተ ክርስቲያናችን ረዥም ታሪክ ንጹሕ ሃይማኖት ያላት ከመሆንዋም በላይ እያንዳንዱ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ልጅ የሆነ ምእመንም ረዥም ታሪክና ንጹሕ የጽድቅ ጎዳና የተጓዘበት ዘመን ሩቅ ፣ ነው ። ካህናቱ ፣ መምህራኑና ሊቃውንቱም ለቤተ ክርስቲያኒቱና ለሀገሪቱ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በማንም ዕሩቀ ምግባር የማይገመትና የማይጎድፍ ታሪክ ነው ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ምእመናን ባሁኑ ወቅት ስለርጉባንና እሩቃን ወገኖቻችን ማዘንናመራራት ብሎም መርዳትና ማጽናናት ያስፈልጋልና በያላችሁበት ተጋገዙ ተረዳዱ» ብለዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው እንዳበቁ የዕለቱ መርሐ ግብር ተፈጽሞአል ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮም ስለ ቅዱስነታቸው ክብር በሀገረ ስብከቱ የተዘጋጀ ግብዣ በመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተደርጐአል ። በግብዣውም ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት ተገኝተዋል ቅዱስነታቸው ከግብዣው ስነ ሥርዓት በኋላ ወደማረፊያቸው ሔደዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ለየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም አጥቢያ ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ላይ አዲስ በተሠራው በደብረ ታቦር ቅድስት ሥላሴ ቤ ክርስቲያን ተገኝተው የአዲሱን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጸሎት በእፍና በውስጥ ካከናወኑ በኋላ ልክ በ፲፪ ሰዓት በቅዱስነታቸው መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት የቅዳሴው ስነ ሥርዓት ተጀምሮ እስከ ሁለት ሰዓት ተኩል ድረስ ተከናውኖአል ።

ከዚያም ታቦተ ሕጉ ወደ ዐውደ ምሕረቱ ወጥቶ ሥርዓተ ዑደቱ ተከናውኖ በተዘጋጀለት ሥፍራ እንደቆመ ሊቃውንት የዕለቱን ግሥ ቃኝተው ለ፲፭ ደቂቃ ያህል አለዝበው አሸብሽበዋል ። የደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘምራንም ተመሳሳይና ያሬዳዊ ጣዕመ ዜማ እያሰሙ ዘምረዋል ። ከዚህ በኋላም የደብረ ታቦር ቅድስት ሥላሴ ሕንፃ ቤ ክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴ ያዘጋጀውን ልዩ መርሐ ግብር ቀጥሎአል ።

በዕለቱ ለሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ አባሎች በሙሉ በሀሳብ ፣ በገንዘብና በጉልበት ለረዱት ምእመናንም ሁሉ የተዘጋጀው ሽልማት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እጅ ተሰጥቶአል ። በዚሁ ጊዜ የከተማው ሕዝብ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በመካከሉ ተገኝተው ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚጠቀምበትንና የዘለዓለም ቤቱ የሆነውን ሕንጻ ቤ ክርስቲያን ባርከው ቀድሰው ፣ አባታዊ ጣዕመ ትምህርታቸውን ሰጥተዋል። ለቤተ ክርስቲያኑም ቅዱስ ፓትርያርኩ ፴ሺህ ብር ለግሰዋል ። በመጨረሻም ለሕንጻ ቤ ክርስቲያኑ ሌት ተቀን ደክመው እዚህ ላደረሱት ታማኞች የሕንጻ አሠሪ ኮሚቴዎች ሽልማት ስለሰጡ የተሰማውን ደስታ በእልልታና በጭብጨባ ለደቂቃዎች ያህል በዐውደ ምሕረቱ ላይ አስተጋብቶአል ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በቅዱስነታቸው ፈቃድ ትምህርት ሰጥተዋል ብፁዕነታቸው በሰጡት ትምህርት የሕዝቡን ክርስቲያናዊ ስሜትና መንፈሳዊ ጥንካሬ በማድነቅ ገልጸዋል እግዚአብሔርን ያገለገለ ፣ መመስገኛውና መቀደሻውን ያውም በአንድነቱና በሦስትነቱ ስም ይህን የመሰለ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ቅዳሴ ቤቱን ለማክበር መብቃት በዓይን ዓይቶ ፈጣሪን ለማመስገን ዕድል ማግኘት ምንኛ መታደል እንደሆነም አስረድተው ትምህርታቸውን ካጠቃለሉ በኋላ ቅዱስነታቸው ለመንፈስ ልጆቻቸው ቃለ ምዕዳንና አባታዊ ቡራኬ ይሰጡአቸው ዘንድ አሳሰበዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎተ ቡራኬአ



ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት ቅዱስነታቸውን በክብር ሲቀበሉ





www.ethiopianorthodox.org



ለቅዱስ ፓትርያርኩ ካህናቱና ምእመናን አቀባበል ሲያደርጉላቸው

ቸውንና የወንጌል ትምህርትታቸውን እግዚአብሔርን በማመስገን ጀምረው የባሌ ጎባ ምእመናን ይህን የመሰለ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ቅዳሴ ቤቱን ለማክበር በመብቃቱ የተሰማቸውን ደስታ በማድነቅና በማመስገን ገልጸዋል አያይዘውም ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ በዚያን ጊዜ በሕይወተ ሥጋ የነበሩ አሁን በሞት ጥላ ያረፉ ወገኖች የገንዘብ ፣ የሀሳብና የጉልበት አስተዋጽኦ ያደረጉ እንደነበሩ ግልጽ ነው ነገር ግን እንደ እናንተ ፍጻሜውን ለማየት ባይችሉ እንኳ በአጸደ ነፍስ ሆነው የትሩፋታቸውን ዋጋ እንደማያጡ አንጠራጠርም ብለዋል ።

ከዚህም በመቀጠል ብፁዕ አቡነ ሰላማን አመስግነዋል ብፁዕነትዎ እንደነዚህ ያሉ የተቀደሱ ምእመናን ይዘው ለሥራ ሲነሡ እነርሱ የበለጠ ለመሥራት ቀድመው የሚገኙ በመሆናቸው በተሰጠዎትና ባገኙት እድል ሊመሰገኑ ይገባል በማለት ብፁዕነታቸውን አድንቀዋል ።የመንፈሳዊ አባቱን ምክርና ትምህርት ሰምቶ በተግባር የሚተረጉም ምእመናን ሁሉ የተባረከና የተመሰገነ መሆኑንም አስረድተው የሕዝቡን ትሩፋት ባርከዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የባሌ ጎባ ሕዝበ ክርስቲያን በእደ መላእክት የታነጸየሚመስል ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ለአገልግሎት በማብቃቱ እርእያነቱና ምሳሌነቱ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉልህ የሚታይመሆኑን አውስተው በተለይም ይህ ቤተ ክርስቲያን በአጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ ስም በመታነጹ ሕዝቡም ከስም በላይ የሆነ ስም ዓለማትን በፈጠረ የሥላሴን መመስገኛ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ለማየት በመብቃቱ ዕድለኛ መሆኑንና የእያንዳንዱን ዋጋ የማያስቀር አምላክም ዋጋውን ለእያንዳንዱ ይከፍል ዘንድ በመመኘት ገልጸው ትምህርታቸውን በጸሎተ ቡራኬ ደምድመዋል ።

የባሌ ጎባ ደብረ ታቦር ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው ካሉት ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ መሆኑን ለመረዳት ተችሉአል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረርጌና የባሌ ሊቀ ጳጳስ በነበሩበት ጊዜ በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ከሐረር ተነሥተው ባሌን በጎበኙበት ወቅት ይህን ቤተ ክርስቲያን ባርከው መሠረት እንዳኖሩና ከዚያም ይህ አሁን የተሠራው ሕንጻ ከመሠራቱ በፊት የነበረው ጥንታዊ ቤ.ክርስቲያን ተሠርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን ከደብሩ የተገኘው ዘገባ ያረጋግጣል ።

የደብረ ታቦር ቅድስት ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን ከከተማው ትንሽ ወጣ ያለ ሆኖ በከፍተኛ ሥፍራ የተተከለ ነው በእርግጥም በአቀማመጡና በተፈጥሮው ጌታችን ግርማ መለኮቱን የገለጸበት የኢየሩሳሌምን ደብረ ታቦር ስለሚመስል ስሙ በትክክል የወጣለት ነው ። ቤተ ክርስቲያኑ ከተተከለበት ጊዜ እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ታላላቅና ባለታሪክ አባቶች ምሁራንና ሊቃውንት አስተናግዶአል አሳልፎአል ። የብዙ ታላላቅ ምእመናን ዓጽም ያረፈበትና ዛሬም ጊዜአቸውን በመልካም ስነ ምግባር ያሳለፉ ወገኖች ያንቀላፉበት ሥፍራ መሆኑን አበው ይናገራሉ ።

ቀደም ሲል በዚህ ሥፍራ የነበረው ቤተ ክርስቲያን በማርጀቱ ለማሠራት ኮሚቴ ሲቋቋም ፈቃደ እግዚአብሔር ሳይሆን ቀርቶ ሊዘገይ መቻሉንና በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም የመቅደሱ ግራ ክፍል





የከተማው ሕዝበ ክርስቲያን አቀባበል ሲያደርጉላቸው

በእሳት ተቃጥሎ በመፍረሱ በ፲፱፻፹፭ ዓ/ም የአጥቢያው ሰንበት ት/ቤት ፣ ምእመናን ካህናቱን በማስተባበር ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጎ ቤ/ክርስቲያኑ እንዲሠራ ጥያቄ በመቅረቡና ወዲያውኑም ኮሚቴ ተቋቁሞ ይህ አሁን በቅዱስነታቸው የተባረከውና ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው ሕንጻ ቤ/ክርስቲያን ሊሠራ መብቃቱን ከደብሩ ታሪክ ማኅደር የተገኘ ዜና ያረጋግጣል ። በዚህ ቤተክርስቲያን ስም ብዙ ድኩማንና ሕሙማን እንደሚረዱና መምህራን ሊቃውንትም ምን ጊዜም እንደማይለዩት የታሪክ ማኅደሩ በስፋው ያብራራል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትኢዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ባሌ ጎባ ገብተው እስከ ወጡበት ድረስ የሕዝቡ መንፈሳዊ ስሜትና ያለውም የአባቶች ፍቅር የቱን ያህል እንደሆነ ለመግለጽ ቃላት አይገኝለትም የቅዱስነታቸውን መስቀል እየተሳለመ ከፊቱ የሚፈልቀው የደስታ ስሜት ተመልካቹን እንኳ ልዩ ስሜት አሳድሮበታል ልብሳችው የነካው ፣ መኪናቸው የዳሰሰው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቀርቶ ከብፁዓን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት እንኳ ቡራኬ ያገኙ ፣ ከነርሱ አልፎ ከክብር ተከታዮቻቸው ሰላምታ የተለዋወጡ የሚሰማቸው ክብርና ደስታ ከእያንዳንዱ ስለሚታይ የባሌ ጎባ ምእመናን ያላቸውን የሃይማኖት ፣ ጽናት ፣ የአባቶች ፍቅርና የወገን አከባበር ምንጊዜም የማይረሳና ማራኪ አርኪ ወገንነቱ በቀላሉ የማይረሳ ብሩህ ገጽ ያለው ሕዝብ ነው ብለን ከመደምደም በቀር ታሪኩን ጽፎ ለመጨረስ አይቻልም ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በ13-6-87 ዓ/ም በዩኒሴፍ በጤና ጥበቃና በቤተ ክርስቲያናችን ስም በናዝሬት ከተማ የሚከፈት ዐውደ ጥናት ስለነበራቸው የባሌ ጎባን ሕዝብ መክረው ፣ አስተምረው ቡራኬ ሰጥተው ሕዝቡ ናፍቆት እስኪወጣለት ሁለት ሦስት ቀን እንዳይቆዩለት እንዲህ ዓይነቱ አስቸኳይ የሥራ ጊዜ እንዳጋጠማቸው ገልጸው ከቅዳሴውና ከትምህርቱ በኋላ ከቀኑ በ፯ ሰዓት ጉዞአቸውን ወደ አዲስ አበባ ቀጠሉ ። እግረ መንገዳቸውንም ሮቤን ጎብኝተዋል ። ሕዝበ ክርስቲያኑ ካህናቱና ዲያቆናቱ መስቀል ይዘው ሕዝቡም በንቂስ ወጥቶ ተቀብሎአቸዋል ቤተ ክርስቲያኑና ሕዝበ ክርስቲያን ጉብኝተው ትምህርት ሰጥተው ለወደፊ ቱበስፋት የሚጎበኙበትንም ቀጠሮ አስይዘው ጉዞአቸውን ወደናዝሬት በመቀጠል ናዝሬት ከተማ ከምሽቱ ልክ ፩ ሰዓት ተኩል ሲሆን ደርሰዋል ።

## "አባት ሆይ ይቅር በላቸው"

ከ፮ኛው ገጽ የዞረ

ነው ቢጅሱ ላይ ደፍተው "የእስራኤል ንጉሥ ሆይ እያሉ እዘበቱበት ይቅርታ አወጀላቸው ። በጲላጦስ አደባባይ ፊት ' ይሰቀል ! ይሰቀል ! ይሙት "ብለው ለፈረዱበት" የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ብሎ ጸለየላቸው። ከመሰቀሉ በፊት "ጠላቶቻችሁን ወደዱ ፣ ለሚቃወሙአችሁም መልካም አድርጉ ፣ የሚረግሙአችሁን መርቁ" ሲል ያስተማረው ጌታችን በዕለተ ዓርብ ስለ እኛ መከራን በተቀበለ ጊዜ ፣ እንደዚሁም በመስቀል ተሰቅሎ እያለ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ በመጸለይ ያስተማረውን ትምህርት በተግባር ገለጸው ።

ስለዚህ ጌታችንን የሚያምንና የሚወድ ሁሉ የጌታችን አርአያ መከተል ይገባዋል ። "እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ ፣ እናንተም ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌየን ሰጥቻችኋለሁ" (ዮሐ ፣ ፲፫ ፣ ፲፭) ሲል ጌታችን እንዳስተማረን እንደ በደሉን እንበድላቸው ፣ እንደጠሉን እንጥላቸው ፣ እንደረገሙን እንርገማቸው ሳንል የጌታችንን አርአያ ተከትለን ሁሉንም በእኩልነት መውደድ ይገባናል ። ስለሁሉም በመጸለይ ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑን ከልብ መገንዘብ ይገባል ።

"ወስብሐት ለእግዚአብሔር"

አባ ገብርኤል

የምዕራብ ሸዋ ሊቀ ጳጳስ



www.ethiopianorthodox.org

# ሦስቱ መስቀሎች በጎልጎታ

በቀድሞ ዘመን የእስራኤል ዋና ከተማ በነበረው በኢየሩሳሌም ግንብ አጠገብ ጎልጎታ ተብሎ የሚጠራ አንስተኛ ኮረብታ ነው ። ይህም ሥፍራ «የራስቀል » በመባል የተለየ ስም እንዳለው በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ፲፱ ቁ ፲፯ ተጠቅሶአል በዕብራይስጥ ጎልጎታ ሲባል በግእዝም ቀራንዮ ይባላል ። ስለዚህ አንድ መንፈሳዊ ደራሲ «የአበው ተስፋ በግርያም ድንግል ተፈጸመ መድኃኒት መስቀልም በቀራንዮ ተተከለ» ሲል ተናግርአል ።ይህም ቀራንዮና ጉልጎታ አንድ መሆናቸውን ያመለክታል ሊቃውንቱም በትርጓሜአቸው ሲያትቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል የቆመው አዳም በተቀበረበት ቦታ ላይ ስለሆነ«የራስቅል»ተብሏል ይላሉ ። ሦስቱ መስቀሎች ዓርብ ጠዋት ወደ ረፋዱ ላይ በጎልጎታ ላይ ተተክለው ቆመው አላፊ አግዳሚው ይመለከታቸው ጀመር እነዚህ መስቀሎች የቆሙበት ዋና አላማ ለቀጣት ሲሆን ሦስት ሰዎች ተሰቅለውባቸው ነበር በመካከል የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን በቀኝና በግራ የተሰቀሉት ሁለቱ ወንበዴዎች ነበሩ በየራስጌአቸውም የሡሩትን ወንጀልና የገደሉትን የስም ዝርዝር ሲገልጽ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእብራይስጥና በሮማይስጥ የተጻፈው « ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ «ይልና በተጨማሪም ሰንበትን ሽሮ በሽተኞችን ፈውሶአል ። ራሱንም የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአል» የሚል ነበር ። ይህንም ጽሑፍ የሚያውቀው እያነበበ የማያውቀውም እያስነበበ በኢየሱስ ላይ የስድብ ውርጅብኝ ያወርዱበት ነበር ። ግማሹም ራሱን እየነቀነቀ ሲዝት የተረፈውም ይስቅበትና ይቀልድበት ነበር ። እንዲያውም አብረውት ከተሰቀሉት አንዱ እንደ ሕዝቡ ያፌዝበት ጀመር ሰዓት እየገፋ ሲሄድ መከራው በዚያው ልክ እየበረታ መሄዱን ቀጠለ ።

ከሁለቱ ሽፍቶች በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ወደ ተሰቀለው ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመለከተ በመካከላቸው የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አባት ሆይ ይቅር በላቸው የሚያደርጉትን አያውቁምና» እያለ ለጠላቶቹ ሲጸልይ ሰምቶ ወንበዴው ተገረመ ።

አንድ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው ሕይወቱን አሳልፎ እየሰጠ ለገዳዮቹ ሲጸልይ መስማት በእርግጥ የሚያስገርም ነበር ምንም እንኳን የተሰቀሉት ሁሉ ሰዎች ነፍስን በመግደልና የሰው ቤት በመዝረፍ የኖሩ ሽፍቶች ቢሆኑም በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ስድብ ቀልድና ጩኸት በእነርሱ ላይ ሳይሆን በመሐከላቸው በተሰቀለው በክርስቶስ ላይ በመሆኑ የሚያስደንቅ ነበር ።

የጌታችን ኢየሱስ ትዕግሥቱ በቀኝ በኩል የተሰቀለውን የሽፍታውን ልብ ስለነካው አብሮ ለተሰቀለው ጓደኛው እንዲህ አለ «እኛስ በሥራችን ሥቃያችን እንቀበላለን ይህ ሰው ግን ምንም ለሞት የሚያደርሰው ስሕተት አላደረገም» ካለ በኋላ ፊቱን ወደ ኢየሱስ መልሶ የፈጸመውን በደል አስበ ኃጢአቱንም እንደሚያስተሠርይለት አመነ ።

ሕይወትን የሚሰጥ ኢየሱስ እንደሆነ ተገነዘበ ወዲያው «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ ስትመጣ እኔን አስበኝ» ሲል ጸለየ ይህንን ያለው ኢየሱስ ጌታ መሆኑንና መንግሥትም እንዳለው መንፈስ ስለገለጸለት ነው በዚያን ጊዜ በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የጠየቀው በመጣ ጊዜ በመንግሥቱ እንዲያስበው ብቻ ነበር ኃጢአተኞችን በንስሐ ተቀባይ የሆነው ስለኃጢአተኞች የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወዲያውኑ ከጠየቀው የበለጠ ምሕረት ሊሰጠው «ዛሬውኑ አንተ ከኔ ጋራ በገነት ትኖራለህ» አለው ይህም አባባል በጎልጎታ የተላለፈ የመልእክቶች መልእክት ዘወትር አማኞችን ሲያስደንቅ ይኖራል ።

ወደ ገነት የሚወስደውም መንገድ በኪሩቤልና በነበልባል ሰይፍ እየተጠበቀ ተዘግቶ ይኖር ነበር አሪት ዘፍጥረት ምዕ-፫ ቁ ፳፬ ስለዚህ በጎልጎታ በተተከለው መስቀል ላይ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም የገነት በር ተከፈተ ወንበዴዎቹ የተሰቀሉባቸው ሁለቱ መስቀሎች ለቅጣትና ለማስፈራሪያ ሲሆኑ የክርስቶስ መስቀል ግን ለቅጣት ሳይሆን ስለ ዓለም ሕይወት መሆኑ በተግባር ተረጋገጠ ።

የሰው ልጆች ኃጢአት ለብዙ ዘመን በሰማይና በምድር መሐከል ታላቅ የሞት ገደብ ፈጥሮ ይኖር ነበር በጎልጎታ ተተክሎ የቆመው መስቀል ግን የክርስቶስ መከራና ስቃይ ስለተፈጸመበትና በላዩም ላይ ክቡር ደሙ ስለፈሰሰበት ሰማያውያንና ምድራውያንን አንድ አደረገ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ ።

ምንም እንኳን ጎልጎታ (ቀራንዮ) ለጊዜው የመከራና የኀዘን ቦታ ቢሆንም ለኃጢአተኞች መጠጊያ ከመሆኑም በላይ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ በር ለማንም የተከፈተው በጎልጎታ በመሆኑ ለክርስቲያኖች ታላቅ ደስታ አስገኝቷል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ «ሁሉ ተፈጸመ» ባለ ጊዜ የክርስቲያኖች ነጻነት ፍጹም ሆነ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ሆኖ የሰጠው የምሕረት አዋጅና ያስገኘው ነፃነት ለሰው ልጆች ሕይወትን ሰጠ ።

ክርስቶስ ለኛ ነጻነትን ለመስጠት ራሱን ነጻነት እንደሌለው አደረገ ለኛም ሕይወት ለመስጠት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ ። ሥልጣን እንደሌለው ሆኖ በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት ቆሞ ተወቀሰ ። ሁላችንም በሕይወት እንድንኖርና ሕይወትም እንዲበዛልን ለኛ ሲል ሕይወቱን ሰጠ ስለዚህ ቪካናንድ የተባለው ሰው ሴቶች የገንዘብ አስተዋጽኦ እያደረጉ ችግረኞችን እየረዱ ሕይወት ሲሰጡ እ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



# የሕማማት ሳምንት ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕማማት መጀመሪያ በሆነው እሑድ (ሆሣዕና) በአህያ ተቀምጦ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ሕፃናትና ሽማግሌዎች የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው "መድኃኒት መባል ከዳዊት ወገን በሥጋ ለተወለደው አምላክ ይገባል" በማለት አዳኝነቱንና አምላክነቱን እየመሰከሩ ተቀበሉት ። ክርስቶስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ ልዩ ምሥጢር አለው ይኸውም በትንቢተ ዘካርያስ ፱ ፡፱ የተነገረው ትንቢት እንደተፈጸመ ለማስረዳት ፪ኛ በአህያ የተቀመጠው ሰው ሌላውን አሳድዶ አይዝም እርሱም ሮጦ አያመልጥም ። ክርስቶስም በእምነት ለሚፈልጉት የማይታጣ ቅርብ ሲሆን በእምነት ለማይፈልጉት ግን የማይገኝ መሆኑን ያስረዳል ።

ሰኞ በቤተ መቅደስ ይሸጡና ይለውጡ የነበሩትን አባረረ ቤተ መቅደስ የጸሎት ቤት እንጂ የንግድ ቤት አለመሆኑን አስተማረ ። ፍሬ ያልተገኘባትን በለስ ረገመ በበለስ አንጻር ኃጢአትን ረገመ አስወገደ ። ሰኞ የተረገመችው በለስ ማክሰኞ ደርቃ ተገኘች በስምዖንም ቤተ ሳለ ማርያም እንተ ዕፍረት ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ሽቱ አምጥታ ቀባችው " ሽቱው በወርቅ ተሸጦ ለነዳያን ቢመጸውት ባልተሻለም ነ፡ር "በማለት ደቀ መዛሙርቱ ሲያጉረመርሙ" ነዳያን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉ እኔ ግን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖር ምና መልካም አደረገች" አለ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፫-፰ ። ስለ ትንሣኤ ሙታንና ስለ ግብር አከፋፈል እንዲሁም ሥራውን ሁሉ በማን ሥልጣን እንደሚሠራ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሰጠ ።

ረቡዕ አይሁድ ጌታን ለመግደል ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ ። የጌታ ምክረ ሞት ተፈጸመ ። እንዲሁም እንደሚይዙት ቀደም ብለው ከይሁዳ ጋር ተስማሙ ። በዚህ ዕለት የጌታ ምክረ ሞት በመፈጸሙ አንጻር ድኅነተ ዓለም ተጀመረ ከዚህም የተነሣ ረቡዕ "ጾመ ድኅነት" በመባል በየሳምንቱ እንዲጾም ሆነ ሐሙስ የመጨረሻውን የፋሲካ እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በላ ከእራት በኋላ መሥዋዕተ አሪትን ሽሮ መሥዋዕተ ወንጌልን ተካ ሥርዓተ አሪትን ለውጦ አዲስ ሥርዓተ ቁርባን ሠራ ። ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮-፳፯ ። የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ" ያደረግሁላችሁን ታያላችሁ ? እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ከአጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል ። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁት እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ ።" (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫-፲፭ በማለት ትሕትናን አስተማረ በጌቴሴማኒ ጸለየ "ወደፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ" ማቴ ፳፮ ፡ ፵ ሲል ጸሎት ሰዎችን ከልዩ ልዩ ፈተና እንደሚያድን አስረዳ ይሁዳ ጌታችንን ያስያዘው ሐሙስ ማታ ነው ።

በአይሁድ እጅ ከገባ ጀምሮ እስከ ተሰቀለበት ሰዓት ድረስ ከአንዱ ሊቀ ካህናት ወደ ሌላው ቤት ሲመላለስ በሊቃነ ካህናቱና በሕዝቡ ፊት እየቆመ የሐሰት ምስክሮች "በሰንበት ድውይ ፈውሶአል የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ አል ቤተ መቅደስን አፍርሼ እንደገና በሦስት ቀን እሠራለሁ" ሲል ሰምተናል በማለት ደግ ሥራውን ክፉ ጻድቁን አምላክ ኃጥእ በማስመሰል ሲመክሩ አደሩ ።

ዓርብ ጠዋት የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሉች በአንድነት ተሰብስበው ኢየሱስ ክርስቶስን አሥረው ወደ ገዡ ወደ ጲላጦስ አቀረቡት ክርስቶስ ሞት የሚገባው መሆኑንም ለጲላጦስ አስረዱት ሕዝቡ ሁሉ በአንድ ድምፅ "ሞት ይገባዋል" እያሉ እንዲጮሁ አስተባበሩ ፣ ጲላጦስ ክርስቶስን መረመረው ክርስቶስ ግን ምንም በደል የሌለበት ሆኖ ተገኘ ፤ ጲላጦስም እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጥቦ የክርስቶስን ጽድቅ መሰከረ ።

በቀትር ጊዜ /ስድስት ሰዓት) ክርስቶስ በሁለት ወንጀለኞች መካከል በመስቀል ላይ ተሰቀለ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ዓለም በሙሉ ጨለማ ሆነ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፬ ፀሐይ ጠቆረ ደም ሆነ ከዋክብት ረገፉ በዘጠኝ ሰዓት "አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፮ በማለት በራሱ ሥልጣን ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው ለየ ። በዚህም ጊዜ መንጦላዕተ ቤተ መቅደስ ከሁለት ተቀደደ ድንጋዮች ተከፋፈሉ ተፈረካከሱ መቃብራት ተከፈቱ ሙታን ተነሡ ።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ሰባት ተአምራት ተፈጽመዋል እነርሱም ፩ የፀሐይ መጥቆር ፪ የጨረቃ ደም መሆን ፫ የከዋክብት መርገፍ ፬ የቤተ መቅደስ መጋረጃ መቀደድ ፭ የድንጋዮች መፈረካከስ ፮ የመቃብር መከፈት ፯ የሙታን መነሳት ናቸው ።

እነዚህ ሰባቱ ተአምራት በመባል የሚነገሩ ዓበይት ተአምራት ናቸው ።

ዓርብ ወደ ማታ ዮሴፍ የተባለ የአርማትያስ ተወላጅ ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የጌታችን ሥጋ ከመስቀል አውርዶ እንዲወስድና እንዲቀብር ጠየቀ ጲላጦስ የኢየሱስን ሥጋ ከመስቀል አውርደው ይሰጡት ዘንድ አዘዘ ። ዮሴፍም በንጹሕ ግምጃ ከፍኖ ቀበረው መለኮት በአካለ ሥጋ በመቃብር አደረ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን በግዞት ለነበሩት ነፍሳት ነፃነት ሰበከላቸው ፩ኛ ጴጥ ፫ ፡ ፲፰-፲፱ ። በክርስቶስ ሕማመ ሥጋ የአዳም ልጆች ሕማመ ነፍስ ተወገደ በክርስቶስ መከራ የአዳም በደል ተሠረየ ። ክርስቶስ መስቀልን በመሸከሙ በአዳም ልጆች ትከሻ ላይ የነበረው ከባድ የኃጢአት ሸክም ከአዳምና



www.ethiopianorthodox.org

ከልጆቹ ትከሻ ወረደ በክርስቶስ ሞት አዳም ከነል ጆቹ ከሲኦል ወጣ ከሞተ ነፍስ ዳነ ስለዚህ ረቡዕና ዓርብ ከበዓለ ሃምሳ በቀር በጾም ይከበራሉ የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምት ቀበላቸው ሰባት አጽዋማት አንዱ ይኸው ጾመ ረቡዕ ወዓርብ ነው እርሱም ጾመ ድኅነት ይ ባላል ።

ይህ ሁሉ መከራ በክርስቶስ ላይ ሲፈጸም ባል ተገባውም ነበር ግን ራሱ ክርስቶስ ለእኛ ቤዛ ይሆን ዘንድ ስለመጣ ሊቀበለው የማይገባውን ተቀበለ ሕመም ሳይኖርበት ታመመ መታሰርና መገረፍ ሳይገባው የኋሊት ታሠረ ፊቱን በጥፊ ጸፋት ምራ ቃቸውን ተፋበት ራሱን በዘንግ መቱት ይሄን ሁሉ በሚያደርጉት ጊዜ ከቶ አልተቀየመም ከባ ሕርይ አባቱ ከአብ ይቅርታን ጠየቀላቸው እንጂ አልተበቀላቸውም በመስቀል ላይ በምሥማር ሲቸ ነከሩት በጦር ሲወጉት "አባት ሆይ የሚያደርጉ ትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው" አለ ይህ አባ ባል ኃዳጌ በቀል መሆኑን ያስረዳል ።

ተከታዮቹ ክርስቲያኖች የእርሱን ፈለግ ተከ ትለው ክፉ ለ ሚያደርግባቸው መልካም መመለስ እንደሚኖርባቸው ክርስቶስ ስለ እነርሱ የተቀበለ ውና የታገሠው መከራ ያስተምራል ይመክራል ። "የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ዶግሞ ፍለ ጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀበለ ። እርሱም ኃጢአት አላደረገም ተንኮልም በአፉ አልተገኘም ሲሰድቡትም መልሶ አልተሳደበም መከራም ሲቀበል አልዛተም ። ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱ በሥጋው ኃጢአ ታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ ። በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልከቱ ፩ኛ ጴጥ ፣ ፪ ፣ ፳፩-፳፭ አዎ የሰው ልጆች ሁሉ በአዳም በደል ጠፍተውና ተቅበዝብዘው ነበር አሁን በመ ድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የጠፉት ተገኝተዋል ። የተበተኑት ተሰብስበዋል በኃጢ አት ባርነት የነበሩት ነፃነት አግኝተዋል ።

ስለዚህ የሕማማትን ሳምንት ክርስቲያኖች ሁሉ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ያከብሩታል ሳምንቱ የሚከበረው ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳናት ከሊቃውንት ስለ ክርስቶስ ሕማምና ሞት የሚናገሩ ትን መጻሕፍት በማንበብ በጾም በጸሉትና በስግ ደት ሲሆን ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ሳምንት የሚ ያሳልፉት ጥሬ ቆርጥመው ውሃ ጠጥተው ወይም የጨው ቂጣ በልተው በመሬት ላይ ተኝተው ነው የላመ የጣመ አይቀምሱም በአልጋና በምቾትም አይተኙም ይህም ሕማምና ሞት የማይገባው አም ላክ ሰዎችን ከመውደዱ የተነሣ የተቀበለውን ፅኖ ትወ መከራ ለማስታወስ ፍቅሩንና ቸርነቱን በየጊ ዜው ለሚነሣው ትውልድ ለማስተማር ነው ።

ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም

## ሦስቱ መስቀሎች በጎልጎታ

ከዝክ ፲፬ የዞረ

ይቶ «የሀገሬ ሴቶች ሆይ መቶ ሕይወቶች ቢኖሩኝ በናንተ በኩል ያለብኝን የውለታ እዳ ለመክፈል ባልበቃኝም ነበር» ሲል ተናግሮአል ። እኛም ብን ሆን እያንዳንዳችን መቶ ሕይወቶች ቢኖሩን በክር ስቶስ በኩል ያለብንን ውለታ ለመክፈል ባልቻል ንም ነበር ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኛ የሚፈልገው ዘወትር ሞቱንና መከራውን እያሰብን መስቀሉን ተሸክመን እንድንከተለው ስለሆነ ሰላም ያደረገበ ትን ክቡር መስቀል በአንገታችን ብቻ ሳይሆን በል ባችንም ጭምር እንሸከመው ።



## ሆሣዕና በአርያም

ሆሣዕና ማለት መድኃኒት እንደሆነ ይታወ ቃል ሕይወት መድኃኒት ከሆነው ኢየሱስ ከሚለው ስም ጋር በትርጓሜም አንድ ነው በማቴዎስ ወን ጌል በምዕራፍ ፳፩ ቍጥር ፱ እንደተጻፈውም ሆሣ ዕና በአርያም ማለት በሰማይ (በልዕና) ያለ መድኃ ኒት ማለት ነው ።

ሌሎችም መጻሕፍት በዚህ ቃል ይስማማሉ ። ከቤተ ፋጌም ተነሥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በፊትና በኋላ አጅበውት ይጓዙ የነበሩ ሕዝብ ሁሉ ለዳዊት ልጅ መድኃኒት መባል ይገባዋል በእግዚ አብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እያሉ አመስ ግነውታል ዘምረውለታል የሰዎቹስ አያስደንቅም ከ ሁሉም የሚያስደንቀው አዕባን በሰው አንደበት ማመስገናቸው ነው ።

እንግዲህ መድኃኒት ስንል ለነፍስም ባህርይ ሆነ ለሥጋ ባህርይ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን በርግጥ የመድኃኒትን አስፈላጊነትና ጥቅም ከጤ ናማ ሰውነት ይልቅ በደዌ ዳኛ ባልጋ ቁራኛ የተያዙ ሕሙማን በሽተኞች ይረዱበታል ። ለምሳሌ በሆ ስፒታል የተኙ ሕሙማንን በሽተኞችን ብንመለ ከት ሐኪማቸው (ዶክተር ) ለጉብኝት እንኳን ወደ እነሱ ብቅ ባለ ጊዜ ከሰማይ እንደወረደ እንደ እግ ዚአብሔር መልአክ እንጅ እንደሰው አያዩትም ይህ ሁሉ ሲሆን የቻለው ሰውየውን ፍለጋ ሳይሆን መድኃኒቱን አግኝቶ ለመ ዳን መሆ ኑ ማን ም አይዘነጋውም ዕውር ምን ትሻለህ ቢሉት ብር ሃን አለ እንዲሉ ማንኛውም በሽተኛ መድኃኒቱን ለማግኘት የሚኖረው ፍላጎት ከዚህ የተለየ አይሆ ንም ፈጣሪዎ ከመድኃኒቴ ጋር አገናኘኝ ብሎ ፈጣ ሪውን የማይለምን ሕመምተኛ አይኖርም ።

(እንግዲህ ሥጋችንን ብቻ ያድነናል ብለን የምናም ንበትን ሐኪማችንንና መድኃኒቱን ለማግኘት ይኸንን ያህል የምንጓጓ ከሆነ ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት ሕሙማነ ነፍስን በትምህርት ማለት ነፍስንም ሥጋ ንም አንድ አድርጎ ባንድ ጊዜ የሚፈውሰውን(የሚያድ ነውን) ኢየሱስ ክርስቶስንማ ፍቱን ሆሣዕና (የታመነ መድኃኒት) ለማግኘት የቱን ያህል ፍላጎት ይኖረን ይሆን ? ፩ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ሰው ራሱ በእምነት በዕውቀት ለሚጠራው ሁሉ ሕይ ወት መድኃኒት ስለሆነ ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ ይፈውሳል ከሞተ ነፍስ ያድናል ። ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፳፭። ፱/ ደዌ ሥጋን በሞት ይገላግሉታል ፣ ምድራዊም ስለሆነ ያልፋል ደዌ ሥጋ የሚባለውም ልዩ ልዩ የሥጋ ደዌ ሲሆን ደዌ ነፍስ ግን የዘለዓለም ነው ይኸውም ኃጢአት ነው ኃጢአት በነፍስ ላይ መከ ራና ፍዳ ፍርድን ያመጣልና ደዌ ነፍስ ይባላል ፣ ንጉሠ እስራኤል ዳዊት ስለ ደዌ ሥጋና ደዌ ነፍስ ልዩነት ሲናገር እንዲህ ብሏል ። ተሣሃለኒ እግዚአ እስመ ድውይ አነ ። ወፈውሰኒ እስመ ተሀውካ አዕ ፅምትየ ። ነፍስ የኒተ ሐ ውከት ፈድፋደ ምንም ቢባል በጽኑዕ ደዌ ተይገርአለሁና ከደዌ አድነኝ ። ሰውነቴ በደዌ ሥጋ ተጨንቃለችና ከደዌ ሥጋዩ አድነኝ ። ይልቁንም በደዌ ኃጢአት ተጨንቃ ለችና ከደዌ ኃጢአቴ አድነኝ ከደዌ ሥጋ ደዌ ነፍስ ያስ ጨንቃልና ይልቁንም ከነፍስ ደዌ አድነኝ ብሏል መዝ ፣ ፩፡፪ ።

ታዲያ ከዚህ ከዘለዓለማዊ ደዌ ኃጢአትም የሚዳነው በሱ በመድኃኒትነቱ በንስሐ በሥጋው በደሙ ወደሱ በመቅረብ እሱን በመዋሐድ ብቻ ነው እንግዲህ የደዌ ሥጋን ናየደዌ ነፍስን ልዩነት በመ ጠኑም ቢሆን ከዚህ ላይ የምንረዳው ይመስለኛል ። ስለዚህ ክርስቶስ በነፍስ በሥጋ ከመጣብን ደዌና ሞተነፍስየሚያድነን ስለሆነ ሆሣዕናመባል ይገባዋል።

መድኃኒትነቱንምለመግለጽ በየመንገዱ ዕው ራንን እየአበራና ልዩ ልዩ ደዌን እየፈወሰ በሚጓዝ በት ጊዜ ይልቁንም ቤተ ፋጌ ተብሎ ከሚጠራው ከተመሳቀለው ጐዳና ሲደርስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ሲልክ በፊታችሁ ወደአለች ሀገር ሂዱ ያን ጊዜ አህያ ከውርንጭላዋ ጋር ታስራ ታገኛላችሁ አምጡልኝ አላቸው ይኸንን ያለበት ምክንያት ሰው ሁሉ ከማእሠረ ኃጢአት የተፈታበት ጊዜ እንደ ደረሰ ለማጠየቅ ነው ምንታደርጋላችሁ የሚላችሁ ሰው ቢኖር ጌታቸው ይሻቸዋል" በሉ አላቸው ፈጥኖ የሚገዛ ከርሱ በቀር የሚገድል የሚያድን እንደሌለ ሲያስረዳ ነው ሆሣዕናበአርያም(በልዕልና) ያለ መድኃኒት ቢባልም ለእኛ ትሕትናን ለማስተ ማር በዘባነ ኪሩብ ሲሠለስ ሲቀደስ የሚኖር እርሱ ባህያ ላይ ተቀምጦ ከቤተፋጌ እስከ ኢየሩሳሌም ያለውን መንገድ ተጉዟል በዚህ ጊዜ ሐዋርያትም ሆነ ሌሎች አዕሩግ ሕፃናት ለነዚህ ለተቀመጠባ ቸው አህዮች ልብሳቸውንም ሆነ ከዱር ቅጠል እየ ቆረጠ ተጎዝጉዞላቸዋል ተነጥፎላቸዋል ይኸንንም ያደረጉት እንኳን ላንተ ለተቀመጥህባት አህያም ክብር ይገባታል መሬት መርገጥ አይገባትም ሲሉ ነው ከዚህ ላይ የምንወስደው ምን ዓይነት ትምህርት ነው ? መልሱ አጭር ነው ። ይልቁንም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ከርስዋ ጋር አንድ ባሕርይ አንድ አካል ሆኖ አማኑኤል ለተሰ ኘባት ለቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ምን ዓይነት ክብር እንደምንሰጣት ምን ዓይነት የምስጋና ገጸ በረከት እንደምናቀርብላት ማሰብና መትጋት እንደሚገባን ያመለክታል ምክንያቱም ሆሣዕና ማለ ት ኢየሱስ ኢየሱስ ፣ ማለት መድኃኒት ማለት ነው እሷም ሆሣዕና (ኢየሱስ) ብለን ለምንጠራው ለመ ድኃኒታችን መገኛ ናትና ።

መ/ሰላም ኃ/ኢየሱስ ከበደ



www.ethiopianorthodox.org

# ከሃያ አራት አብያተ ክርስቲያናት በላይ ያሠሩና የሠሩ ምእመን

«እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን በደስታ ይቀበላል »

የእግዚአብሔርን ስም ማመስገኛ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያ የሚሆን የገንዘብ ችሮታም ይሁን ርዳታ ሲጠየቁ በሐሴት የሚሰጡ ክርስቲያኖች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ይታወቃል ። ይልቁንም በማንም ቅስቀሳና ጉትጎታ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራሳቸውን ለእግዚአብሐር ያስገዙ እግዚአብሔር በሀብታቸው እንዲያዝዝ የፈቀዱ በጎ አድራጊ ምእመናን ሲገኙ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን በደስታ ይቀበላል ። ሲል ያስተማረው ትምህርት በተግባር ይተረጐማል ።

በመግቢያነት የተጠቀምንበትን ጽሑፍ ያሰፈርነው ያለምክንያት አይደለም ። ከ፳፬ በላይ አብያተ ክርስቲያናትን ያሠሩና የሠሩ በጎ አድራጊ ልናስታዋውቃችሁ ነው ። ከትውውቁም በኋላ አርአያነታቸው ሊወሰድ የሚገባው በመሆኑ ምእመናንን የዚህ ቅዱስ ተግባር ተካፋይ እንዲሆኑ ለመጋበዝ ነው ።

አቶ ጌትነት ወርቁ ይባላሉ ።ዕድሜ አቸው ፵፱ ዓመት ነው ። « ከልጅነቴጀምሮ በቤተክርስቲያን የምመላለስ የንዋየ ቅድሳትንና የእድሳት ሥራዎችን በቅርቡ የምከታተልና እግዚአብሐር በፈቀደ መጠን የምችለውን ፈጻሚ በመሆኔ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ » ይላሉ ።

በመልካም ሥራቸው ሁሉ የማይለዩዋቸውን የ፳ ዓመት ባለቤታቸው ወ/ሮ አጸደ ሙላት ሞራል የምትሰጠኝ ለመንፈሳዊ አገልግሉት ዝግጁ የሆነች ረዳቴ የሣራ ተምሳሌት ይሏቸዋል ። ወ/ሮ አፀደ ሙላት በቤት ውስጥ የአቀባበል መስተንግዶ ከማድረጋቸውም በላይ ለቀሳውስትና ለኮሚቴ አባላት የትራንስፖርት ወጪ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ ፤ ያሉን አቶ ጌትነት ባለቤታቸው የዱር ቤቴ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ስትሠራ ሥራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ያለድካምና መሰልቸት አብረዋቸው ለፍጻሜ አብቅተዋል ። የይስማላ ደብረ ገነት ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ለፍጻሜ ሲቃረብ ግን ታመው በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተኝተው ስለነበር በምርቃቱ ሥነሥርዓት ላይ አልተገኙም ።

በዚሁ እለት በገዳሙ ኃላፊ አስተባባሪነት ካህናቱ የጸሉት ፕሮግራም አካሂደውላቸዋል ። በኋላም በእግዚአብሔር መሐሪነት በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት የጸሉት መልስ በመኘቱ በሰላምና በጤንነት ለመኖር ችለዋል ብለውናል።

ክካህማይ ገ/ እግዚአብሔር

ለአቶ ጌት ት ስለመልካም ተግባራቸው የሚያደንቋቸው ሁሉ በየሚችሉት ቋንቋ ያመሰግኗቸዋል ይጸልዩላቸዋል ። ስፋት ያለውን ሥራቸውን የተመለከተው የአቸፈር ወረዳ ነዋሪ ግን በዚህ መልክ ስሜቱን ገልጾላቸዋል ።

አከማችተው ገፋት ወተቱን በጋን
ቢገፉት ቢገፉት የማያልቀውን ።
ተገፍቶ ተገፍቶ ተገፍቶ ቢወጣ
ጌትነት ቅቤ ነው ለራ ስ የሚበቃ ።
ዝቅ አርገው ሱሪህን አታሳየው ባትህን
ሕዝቡ ተጨነቀ እያየው ጉልበትህን ።
እውቀትና ሞያ ባንድ ላይ ሲኖሩ
በጌትነት ላይ ነው ቤት ሠርተው የቀሩ



አቶ ጌትነት ወርቁና ባለቤታቸው ወ/ሮ አፀደ ሙላት

ከላይ የሠፈሩት የግጥም ስንኞች በአቸፈር ወረዳ ሕዝብ ለአቶ ጌትነት ወርቁ ከተበረከቱ እጅግ በርካታ የግጥም ሐረጎች ቆንጥረን የወሰድናቸው ናቸው ። አቶ ጌትነት ወርቁ በምዕራብ ጎጃም ውስጥ የአቸፈር ነዋሪና በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው ። እኝህ ሰው በአቸፈርም ሆነ በመላ የምዕራብ ጎጃም ሕዝብ ዘንድ ያላቸው ተወዳጅነት እጅግ ከፍተኛ ነው ። ይህንን የላቀ የሕዝብ ፍቅር ያገኙት ያለምክንያት አይደለም ።

አቶ ጌትነት እስከ አሁን ድረስ ከራሳቸው እጅግ በርካታ ገንዘብና ንብረት በማውጣት እንደዚሁም የየአካባቢውን ሕዝበ ክርስቲያን በማስተባበርና በመምራት ከ፳፬ በላይ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል ፣ አቶ ጌትነት ለመጀመሪያ ጊዜ ያሠርዋት ቤተ ክርስቲያን በትውልድ መንደራቸው ዱር ቤቴ ላይ የነበረችውን ኪዳነ ምሕረትን ነበር ። ያኔ የሃያ አምስት ዓመት ለግላጋ ወጣት ነበሩ ። ቢሆንም ከጥንት ከጠዋቱ እግዚአብሔር ለዚህ የተቀደሰ ተግባር መርጧቸው ነበርና በዛ ትኩስ የወጣትነት ዕድሜያቸው እንደሌላው ወጣት ሥጋዊ ምኞት ፤ ድሎትና ቅንጦት ሳያምራቸው በነበራቸው መጠነኛ ገንዘብ በእርጅና ምክንያት ውሃ እያፈሰሰየነበረውን የኪዳነ ምሕረት የሣር ክዳን ቤተ ክርስቲያን በአዲስ መልክ አስገንብተው ቆርቆሮ አስበሱት ።

አቶ ጌትነት የኪዳነ ምሕረትን ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ሲነሱ በእጃቸው የነበራቸው አጠቃላይ ገንዘብ ከአሥር ሺህ ያልበለጠ ነበር ። እንደዛም ሆኖ እንዴት ያለችኝን አራግፌ ለዚህ ሥራ አወጣለሁ ብለው አልተጨነቁም ፣ አላቅማሙም ፤ በእግዚአብሔር ተማምነው ሕዝብን አስተባብረው ሥራውን ጀመሩት ። በአሥራ አምስት ሺህ የሕንጻ ሠራተኛ ተዋዋሉ ። በመጨረሻ ለሕንጻው ሠራተኛና ለቆርቆሮ ወደ ሃምሳሁለት ሺህ ብር ጨረሰ ። የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ እንደተጀመረ የአቶ ጌትነት ገቢም አብሮ እያደገ መጣ ። አቶ ጌትነት እንዳጫወቱን የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንን ለማሠራት ሲነሡ በኪሳቸው የነበረው ብር አሥር ሺህ ብቻ ሲሆን በመጨረሻ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተጠናቆ ሲመረቅ ለሥራው ካወጡት ሃምሳ ሁለት ሺህ ብር በላይ ገንዘብ ትርፍ ነበራቸው ። አቶ ጌትነት በቅርብ ጊዜ (፲፱፻፹፭ ዓ ም) በራሳቸው ገንዘብና ሕዝቡን በማስተባበር ከግማሽ ሚልዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የይስማላ ደብረ ገነት ቤተ ክርስቲያንንአሠርተዋል ።

የይስማላ ደብረ ገነት ቤተ ክርስቲያንን ለማሠራት በተደረገው እንቅስቃሴ የገዳሙ አስተዳዳሪ መ/ታ ፀሐይ ገሠሠ እና የገዳሙ እቃ ቤት ኃላፊ አባ ገ/ ማርያም ምትኩ ያበረከቱትን የላቀ አስተዋጽኦ መጥቀስ የግድ ነው ።

አቶ ጌትነት ላለፉት ሃያ ዓመታት ገደማ ከተለያዩ አካባቢዎች ከሕዝብ ክርስቲያን የሚቀርብላቸውን ጥሪ በሙሉ ፈቃደኝነት በመቀበልና በራሳቸውም አነሳሽነት ይህን ያህል አብያተ ክርስቲያናት ሲሠሩ ምን ያህል ወጪ እንዳወጡ ጠይቀናቸው ነበር ። እርሳቸው ግን «አሁንም ቢሆን እናንተጋ የመጣሁት የአካባቢዬ ሕዝብ የሠራኹው ሥራ ለምን በቤተ ክርስቲያን ጋዜጣና መጽሔት አይወጣም ተግባርህ ለሌላው አርአያ መሆን አለበት ብሎ ስላስቸገረኝ እንጂ እኔይህንበመሥራቴ ሌላው እንዲያውቅልኝ ብየ አይደለም ፤ » ነበር ያሉን ። በእርግጥም አቶ ጌትነት ወርቁ ጋር ባደረግነው ውይይት የሳቸውእምነት- - -«ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ» የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ መከተል ነው ። ርሳቸው የአምላክን መንገድ ሲመከተል እንደመረጡ ሁሉ አምላክ ይከተላቸው ከማለት ሌላ ምን ማለት ይቻላል ?

«ባልና ሚስት - - - ከአንድ ወንዝ - - - » እንዲሉ የአቶ ጌትነት ወርቁ ባለቤት ወ/ሮ አጸደ ሙላትም የላቀ አስተዋጽኦ አበርክተዋል አቶ ጌትነትም በርታ እያለች የምታበረታታኝ ርስዋ ናት ሲሉ ምሥክርነታቸውን ሰጥተዋል ።

በ ጐ አ ድ ራ ጊ ው ሃ ያ ዓመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአቸፈር ወረዳ ሃያ ሁለት አንድ በዳንግላ ሌላ አንድ በአገው ምድር (ሜጫ) በአጠቃላይ ፳፬ አብያተ ክርስቲያናትን አሠሩ ይህም ከጊዜ አኳያ ሲሰላ በአማካኝ በዓመት አንድ ቤተ ክርስቲያን ሠርተዋል ማለት ነው ። አቶ ጌትነት «ለሐውልት የተከልኩት ይህ ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል (ዘፍ ፳፰ ፣ ፳፪) የሚለውን የእግዚአብሐር ቅዱስ ቃል ብቻ አይደለም የፈጸሙት « - - - - እንጨትንም አምጡ ቤቱንም ሥሩ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል ። (ሐጌ ፩ ፣ ፰) የሚለውንም አምላካዊ ቃል በተግባር ተረጉመውት እንጂ ፤ »

ታድያ ለእኝህ ሰው መሪጌታዎች ቢቀኙላቸው መዘምራኑ ቢዘምሩላቸውእረኞች ቢዘፍኑ ላቸውምን ያስደንቃል ? አቶ ጌትነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሥራ ምክንያት ወደ ባሕር ዳርና አዲስ አበባመምጣቱንቢያዘወትሩም አቸፈርን ግን አልረሱዋትም ። ቢሆንም አቸፈሮች ዘወትር ከአጠገባቸው እንዲለዩዋቸው የሚፈልጉ አይመስሉም ። ለዚህም ይመስላል የአቸፈር ሰው ፣

- - - እንደበሬ ታራሹ ታላቢ እንደላም
የትእግሥት ባለቤት ጸባየ ገራም
ፈረስማ ሞቷል ያጋሰሲቱ ልጅ
አቸፈር ሰው በቅሎ መሄዱ ከፋ እንጅ ።

ብሎ የገጠመላቸው ፣ የአቸፈር ሕዝብ ለአቶ ጌትነት ያለውን ፍቅር ባለፈው አስከፊው ሥርዓት ወቅት በተግባር አሳይቷል ። የነበረው ሥርዓት ለዘመቻና ለጦርነት ካልሆነ በስተቀር ሕዝቡ ገንዘቡን አውጥቶ ጉልበቱን አስተባብሮ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አይፈቅድም ነበር ። በዚህም የተነሣ በወቅቱ የነበሩ የደርግ ባለሥልጣኖች አቶ ጌትነትን በምሥጢርና በድብቅ እያስጠሩ ቤተ ክርስቲያን መሥራታቸውን እንዲተው ያስጠነቅቁአቸው ነበር ። እሳቸው ግን እንዲራሳቸውን ለአምላክ አስገዝተዋልና የእግዚአብሔርን ቤት ከመሥራት የሚከለክለኝ የለም አሉ ።

በዚህ ጊዜ ነበር መላው የአቸፈር ሕዝብ «ጌትነትን መንካት እኛን መንካት ማለት ነው ፣ በጌትነትና በዓይን ቀልድ የለም» ብሎ በኅብረት ሆኖ ከጎናቸው የተሰለፈው ። ድርቢያብር አንበሳ ያሥር ሆነና ሕዝቡና አቶ ጌትነት ጣትና ቀለበት ሆነውሃያ አራት አብያተ ክርስቲያናትን አድሰውና አንጸውለፍጻሜ አደረሱ ።





www.ethiopianorthodox.org

አቶ ጌትነት ቤተ ክርስቲያን በመሥራትና በማሠራት ብቻ አላበቁም ። ባሰሩዋቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥም ሆነ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ንዋየ ቅድሳት ከብልሽትና ከስርቆት ተጠብቀው ለትውልድ የሚተላለፉበት መንገድም ቀይሰዋል ። ለዚህ አገልግሉት ይሆን ዘንድም ቁመቱ ፩·፴ ስፋት ፹ ሳ·ሜ የሆነ የብረት ካዝና (ቁምሳጥን) እየሠሩ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ በመስጠት ላይ ይገኛሉ ። እያንዳንዱ የብረት ሳጥን እስከ ፲፯ ሺህ ብር የሚፈጅ ሲሆን እስከ አሁን ለቅድስት ማርያም (አብቾከለ ማርያም) ለንፋስ ጊዮርጊስ) ለቢኮላ አባይ (አቡነ ዘርአ ብሩክ) አሠርተው የሰጡ ሲሆን አሁን ደግሞ ለኪዳነ ምሕረት በማሠራት ላይ ናቸው ። ለቀሪዎቹም ቢሆን ለእያንዳንዱ አንዳንድ የብረት ቁም ሳጥን አሠርተው ለመስጠት ዕቅድ አላቸው ። እስከዛው ንዋየ ቅድሳት እንዳይጠፉ ሕዝቡ በየተራ እየወጣ እንዲጠብቅ በማድረግ ላይ ናቸው ።

አቶ ጌትነት ወርቁ ላለፉት ዓመታት ለቤተ ክርስቲያን ላበረከቱት የተቀደሰ ተግባርና አገልግሉት ከምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ጀምሮ እስከ ታች በተዋረድ ባሉት የቤተ ክህነት አመራር አባላት የተለያዩ የምስጋና ደብዳቤና ምስክር ወረቀት ተሰጥቶአቸዋል ። አቶ ጌትነት ለእነዚህ ሁሉ ታላቅ ክበሬታ አላቸው ከሁሉ በላይ ግን አቶ ጌትነት «እኔ ይህን ሁሉ የሠራሁትና ወደፊትም በእግዚአብሔር ፈቃድ የምሠራው ይህን አደረገ ለመባል ፈልጌ አይደለም ዋና ዓላማየ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለማክበር ነው ከዚህም ሌላ ገንዘብ ቀሪ እንጂ ወደ ዘለዓለማዊ ቤታችን አብሮን የማይሄድ በመሆኑ ከወዲሁ ባለን ሀብት የታረዙትን በማልበስ ፥ የተራቡትን በማጉረስ እንደዚሁም የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባቸው አብያተ ክርስቲናት በማደስና በመሥራት የገንዘብ አቅማችን ደካማ ቢሆን እንኳን ሕዝቡን በማስተባበር ሁላችንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ከጌታችን የተሰጠንን አደራ መወጣት አለብን»ባይ ናቸው ።

አቶ ጌትነት የወደፊት ዓላማቸውም ብሩህ ነው ። ገና ምን ሠራሁና ነው የሚሉት በእርግጥም በቅርቡ ማለትም መጋቢት ፲ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም በጠቅላይ ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አዳራሽ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ሰብሳቢነት በምሥራቅና ምዕራብ ጎጃም ያሉትን ገዳማትና አድባራት ለማነጽና ለማደስ በተደረገው ስብሰባ ተገኝተው ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር ከ፺ሺህ—፻ሺህ ብር ለመለገስ ቃል መግባታቸው ራሳቸውን ምን ያህል ለመንፈሳዊ ተግባር እንዳሰለፉ የሚያሳይ ጉልህ ማስረጃ ይመስለኛል ። በዚህ አጋጣሚ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የሚገኙ ባለሀብቶች ሀብት የእግዚአብሔር መሆኑን ተረድተው የአቶ ጌትነትን አርአያነት እንዲከተሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን ።

በመጨረሻም መተባበር ፥ መፈቃቀር ፥ መረዳዳት ኃይል መሆኑን በተግባር ላሳየው የአቸፈርና የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ያለንን አድናቆት ለመግለጽ እንወዳለን ።

# የትግራይ ሀ. ስብከትና ልማቱ

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የትግራይ ክልል ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ከኼዱበት ጊዜ ጀምሮ በሀገረ ስብከቱ ከፍተኛ የሆነ የልማት እንቅስቃሴ በመካኼድ ላይ እንደሚገኝ የስምሪት ፳፱ ሰ-መ-ጉባኤ ልኡካን አረጋገጡ ።

በመንበረ ፓትርያርኩ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከየካቲት ፳፱ እስከ የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በመላ ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከቶች እንዲካኼድ በነደፈው መርሐ ግብር መሠረት ልኡካኑ በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማና አካባቢዋ እየተዘዋወሩ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና በሀገረ ስብከቱ ባለሥልጣናት የተከናወነውን የልማት ሥራ በዝርዝር አቅርበዋል ።

ልኡካኑ ሲሚናሩ በተከፈተበት ወቅት በሀገረ ስብከቱ ሥራ አሥኪያጅ በመምህር ኃይለ ሥላሴ ዘማርያም የተነበበው ሪፖርት የቤተ ክርስቲያን ብዛት ፱፻ የመምህራን ብዛት ፩ሺ፮፻፳፭ የካህናት ብዛት ፳፭ሺ፭፻ ጠቅላላ የምእመናንና የካህናት ድምር ፫ሚሊዮን ፫፻፹፭ሺ፭፻ መሆኑን ከገለጹ በኋላ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ



ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጉባኤውን በጸሎት ሲከፍቱ



ጳጳስ ሆነው ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በመላ ሀገረ ስብከቱ ሌት ተቀን ያለዕረፍት በመጎብኘት በማስተማር ፥ ክህነት በመስጠት ሰበካ ጉባኤውም እንዲጠናከር መመሪያና ትእዛዝ በማስተላለፍ ፥ የልማት ተግባራትም በተገቢ ሁኔታ እንዲራመድ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚገልጽ መሆኑን ልኡካኑ በስፋት ገልጸዋል ።

ልኡካኑ በሪፖርታቸው እንዳብራሩት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በየወረዳውና በየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት በመዘዋወር ከመቀሌ እስከ ምዕራባዊው ደቡብና ወልቃይት ጸገዴ ከአላማጣ ሁመራ ድረስ የመኪናውን በመኪና የእግሩን በእግር እየሄዱ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሰበካ ጉባኤን ፥ ስብከተ ወንጌልንና ሰንበት ት/ቤቶችን እንዳጠናከሩ ፥ ልማት እንዲስፋፋ ቅርሶች በአግባቡ እንዲጠበቁ እንዳደረጉ ፥ በአጠቃሊይ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ሰፋ ያለ አባታዊ መመሪያና ትምህርት በሁሉም ቦታ ሲሰጡ መቆየታቸው ከሥራ አስኪያጁ ሪፖርት የተገኘውን በሪፖርታቸው ጠቅሰዋል ።

በሀገረ ስብከቱ ርእሰ ከተማ ስላለው የልማት ሁኔታ በዝርዝር ሲታይ ፩ኛ በመንበረ ጵጵስናውና በሀገረ ስብከቱ ጽ ቤት ግቢ ከ፴፤ በላይ የሆኑ ለእንግዳ ማረፊያና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ልዩ ልዩ ክፍል ያላቸው ተሠርተዋል ብለዋል ልኡካኑ ።

፪ኛ/ ከመቀሌ ከተማ በስተ ሰሜን በኩል በኢላላ ገረብ (ወንዝ) አጠገብ ፯·፫ ሔክታር መሬት ከመንግሥት በመጠየቅና በማግኘት የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች በማቋቋሚያም ማለትም

፩ኛ/ የቡሎኬት ማምረቻ ፪ኛ/ የከብት ርባታ ፥ ፫ኛ/ የጓሮ አትክልት ማለትም ቀይ ሥር ጥቅል ጎመን ቲማቲም ፥ የከብት መኖ የሚሆን ዛፍ የወንዙን ውኃ በሞተር በመሳብ የተተከለበትና የለማበት ሰፊ እርሻ እንደሚገኝ በመተንተን አስረድተዋል ።

እንዲሁም ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የልማት ዓይነቶች እኛ ልኡካኑ በሰሚናሩ ፍጻሜ ላይ ተዘዋውረን ጎብኝተናል አይተናል ። ትክክለኛነቱን አረጋግጠናል ሲሉ ልኡካኑ አትተዋል ። በተጨማሪም ልኡካኑ ሲያብራሩ ፫ኛ/ በዚህ ዓመት ለተለያዩ ገዳማትና አድባራት የወፍጮ መኪና መስጠታቸው



የስምሪት ፳፱ ልኡካን በጉባኡው ላይ እንዳሉ

፬ኛ/ በሽሬ እንዳ ሥላሴ ከተማ የዘይት መጭመቂያ መቋቋሙ ፤

፭ኛ/ በመኸሆ ወረዳ ኩሬ በመሥራት ፲ የችግኝ ጣቢያ መቋቋሙ ፥

፮ኛ/ ከክልሉ መስተዳድር ፕሬዝዳንትና ባለሥልጣናት ጋር በመነጋገር በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በደርግ ተወስዶ የነበረውን የከሣቴ ብርሃን ሰላማ መንፈሳዊ ት/ቤትን አስመልሰው ባሁኑ ጊዜ መምህራንን በመመደብ በ፩ኛና መለስተኛ ፪ኛ ደረጃ ፬፻፷ የሚሆኑ ተማሪዎች ገንዘብ እየከፈሉ በመማር ላይ መሆናቸውን ፥

፯ኛ/ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የገንዘብ አስተዋጽኦ የተጀመረ መሆኑ በሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በመምርህ ኃ/ሥላሴ ዘማርያም ሪፖርት ተተንትኖ መነገሩን ልዑካኑ ካቀረቡት ሪፖርት መረዳት ተችሉአል ። ልሉካኑ ወደ ሰሚናሩ ዓላማ በመመለስ ሲያብራሩ በሰሚናሩ ላይ ስለ ፲፱፻፹፮ ዓ/ም የሰበካ ጉባኤ የሥራ አፈጻጸም በሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ ሰፊ ትምህርትና መመሪያ መስጠቱ ፥ ከዚያም ስለምእመናን አመዘጋገብና የቅጽ አምላል በሊ.ቀ ትጉሃን ዓለምሰገድ በየነ ሰፋ ያለ ትምህርትና ማብራሪያ እንደተነገረ ገልጸዋል ።



መምህር ኃ/ ሥላሴ ዘማርያም የሀ/ ሥራ አስኪያጁ ሪፖርት ሲያሰሙ

ጸዋል ። ሦስቱም ቀናት ስለሰሚናሩ ዓላማ ጥናታዊ ትምህርትና ውይይት በብፁዕነታቸው በልኡካኑና በሀገረ ስብከቱ ባለሥልጣናት በቅደም ተከተል መሰጠቱን ሪፖርቱ ጠቁሞ በጉባኤው መካከል ስለርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን እድሳት በሀገረ ስብከቱ በኩል ሊሰበሰብ የሚገባውን ገንዘብ ለመወሰን ጉዳዩ በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ተነሥቶ ሰፋ ያለ ቅስቀሳና መመሪያ ተሰጥቶ ውሳኔም ተላልፎአል በማለት ልኡካኑ አስረድተዋል ። በዚሁ መሠረት ለአርአያነትና ለቅስቀሳ በልኡካኑ አስተዋጽኦ ከተጀመረ በኋላ ከብፁዕ ሊቀ ጳጳሱ አንሥቶ መላው የሰማናሩ ተሳታፊዎች በጉባኤው ላይ ገን

ተከታዩን በገጽ ፳፯ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# «ገዳማዊ ሕይወት»


# «የምስካየ ኅዙናን ገዳም»

ከሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም

ካሁን ቀደም ስለገዳማት ታሪክ ከየሀገረ ስብ ከቱ ባገኘነው መረጃ መሠረት በተከታታይ መጻፋ ችን ይታወሳል ። ዛሬ ደግሞ በአዲስ አበባ ስለሚ ገኘው የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ታሪክ ከብዙ በጥቂቱ ፤ ከረዥሙ ባጭሩ ከዚህ እንደሚከ ተለው እንገልጻለን ። «ምስካየ» እመስከየ ተጠጋ አስጠጋ ብሎ ይተነትነዋል ።

ስለዚህም ምስካየ ኅዙናን ማለት ያዘኑ ፥የተ ከዙ ፥ የተጨነቁ ፥ የተቸገሩ ሁሉ መማጸኛ መጠ ጊያ መሸሻ ማለት ነው ። በመሆኑም ይህ ታቦት በዚህ ስም እንዲጠራ የተፈለገበት ምክንያት አለው።

ይህ ታቦተ መድኃኔ ዓለም ከ፲፱፻፳፰ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ድረስ ሀገራችን ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ወረራ ኃይል በተያዘች ጊዜ በስደትና በሀገር ውስ ጥም በዱር በገደል ፥ በጫካ በበረሀ ሆነው ለነጻ ነታቸው ሲታገሉ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ኃይ ልና ጽናት ፥ ረድኤትና ብርታት በመስጠቱ የድ ልና የነጻነት አርማም በጀግንነት በማነናጸፉ በቤተ መንግሥቱና በሕዝቡ ዘንድ ከመወደዱ ሌላ የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንም ባለ ውለታ አድርጓታል ።




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በምስካየ ኅዙናን የት/ቤቱን የመሠረት ድንጋይ ሲያኖሩ

ይኸውም ይህ ታቦተ መድኃኔ ዓለም ከኢትዮ ጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ኼዶ ከ፲፰፻፲፩ እስከ ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ድረስ በዴር ሡልጣን ገዳም ቆይቶአል ። ከዚ ያም ወደ እንግሊዝ አገር ኼዶ በዚያ ለነበሩና በስ ደት ለኼዱ ለአጼ ኃይለ ሥላሴና ለንጉሣውያን ቤተሰቦች እንዲሁም ሌሎች ኢትዮጵያውያን የአ ምልኮት ሥርዓትና የቅዳሴ ፥ በአጠቃላይ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲፈጸምለት ቆይቶአል ። ከነጻነት በኋላ ማለትም በ፲፱፻፴፭ ዓ.ም ወደ ኢትዮ ጵያ ተመልሶአል ። ስለዚህ ይህ ታቦት ከሀገራቸው ወጥተው በሌላ አገር ተሰደው ለነበሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ መሸሻና መጠጊያ ሆኖ ከመቆየቱም በላይ የሕዝቡን ጸሎት ፥ መሥዋዕትና ልመና በቅድመ እግዚአብሔር ቀርቦ መልሱ በነጻነት መጎናጸፍ ብለተረጋገጠ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ተባለ።

ስለሆነም ይህ ታቦት ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም ብለው ስድስት ኪሎ በሚገኘው ቀዳማዊ ኃ ሥላሴ ሆስፒታል እየተባለ ሲጠራ በቆየው ውስጥ ቤተ ሳይዳ የሚባል መቃረቢያ አሠርተውለት ስለ ነበረ ከእንግሊዝ በመጣ ጊዜ እዚሁ ውስጥ እንደገባ ይነገራል ። በዚያም ለሕሙማኑ ፥ ፈውስ ምሕረት ሆኖአቸው እንደቆየ ይተረካል ። ታቦቱ ፥ ከስሚ ንቱ የተነሣ ሕዝቡ ከዱሮ አእሮፕላን ማረፊያ እና ከቦሌ ከአቃቂ ሳይቀር እየመጡ እዚሁ እንደሚያ ስቀድሱና እንደሚጸልዩ ተረጋግጦአል ።

በክቡር አባ ሐና ጅማ አማካይነት ይህ አሁን ያለው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ታቦተ ሕጉ የገባበት ሃምሳኛ ዓመቱን ወይም የወርቅ ኢዮቤልዩን አክብሮአል ። ታቦቱ አሁን ያለበት ሥፍራ ለማያ ውቁ በከፍላተ ሀገራትና በውጭ አገር ላሉ ኢትዮጵ ያውያን ወገኖቻችን ከሸርሚዳ አሜሪካን ኤምባሲ ዝቅ ፥ ከስድስት ኪሎ ከፍ ብሎ በድሮ ተፈሪ መኮ ንን ት/ቤት አሁን እንጦጦ አጠቃላይ ፖሊቴክኒክ ት/ቤት ጎን የሚገኝ መሆኑን ስንገልጽ በደስታ ነው ።

ይህ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ቦታ እንዲተከል ያስፈለገበት ምክንያት የዚሁ ት/ቤት ተማሪዎች በዕረፍት ሰዓታቸው ከአዳሪ ት/ቤታቸው ወጥተው በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው እንዲጸልዩ ፥ ቅዱስ መጽሐፍም እንዲማሩና እንዲያጠኑ ፥ በአጠ ቃላይ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲያጎለብቱ እዚ ሁ ቅዱስ ሥፍራ በወቅቱ እየተገኙ እምነታቸውን እንዲያጠነክሩ ታስቦ የተደረገ መሆኑን ጉዳዩን የሚያውቁት አባቶች ይናገራሉ ።



ብፁዕ አቡነ ማትያስ ከገዳሙ አስተዳዳሪ ጋር የት/ቤቱን ተጨማሪ የሥራ ሂደት ሲከታተሉ

በእርግጥም በዚሁ ት/ቤት ዘመናዊ ትምህርት ሲማሩ የነበሩና በዚሁ ቤተ ክርስቲያን እየተገኙ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ሲያዳብሩ የቆዩትን ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ከዚሁ ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ተለይተው አያውቁም ። ለገዳሙ ሕልውናና ልዕልናም ምኞ ታቸውና ጸሎታቸው ጥልቅ ነው ።

በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ «ተምሮ ማስተማር» የኖረውና የሚኖረው የወጣቶች ሰንበት ት/ቤትም በነዚያ ወጣት ተማሪዎች አማካይነት የተቋቋመ የተቀደሰ ሰ/ት/ቤት አለ ። ይህን ሰ/ት/ቤት ካቋቋ ሙት መካከልም አንዳንዶቹ ለእድገቱና ለመቃናቱ ጥበቃ ያመቻቸው ዘንድ ከአጠገቡ አይለዩም ።

የተምሮ ማስተማር በአንጋፋነቱ የታወቀ ፥ በሃይማኖቱ ጥራትና ጽናትም የታመነና በፈተና የማይበገር ፥ ለሌሉች በሞዴልነት ተመዝግቦ የታ ሪክ ምዕራፍ ያስከፈተ ፥ ተከታይና መሳይ የሌለው በቀላሉ እንደሚደለሉ አንዳንድ ደካሞች ፥ወጣቶች በብልጭልጭ የማይማረክ ፥ ከአባቶቹ እምነት የማ ይናወጥና የማይወጣ በጽኑ ዓለት ላይ የተመሠረተ ነው ። ስለሆነም ይህ የተምሮ ማስተማር ሰ/ት/ቤት ገዳሙን ባለታሪክ ከሚያደርጉት ዓበይት ጉዳዮች አንዱና የዚሁ ዓላማ ካላቸው የወጣቶች ሰንበት ት/ቤትም በአንጋፋነቱ የተመሠከረለት ነው ።

ገዳሙ ከታነጸበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ አበ ምኔቶች ወይም አስተዳዳሪዎች አሳልፎ አል ። ባሁኑ ጊዜ ገዳሙ ፲፭ የሚሆኑ መነኮሳት ፰ ዲያቆናት በድምሩ ፳፫ ልኡካን በትምህርት ፥ በጸ ሎትና በቅዳሴ ያገለግላሉ ። ባሁኑ ወቅት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የተቀደሰ ፈቃድ የገዳሙ የበላይ ጠባቂ ብፁዕ አቡነ ማትያስ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ የገዳሙ አስ ተዳዳሪም መምህር ተስፋ ሥላሴ ሞገስ ናቸው ። ፲ የሚያህሉ አበው መነኮሳት አገልግሎታቸውን ፈጽመው ወደማይቀሩበት ዓለም ተሸጋግረዋል ።

አሁን በብፁዕነታቸውና በቆሞሱ ዘመነ ሢ መት በገዳሙ ውስጥ ብዙ ታላላቅ ሥራዎች በመ ከናወን ላይ ናቸው ። የገዳሙ መነኮሳትና ዲያቆና ትም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለገዳሙ ግን ባታም ሌት ተቀን የሚፋጠኑ ናቸው ። ሰበካ ጉባኤውም ከአበው መነኮሳትና ዲያቆናት ጎን ተሠ ልፎ በልማት ዘርፍ ያለው ተሳትፎ እጅግ የላቀና ተወዳዳሪ የማይገኝለት የሥራ እንቅስቃሴ በማሳየት ላይ ይገኛል ።

የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለምን ገዳምዓላማና ተግባር የሥራ እንቅስቃሴና ርምጃ አይተው ለመምሰልና ለመከተል ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ለልማት ሥራ መሰለፍ አለ ባቸው ። አለቆች ማባረር ፥ ዲያቆናትን ማቀያየር የቤተ ክርስቲያን ልማት ሊሆን አይችልም ።እገሌን አስወግዱልኝ ፥ ዕገሌን ላኩልን (ይምጣልን) እያሉ በቤተ ክህነትና በአ-አበባ ሀገረ ስብከት ተኰልኵሎ ከመዋልና ሥራ ፈት ከመሆን ይልቅ ሠርቶ አም ርቶ ፤ አበርክቶ የሥራንና የድካምን ፍሬ መመገቡ ከሁሉ ይመረጣል ።



መምህር ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የገዳሙ አስተዳዳሪ

ለአብነት ያህል የምስካየ ኅዙናን መድኃኒ ዓለም ገዳም የሥራ እንቅስቃሴ ምን እንደ ሚመስል በቅርብ ያለው መጥቶ አይቶ መረዳቱ አማራጭ የሌለው ብልህነት ነው ። በውጭ ላሉት ደግሞ

www.ethiopianorthodox.org

በመምህር ተስፋ ፕላንና ዲዛይን አውጭ የተሰሩትን ከዚህ እንደሚከተለው ዝርዝር ሁኔታቸውን እንገልጻለን ። ሁሉም ይህን የተቀደሰ ተግባር አይቶ እንቦና ተረድቶ በዚህ በልማት ሥራ እንደሚንቀሳቀስም ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

በዚህም ገዳም ሁለተኛ መለስተኛ ደረጃ ዘመናዊ ት/ቤት አለ ። ሁለተኛ ደረጃ ለመከፈትም ባለ አምስት ደረጃ(ክፍል)ሕንጻ እየተሠራ ነው።ከዚህም ሌላ በገዳሙ ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ከፍያለ ነው። ይህ የሥራ ርምጃ ከፍ ሊል የቻለው ብፁዕ አቡነ ማትያስ የአ-አበባ ሀ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የዚሁ ገዳም የበላይ ጠባቂ ፣ መምህር ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የገዳሙ ዋና አስተዳዳሪ ሆነው ከመጡ ጀምሮ ነው በእርግጥ እነአባ ግርማ ጽዮን ተ/ሃይማኖት በነበሩበት ጊዜም ሥራው በማደግ ላይ ነበር ።ሆኖም ባሁኑ ጊዜ ሥራው ከመቸውም ይልቅ እጅግ ከፍተኛ ነው። ይኸውም ፩ኛ/ ተራርቀው የነበሩ ታቦተ ማርያምና ታቦተ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ጽላቶቹ ከትልቁ መንበር የተያያዘ ዘመናዊ በሆነ መልኩ የተሠራ አውቶማቲክ ብረት መንበር ተሠርቶላቸው ግራና ቀኝ ተከፍቶ በሦስት እንዲቀደስ ሆኖአል ።

፪ኛ/ በመድኃኔ ዓለም መንበረ ታቦት በጣራው ላይ ካሁን በፊት የብርሃን ችግር ስለነበረ በመስቀል ቅርጽ ተሠርቶ በዘመናዊ ፍሉ ሮሰንት ተጊጦ አገልግሎት በስመጠት ላይ ይገኛል ።



የገዳሙ ኬክ ቤት ሠራተኞች ከገዳሙ የበላይ አስተዳዳሪ ጋር

፫ኛ/ የጳውሎስ መልእክታት ማንበብያ ከአንድ ሰው በስተቀር ሁለት ሦስት የማያዝር ስለነበረ አሁን በብረትና በላሚራ ተሠርቶ ብዙ ሰው በማስተናገድ ላይ ነው ።

፬ኛ/ ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ ታላላቅ እንግዶች ወደዚህ ገዳም በሚመጡበት ጊዜ በዕቃ ቤት በቅርስነት ከተቀመጡ ወንበሮች መካከል ይወጡ ነበር ። አሁን ግን ይህን ችግር ለማቃለል በዘመናዊነታቸውና በይዞታቸው እጅግ የሚያማምሩ ሁለት ወንበሮች ተሠርተዋል ።

፭ኛ/ የቤተ ክርስቲያኑ የኤሌክትሪክ መብራት ኃይሉ ደካማ በመሆኑ አሁን ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል ሊያሟላ አይችልም ነበር።ግን በኃይሉ ለአንድ ፋብሪካ ሊሆን የማይችል የመብራት ኃይል ሲዘረጋ ፣ ይህንኑም ለመዘርጋት የቤ/ክርስቲያኑ ፕላን በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ በተጨማሪ ከታወቁ የኤሌክትሪክ ኢንጅነር ጉመዱ እንዴት እንደሚዘረጋ የሚያሳይ ፕላን ተዘጋጅቶ ሥራውን በቅርቡ ለማስጀመር ጥረት እንዳለ ተረጋግጦአል ።

፮ኛ/ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የነበረው መደገፊያ ዕንጨት በማርጀቱ በብረት ቋሚ የሆነ በላሚራ መልክ መጠለያ ተሠርቶ ምእመናን በሚያስቀድሱበት ጊዜ ቅዝቃዜ ስለፈጠረ መምህር ተስፋ ሞገስ የገዳሙ አስተዳዳሪ ከአባላት ጀምሮ የተለያዩ ምእመናን በማስተባበር ፣ ራሳቸውም አርአያ በመሆን ጣውላ የማልበሱ ተግባር እየተገባደደ ነው ።

፯ኛ/ የኬክ ቤቱን የቢሮን ፣ የመጋዘን ፣ ችግር በአንድ ፎቅ ፮ ክፍሎችን ከሁለት መጸዳጃ ቤት ጋር ቢሮ ተሠርቶአል ። በተጨማሪ ኬክ ቤቱ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የቦታ ጥበት ስለነበር ይህን ለማቃለልና እንዲሁም መጠለያው ተገልጋዩን ሕዝብ ለዓይን የሚስብ ጥንታዊ ታሪካዊ ከሆኑት የአክሱም ቤተ ክርስቲያንና ከላሊበላ ቤተ መቅደሶች አንዱ የሆነው ተሠርቶ ሥዕል ተሥሎበታል ።

፰ኛ/ ለገዳሙ፣ለት/ቤትና ለኬክ ቤቱ የውኃ በርሜል እያንዳንዱ ፳ ሺህ ሊትር የሚይዝ ቦታ በማይፈጅ ሁኔታ አሠርተዋል ።

፱ኛ/ የቅዳሴ ጸበል ዲያቆናት ከሩቅ ቦታ በባልዲ እየተሸከሙ ያመጡ ነበር ። ይህን ችግር ለማቃለል ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውኃ በቧንቧ ገብቷል ።

፲ኛ/ የት ቤቱን ሁለተኛ ደረጃ ለማስጀመር ተብሎ ከጀርመን ርዳታ ድርጅት በተገኘው ገንዘብ ከኮንትራክተሩ ጋር በተፈረመው ውል መሠረት ባለሁለት ፎቅ ሥራ ለሁለት ዓመት እንደሚፈጅ ተገምቶ የነበረውን በ፰ ወር ጊዜ ውስጥ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከታሰበው በላይ የ፩ ፎቅ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል ።



ሥርዓተ ተክሊል የሚደረግባቸው በአዲስመልክየተሠሩ አክሊላት

፲፩ኛ/ የገዳሙ ጽ/ቤት የቢሮ ጥበትን በማጠቃለል እንዲሁም የተክሊል መፈራረሚያና የማኅበሩ የምግብ አዳራሽ ከመሆኑ በፊት ከተሠራው ቢሮ በ«ረ» ቅርጽ የአስተዳዳሪውን ቢሮ የጸሐፊውን ቢሮ ውስጥ ለውስጥ ፲፪ ሜትር ርዝመት ያለው አዳራሽና ሁለት ዘመናዊ መጸዳጃ ቤት ከነሻወሩ ሥራው ተጠናቅቆ በቅርብ እንደሚጀምር ይጠበቃል ።

፲፪ኛ/ የዘበኞቹ መጠበቂያ ከዋናው በር ገዳሙንና ት/ቤቱን በአንድ ላይ ሊያስጠብቅ የሚችል ባለ ፩ ፎቅ (ማማ) በዘመናዊ መልክ ተሠርቶአል ።

፲፫ኛ/ ሥርዓተ ተክሊል በሚደርስበት ጊዜ በአክሊል እጥረት ሥርዓቱ የተጎርጎረጎረ አድርጎታል ። በማለት አገልግሎት በተፈጸመላቸው ምእመናን ቢጋዜጣ ጭምር አስተያየት በመቅረቡ ችግሩም እየጎላ በመምጣቱ ይህን ለማቃለል ፬ ጥንድ ስምንት አክሊል ከ፲፬ ካባ ጋር ተሠርቶ ችግሩ እንዲቃለል ተደርጎአል ።



የትምህርት ቤቱ የትምህርት አመራር ኮሚቴ አባላት

፲፬ኛ/ በመድኃኔ ዓለም መንበር ላይ በ «ቶ» ቅርጽ በዘመናዊነቱ በኒዮን መብራት እና «መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ» የሚል ጽሑፍ በኒዮን መብራት በሚያምር ሁኔታ ተዘጋጅቶ አገልግሎት ሲሰጥ ይገኛል ።

፲፭ኛ በቤተ ክርስቲያኑ ግራና ቀኝ እንዲሁም በድርገት መውረጃ ውስጥ ጣራ ላይ ዘመናዊ የመስቀል ቅርጽ ያላቸው መብራቶች በሚያምር ሁኔታ ተሠርቶአል ።

፲፮ኛ/ የግብር ማድቀቂያ ቦታ ከቤተ ልሔሙ ራቅ ያለ ስለነበር ለሥራ ችግር ፈጥሮ ነበር አሁን ግን ከቤተ ልሔሙ አጠገብ ተሠርቶ የግብር መስጫው ባለአንድ ተሸካሚ ክብ ቅርጽ ያለው ጠረጴዛ ሆኖ ተሠርቷል ።



ከገዳሙ የልማት ኮሚቴ አባላት በከፊል

፲፯ኛ/ ለአሥራ ሰባት ዓመት በደርግ መንግሥት ተዘግቶ የነበረው የቤተ ክርስቲያኑ ከቀድሞ አልጋ ወራሽ ግቢ ጋር የሚያገናኘው በር ተከፍቶ ለት ቤቱ ተማሪዎችና ቤ/ክርስቲያኑን ለመሳለም ለሚመጡ ምእመናን መውጫና መግቢያ ጭምር ሆኖ እያገለገለ ነው ።

፲፰ኛ/ ወደ ዕቃ ቤቱ መግቢያ ትልቁ በር አልፎ ማንም ሰተት ብሎ እንዳይገባ ታስቦ ጠንካራ የሆነ ብረት መዝጊያ ተበጅቶለት ለቅርሶች ጥበቃ አስተማማኝ አድርጎታል ።

አስተያየት ፣

የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤ ክርስቲያን ገዳም በልማት ሥራ ከየትኛውም አድባራትና ገዳማት እጅግ በላቀ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ። «ሥራ ለሠሪው» ተብሎ በአባቶች እንደተነገረውና ጠቢቡ ሰሎሞንም «ቦ ጊዜ ለኩሉ» እንዳለው ይህ ገዳም ሰፊ ቦታ ቢኖረው የሥራ እንቅስቃሴው በበለጠ ተራምዶ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን የሥራ ዕድል ሊከፍት ይችል እንደነበረ ከአያያዙ መረዳት ይቻላል ስለሆነም አሁንም ቢሆን ከቅጽረ ቤ ክርስቲያኑና ከት ቤቱ የተያያዙት ቤቶች መፍትሔ አግኝተው ት ቤቱ በተፈለገው መልኩ እንዲስፋፋ ለማድረግ እንዲቻል የሚመለከተው ሁሉ ትብብር ይፈጥር ዘንድ ሳንጠቁም አናልፍም ፤





www.ethiopianorthodox.org

# የሊቃውንት ዓምድ

## የአለቃ ሲራክ ፈቃደ ሥላሴ የሕይወት ታሪክ

ሊቁ አለቃ ሲራክ ፈቃደ ሥላሴ ከነጋድራስ ፈቃደ ሥላሴና ከወ/ሮ ትደግ ብሩ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፮ ዓ/ም በትግራይ ክ/ሀገር አድዋ መድኃኔ ዓለም ተወለዱ ።



አለቃ ሲራክ ፈቃደ ሥላሴ እነሀ ነበሩ

አባታቸው እርሳቸውን ከመውለዳቸው በፊት በኢየሩሳሌም ገዳም ዮርዳኖስ ውስጥ ሳይመነኩሱ በምናኔ ብቻ ፲፱ ዓመት ከቆዩ በኋላ ዘር ከገዳም ያወጣል»እንደሚባል ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወ/ሮ ትደግ ብሩን አግብተው ሁለት ሴትና ሊቁን አለቃ ሲራክን ወለዱ ። ከዚህ በኋላ ትዝታቸው ምናኔ ስለሆነ እንደገና ንብረታቸውን ትተው ደብረ ዓባይ ከሚባለው ገዳም ገብተው ከመነኩሱ በኋላ ልጇን እም ጡልኝ ብለው ሊቁ አለቃ ሲራክን በገዳሙ ውስጥ እንዲማሩ አድርገዋል ። ሊቁ አለቃ ሲራክም ከንባብ-ዳዊት ከፈጸሙ በኋላ ጸዋተወ ዜማ ጾመ ድጓና ምዕራፍ ዝማሬና መዋሥዕት የቅዳሴ ዜማና አቋቋም ከመሪጌታ ተድላ ተምረዋል ።

ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከአቡነ ማቴዎስ ዲቁናን ተቀብለዋል ።

ሊቁ አለቃ ሲራክ በጌምድር ወገራ ዳባት ገብርኤል ከየኔታ አበራ የቅኔን ትምህርት አጠናቀው እንደገና ሚካኤል ደብር ከጌቴገሞራ ዘንድ ገብተው ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው ለመምህርነት በቅተዋል ።

ከዚያም ደብረ ታቦር መድኃኔዓለም ሄደው መምህር ሐዲስ ተክሌ በኋላ አቡነ ዮሐንስ ከተባሉት ዘንድ የሐዲሳትን ትርጉም ተምረው አጠናቀዋል ።

መም/ሐዲስ ተክሌ ወደ አ-አ- ሲመጡ የአደራ አባታቸው በመሆናቸው ይዘዋቸው ስለመጡ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀምጠው ያስተምሩ ስለነበር አለቃ ሲራክም በተጨማሪ የፍትሐ ነገሥት ትርጉም ይማሩ ጀመር ።

ሊቁ አለቃ ሲራክ መምህራቸው አዲስ ተክሌ ኢየሩሳሌምን እንዲሳለሙ ጃንሆይ አጼ ኃ/ሥላሴ ስለፈቀዱላቸው ከመምህራቸው ጋር አብረው ኢየሩሳሌም ሄደው አርባ ቀን ያህል ተቀምጠው ተመልሸዋል ። እኚሁ መምህር ከኢየሩሳሌም መልስ የአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አልቅና ስለተሾሙ አለቃ ሲራክም ከዚያው ሄደው ጀምረውት የነበረውን የፍትሐ ነገሥት ትርጉም ተምረው አጠናቀዋል ።

አለቃ ሲራክ መምህራቸው የጋብቻን ሥርዓት እንዲፈጽሙ ቢጠይቋቸው ለብዙጊዜ መልስ ሳይሰጡአቸው ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ እንደሚመነኩሱ ቢነግሯቸው በሕግ ተወስኖ መኖር ስለመረጡ ወ ሮ ሙሉወርቅ ይትባረክን በተክሊልና በሥጋወደሙ የትዳር ጓደኛ መሥረቱ ። ከዚያም መምህራቸው እንቦበርን ለቀው አ-አ- ቀድሞ መካነ ሥላሴ አሁን በዐለወልድ ቤተ ክርስቲያን የሚባለውን ስለተሾሙ አለቃ ሲራክም እንኮበርን ለቀው ከባለቤታቸው ጋር እዚሁ አ-አ- መጥተው ከጃንሆይ ዘንድ ቀርበው ከሊቃውንቶች ጋር የሐዲሳቱን ነጠላ ትርጉም በጸሐፊነትና በተርጓሚነት ለተወሰኑ ዓመታት ሲሰሩ ቆይተዋል ።

ጠላት አገራችንን ለቆ እንደወጣ ግርማዊነታቸው በጎጃም አድርገው ደብረ ሊባኖስ በገቡ ጊዜ ቅኔና ንግግር አቅርበው ባልደረባ ተሰጥቶአቸው ፍቼ ልዑል ራስ ካሣ ቤት ድረስ ተከትለው ሄደው ብር (100) መቶ ብር ጉርሻ ተሰጥቷቸው ከዚህም ጋር አ-አ- ሄደው ሥራ እንደሚሰጣቸው ስለተነገራቸው አ- አ- መጥተው ከግርማዊነታቸው ዘንድ ቀርበው የፍርድ ሥራ ይሰጠው ሲሉ ለብላታ አየለ ገብሬ ትዕዛዝ ቢያስተላልፉላቸውም የፍርድን ሥራ ስለአልፈቀዱ ትምህርት ሚ/ር ሄደው የአስተማሪነት ሥራ በጠየቁ ጊዜ ሚኒስቴሩ አቶ መኮንን ደስታ ከነአቶ ከበደ ሚካኤል ጋር ሆነው በደስታ ተቀብለው በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በአስተማሪነት ተቀጠሩ ። ከዚያም ቀደም ሲል ባላባቶች ዛሬ መድኃኔ ዓለም ት/ቤት ጉለሌ ተዛውረው ከነሙሴ ባርቤርት እንግሊዛዊ ዲሬክተር ጋር የትምህርት ክፍል ምክትል ሆነው ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ እንደገና ወደ ተፈሪ መኩንን ትምህርት ቤት በአስተማሪነት ተዛውረው ሠርተዋል ።

ሊቁ አለቃ ሲራክ በዚሁ ትምህርት ቤት በትርፍ ጊዜአቸው እንግሊዝኛ ቋንቋ ተምረው አጠናቀዋል ።

አለቃ ሲራክ በትምህርታቸው ብቁ በመሆናቸው ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ለጃንሆይ ነግረው ከትም/ሚ/ር ሥር ወጥተው በቤተ ክህነት እንዲሰሩ ስለአስደረጓቸው ከመምህር ራስ ወርቅ ጋር ከግርማዊነታቸው ዘንድ ቀርበው ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ትም/ቤት ኃላፊ መምህር ራስ ወርቅን ዋና ሹም ሲያደርጉ አለቃ ሲራክን ምክትል ሥራ አስኪያጅና ዋና ጸሐፊ ሆነው እንዲሰሩ አስፈቅደውላቸው ለብዙ ዓመታት ሠርተዋል ።

ከዚያም ደብረ ብርሃን አዳሪ ት/ቤት ይቋቋም ሲሉ ግርማዊነታቸው ትዕዛዝ በመስጠታቸው የዚህ ሥራ ልምድ ያላቸው አለቃ ሲራክ ስለሆኑ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ አስጠርተው ደብረ ብርሃን ከተማ ላይ አዳሪ ትምህርት ቤት አቋቁመው በተጨማሪም የሁለቱን አውራጃዎች የተጉለትና ቡልጋን እንዲሁም የመንዝና ይፋት ትምህርት ቤት ሥራ አስኪያጅነትን ጨምረው እንዲሰሩ አዘዙዋቸው ። በትዕዛዙ መሠረት ደብረ ብርሃን ላይ አዳሪ ትምህርት ቤት ከፍተው ተማሪዎች እንዲማሩ የብሉይና የሐዲስ ትርጉም የቅኔ ፣ የዜማና የንባብ መምህራን ተቀጥረው እንዲያስተምሩ አድርገዋል ።

### የደብር አለቅነት ሹመት

ለመጀመሪያ የአንኮበር ማርያምን እልቅና በግርማዊነታቸው ፈቃድ ተሹመዋል ። አለቃ ሲራክ የቦታው እርቀት ለሥራቸው አስቸጋሪ መሆኑን ስለአስረዱ የጌጣት ገብረ መንፈስ ቅዱስን ቤተ ክርስቲያን እልቅና ይዘው አዳሪ ትምህርት ቤቱን እንዲያስፋፉ ተፈቀደ ። ይህ ቤተክርስቲያን በድሮ ጊዜ በገደል ውስጥ የተሰራ ስለነበር ይህንኑ ችግር ለሕዝቡ በመግለጽና የሕዝቡም ድጋፍ ስለተጨመረበት ቤተ ክርስቲያኑን ለሕዝቡ አማካይ ከሆነ ቦታ አውጥተው ስለአሠሩት ክርስቲያኑ ሕዝብ ሲገለገልበት ይገኛል ።

አለቃ ሲራክ እንደገና ትተውት የነበረውን ሥራቸውን ለመቀጠል በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት በመምህርነት ተቀጥረው ለ፲፰ ዓመታት ሲያገለግሉ ቆይተው በጡረታ ተገልለዋል ።

### ከጡረታ በኋላ የሠሯቸው ተግባራት ።

ሀ/ ድርሣነ ኡራኤል መጽሐፍ በግዕዝ ብቻ በመሆኑ ሁኔታው ስለአሳዘናቸው ከብዙ ጊዜ ድካም በኋላ ግዕዙን ወደ አማርኛ በ፲፫ ከፍለው ምዕራፍና ቁጥር ገጽ እያወጡ ለሁለት አመታት ያህል ሰርተው ማተሚያ ቤት ገብቶ ከታተመ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡ ታሪኩን እያነበበ ምሥጢሩን እየተረዳ ሲገለገልበት ይገኛል ።

ለ/ ድርሣነ ሩፋኤልም እንደዚሁ በግዕዝ ብቻ ተጽፎ ስለቆየ ንባቡን ከነትርጉሙ ጽፈውት ስለነበር በአሁኑ ጊዜ እንዲታተም ተዘጋጅቶ ይገኛል ።

ሐ/ የተለያዩ ፩፫/ሃያ ሦስት/ የጸሎት መጻሕፍት ጽፈውና አዘጋጅተው በማቅረባቸው ታትሞ ሕዝቡ እየጸለየባቸው ይገኛሉ ።

ሊቁ አለቃ ሲራክ ይህንን ሁሉ አገልግሎት በተለያዩ ቦታዎች ሲያካሂዱ በሕግ ጋብቻ መወሰናቸው ለሥራ ችግር አልፈጠረባቸውም ። አለቃ ሲራክ ፩ኛ/ ወ.ሮ ጽጌረዳ ሲራክ ፣ ፪ኛ/ ወ.ሮ የትምወርቅ ሲራክ ፣ ፫ኛ አቶ ኃይለመለኮት ሲራክ ፣ ፬ኛ/ ወ.ት ፀሐይ ሲራክ ፭ኛ/ አቶ ኤልያስ ሲራክን እንደ ወለዱ ባለቤታቸው በሞት ስለተለያቸው እነዚሁኑ ልጆች በምግባርና በሃይማኖት ኮትኩተው በትምህርት አንጸው በማሳደጋቸው ሁሉም ትምህርታቸውን ጨረሰው አገራቸውንና ራሳቸውን በሥራ እየረዱ እንዲኖሩ ከማድረጋቸውም ሌላ ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋወደሙ እንዲፈጽሙ አብቅተዋቸዋል ። አለቃ ሲራክም ባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለይዋቸው በኋላ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሄደው የምንኩስናውን ሥርዓት ፈጽመዋል ።

ሊቁ አለቃ ሲራክ ፈቃደ ሥላሴ መላዘመናቸውን በሥራና በበጎ ምግባር ፈጽመው ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ ዘመድ ወዳጅ በተገኙበት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል ።

ከልጆቻቸው

## የትግራይ ሀ. ስብከትና ልማቱ

ከገጽ 21 የዞረ

ዘብ እንዲያዋጣ ተደርጎአል ካሉ በኋላ የተዋጣውም ገንዘብ ብር ፯፻፸፫ (ሰባት መቶ ሰባ ሦስት ብር) መሆኑንም ገልጸዋል ።

በሦስቱ የሰሚናር ቀናት የተካሄደው ጉባኤ በመርሐ ግብሩ መሠረት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ጸሎተ ቡራኬና ትምህርተ ወንጌል መሆኑንና ስማናሩም ሰላምና ጸጥታ ባለው መንፈስ እየተካ ሔደ ለፍጻሜ መድረሱንም ልኡካኑ በአንክሮ ገልጸዋል በጉባኤው ላይ የተሰጠው ትምህርትና መመሪያ ግልጽና እርኪ ስለነበረ በጉባኤው ተሳታፊዎች ዘንድ ተቀባይነትና ምስጋና አግኝተዋል ሁሉንም ለመፈጸምና ለማስፈጸም በአንድ ድምፅ ሁሉም ቃል ገብቶአል በማለት ልኡካኑ ሪፖርታቸውን ደምድመዋል ።





www.ethiopianorthodox.org

# ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ

ይህ ርእስ የጠበቀ አኖጅ ያለበትና የክርስቲያኖች ሕይወታዊ መልእክት እንደሆነ ከቃሉ ሐረግ መረዳት ይቻላል ።

ይሁንና ወደ መሠረታዊ ትምህርቱ ከመግባታችን በፊት ዝግጅት ስለሚለው ኃይለ ቃል በመጠኑ ለመግለጽ እንወዳለን ለመማርም ለማስተማርም ለመብላትም ለመጠጣትም እንግዳን ለመቀበል ለመሸኘትም ይህን የመሰለ ሁሉ ያለ ዝግጅት አይፈፀምም ሆኖም የዚህ ዓለም ዝግጅት ዓይነቱ በየመልኩ ቢታይና ቢነገርም ጊዜያዊ እንጂ ዘለዓለማዊ ባለመሆኑ ብዙ ዘመን አያረካም ምክንያቱም አዘጋጅውና ተዘጋጅው ኃላፍያን ሲሆኑ ከርእሱ እንደተረዳነው ሁሉ በሚያልፈው ዓለም የማያልፍ ዝግጅት ሊኖረን ይገባል ።

ስለዚህ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በመወለዱ በሠላሳ ሦስት ዓመት ከሶስት ወር በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ የሰውን ልጆች ሁሉ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከግዞት ወደ ነፃነት ከኃጢአት ወደ ሥርየት እንዲሸጋገሩ ወንጌልን ሲያስተምር ከተናገራቸው ብዙ መመሪያዎች አንዱ "ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ" የሚለው አምላካዊ ቃል እንደሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት መረዳት ይቻለል ይኸውም የምናዘጋጀውም ምን እንደሆነ የምንዘጋጀውም ለምን እንደሆነ ከማንም ሳይሆን ከራሱ ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ለመሆኑ ከአባቶቻችን ከሐዋርያትና ከሊቃውንት የተረዳን መሆናችን እሙን ሲሆን ልቡናችንን ከክህደት ከቂም በቀል ሰውን ለመጉዳት መጥፎ ሀሣብ ከማመንጨት ፤ ሕሊናችንንም በሐሠት ከመፍረድና ከመመስከር ወንድሙን ከመጥላት ተጠብቀን ለፍቅር ለትሕትና ፤ ለጽድቅ ፤ ለሰላም ለትዕግሥት ለጸሎት ፤ ለምስዋት ማለትም ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ለእግዚአብሔር መልሶ በመስጠት ፤ ለርህራሔ ፤ ለሚዛናዊ ፍትሕ በንስሐ መዘጋጀት ክርስቲያናዊ ግዴታ መሆኑን ማጤን አለብን ። በይበልጥም የርእሱን ኃይለ ቃል ለመረዳት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ተቀምጦ ሳለ ሐዋርያት ቀርበው ዳግመኛ የመምጣትህ ምልክቱ ምንድን ነው? ብለው ሲጠየቁት የተነገረውን ቃል ተቀብሎ ተዘጋጅቶ ለጠበቀ ዋጋ ለመክፈል ሲሆን በቃሉ ሳላመነ በሕጉ ሳልጸና ተዘጋጅቶ ሳልጠበቀ ፍዳ ለመክፈል እንደሆነ በየጊዜው ከምናነባቸውና ከምንሰማቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ቻል ሳንል በብሩህ ህሊና ቃሉንከምሰጢሩ ጋር ብናገናዝበው እንዲህ ሲል ያስረዳናል ።ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁ የበራ ይሁን እናንተም በመጣና በር በመታ ጊዜ ወዲያው ይከፍቱለት ዘንድ ከሠርግ እስኪመለስ ጌታቸውን እንደሚጠብቁ ሰዎች ሁኑ ጌታቸው መጥቶ ተግተው እንዲህ ሲያደርጉ የሚያገኛቸው አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው ነገር ግን ይህን እወቁ ባለቤት ሌባ የሚመጣበትን ጊዜ ቢያውቅ ተግቶ በጠበቀ ቤቱንም እንዲቆፍሩት ባልፈቀደም ነበር እናንተም ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ ባልጠረጠራችሁበት ሰዓት ይመጣልና ሉቃ ፣ ፲፪ ፣ ፴፭-፵ ለመባል የሚያበቃን ይህ ብቻ አይደለም ባለቤት መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና ማታም እንደሆነ፣በመንፈቀ ሌሊትም እንደሆነ ዶሮ ሲጮህም እንደሆነ ጥዋትም እንደሆነ ድንገት እንዳይመጣባችሁ ተኝታችሁም እንዳያገኛችሁ ። ሲል የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተላለፍልንን አምላካዊ ትዕዛዝ ነቅተንና ተግተን ባልጠረጠርነው ሰዓትና ባልቀጠርነው እለት እድሜ እጥራችንን ጥሶ ሕይወት ግባችንንአፍርሶ ከጌታችን እንዳንለይ እንድንጠነቀቅ ሁላችንንም ያስገነዝበናል ።

ያም ሆነ ይህ አንብበንና ሰምተን በቃሉ ለመጠቀም እንጂ በምንሰማው ወሬ በምናየው ድርጊት መደንገጥና መፍራት የለብንም በማይቀር ነገር ከመደንገጥና ከመፍራት የተነሣ ሥራ ፈቶች እንዳንሆን ያስፈልጋል ።

ምክንያቱም አስቀድሞ ቃሉ የተነገረን ከኃጢአት ርቀን ንጽህናን ጠብቀን ከሀሰት ይልቅ እውነትን መርጠን ብንሳሳትም በንስሐ ታድሰን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አመጣጥ በደስታ ብንጠባበቅ የአባቴ ቡሩካኖች ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያት ትወርሱ ዘንድ ወደኔ ኑ የሚለን መሆኑን ተዘጋጅተን ለመጠበቅ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ።

ሊቀ ጠበብት ያሬድ ሞላ

# ታማኝ አገልጋይ

እግዚአብሔር ለሰው ልጆችና ለቤተ ክርስቲያን የነበረውን መልእክት ወዶና መርጦ በሰዎች በኩል ማስተላለፉ ግልጽ ነው መልእክቱን የሚያስተላልፉት ሰዎች የራሱ ጥሪና በረከት ስለነበራቸው ታማኝ አገልጋይ ለመሆን በቁ በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ አገልጋዩ አገልግሎትን ከሙያ አንፃር ብቻ የሚመለከትና እንደ ዓላማዊ ጥበብና እውቀት የሚመካበት ከሆነ ታማኝነትን ያጣል ።

ስለዚህም ነው አንድ ሊቅ " አገልግሎት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ታማኝነትም ነው" ያለው ይህ ዓይነቱ ጥሪና አገልግሎት የከበረ ነው ። ለአገልግሎት ስንጠራ የተጠራነው ለልጅነት ነውና እንደልጆቹ ከናርን ደግሞ የመታዘዝን ጠባይ እና ሳያለን ይህም ሲሆን ለልጅነት የጠራን አምላክ ታማኝ አድርጎ ስለሚቆጥረን የሥራን ወይም የአገልግሎት ድርሻ ያሰጠናል ትኩረቱ ደግሞ ከስጦታው ወይም ከአገልግሎቱ ላይ ሳይሆን የእኛ ታማኝ ሆኖ ማገልገሉ ነው ። አገልግሎት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ታማኝነትም ነው እንደ እውነቱ ከሆነ በአሁኑ ጊዜያችን ይህ ጥቅስ በየአገልግሎት ስፍራችንና የስራ መስክ ሁሉ በትልልቅ ፊደሎች ተጽፎ ሊነበብ የሚገባው ነው ።

ታማኝነት ደግሞ የአፍአዊ ነገር ሳይሆን የልብ ጉዳይ ነው ። እንዲህ የእግዚአብሔር ጉዳይ ከልባችን ጋርነ ው የሕይወት መውጫ ከልባችን ነውና አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ" የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና ይላል ። (ምሳሌ ፣ ፬ ፣ ፳፫) ።

በአገልግሎት ውስጥ ታማኝነት አስፈላጊ ከሆነ ታማኝ ለመሆን ደግሞ አደራውን የሰጠን ማን እንደ ሆነና አደራውም ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው ። በማቴዎስ ወንጌል ም ፣ ፳፭-፲፬ - ፴ አደራውን ከተቀበሉት ሦስት አገልጋዮች መካከል የምንማረው ታሪክ በታማኝነት ተግቶ የሠራ እጥፍ ድርብ በረከት እንደሚያገኝ እንማራለን ለማስረጃም ያህል ገብርኄርን ታማኝ ያሰኘው ሁለቱን አራት አምስቱን አሥር አድርጎ ለጌታው በማስረከቡ ነው ። የተቀበሉትን አደራ በታማኝነት የማይወጡና አደራውን የማይጠብቁ ግን እናንተ ሰነፎች ተብለው እንደሚፈረድባቸውና ወቀሳ እንደሚደርስባቸው ተጽፎአል እኛም ትጉሆች እንጂ ሰነፎች ተብለን እንዳንነቀፍና እንዳይፈረድብን በታማኝነት ተግተንና ነቅተን ማገልገል ይገባናል ።

እግዚአብሔርን በሕይወት ሳለን በተግባርና በቃል ማገልገል ትልቅ ክብር ነው ማንኛውም ዓይነት አገልግሎት የሚሰጠው የአገልጋዩን ታላቅነት ለማሳየት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለመግለጽ ነው ከዚህም ጋር አገልጋዩ ሕይወቱን ከልዩ ልዩ ወጥመድ ከሆኑ ፈተናዎች መጠበቅ ይገባዋል የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል ስለምናገለግለው ስለዚህ ሊጋስ ስጦታ ማንም እንዳይነቅፈን በጌታ ፊት ብቻ ሳይሆን በሰው ፊትም ቢሆን መልካም የሆነውን እናስባለንና ይላል ። ፪ኛ ቆሮ ፰ - ፳ - ፳፩) ።

የቀደምት ሰዎችን ታሪክ ከቅዱሳት መጻሕፍት በምንመረምርበት ጊዜና አሁንም እንኳ አልፎ አልፎ እንደሚታየው እግዚአብሔር በአገልግሎት ደረጃ ስለአስቀመጣቸው አገልጋዮች ታላቅ ወጥመድ የሆኑ ብዙ ነገሮች እንደ አሉ እንገነዘባለን በኑሮውና በአገልግሎቱ እግዚአብሔርን ለማስከበር የሚፈልግ ማንኛውም አገልጋይ እነዚህን ወጥመዶች ለይቶ በማወቅ ራሱን ከእነዚህ መሰናክሎች መጠበቅ አለበት ።

ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሁሉ ሽሽ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናናትንም የዋህነትንም ተከታተል (፩ኛ ጢሞ፣ ፮ ፣ ፲፩) በማለት ይመክረዋል ።

እንዲህ ከሆነ በተቻለ አቅም የተሰጠውን አገልግሎት ጠብቆ መልካሙን ሩጫውን በመጨረስ የጽድቅን አክሊል ከጌታው ለመቀበል የሚፈልግ አገልጋይ ከዚህ በፊት ለብዙዎች መውደቂያ ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ራሱን መጠበቅ ይገባዋል ። ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን ለማየት እንሞክር

፩ ከገንዘብ ፍቅር መራቅ ፣

፪ የሌላውን አለመመኘት ፣

፫ ለውዳሴ ከንቱ አለመገዛት ፣

ስለዚህ እነዚህን ከአልፋትን እግዚአብሔር አምላክ ለወዳጆቹ ያዘጋጀውን የጽድቅ አክሊል ለመቀበል እንደሚያበቃን እምነን ታማኝ አገልጋይ እንሁን

ዲ በላይ ጸጋየ

# የሴቶች ዓምድ

## አዋልደ ኢየሩሳሌም

አዘጋጅ ወ/ት መዓዛ አስማማው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የማስተማር ሥራውን የጀመረው በታላቂቱ ከተማ በኢየሩሳሌም ነበር ። ከትምህርቱ ጋርም የተአምራት የፈውስ የበረከትና ሌሎችንም መንፈሳዊና አስደናቂ መልካም ተግባራትን ያከናወነው ከዚያችው አገር ነበር ። ለአገልግሎት የመረጣቸው ደቀመዛሙርት የትምህርቱ ተከታታይ የነበሩት ቅዱሳት እንስት ስለ ሚፈጸመው በጎና ቅን ሥራ ሁሉ የመጀመሪያ ተመልካቾች ነበሩ ።

በኋላም የመጣበትን ዓለምን የማዳን የመጨረሻ የመከራ ጽዋ ለመቅመስ ሲዘጋጅ እስከሞት ድረስም ቢሆን እከተልሃለሁ እስከ ማለት የደረሱ አልታጡም ። ቢሆንም ቃል ተግባር ሆኖ አልተገኘም ። የመከራው ጉዞ የቀራንዮው ዳገት የእምነት ጽናትና ጥንካሬ የተፈተነበት እንደነበር አይዘነጋምና ።

ትምህርቱን ተአምራቱን የጠሉት አይሁድ እያንገላቱ መስቀል አሸከመው ሊሰቅሉት ሲወስ





www.ethiopianorthodox.org

ዱት የርም ጭፍሮች ሕዝቡ እንዳይከተለውና የመ ከራው ተካፋይ እንዳይሆን ሲያባርሩ ቅዱሳት አን ስት ግን ወደ ኋላ አላሉም ። የትምህርቱ ተካፋይ የነበሩት ደቀ መዛሙርት እንኳ ፈርተው ሲበታ ተኑ ሁሉም ራሱን ለማዳን ሲሯሯጥ ሴቶች ግን የተደረገላቸውን ጸጋና ምሕረት እያስታወሱ የክር ስቶስ ፍቅር አስገድዶአቸው በዚያ አስፈሪ የመከራ ጊዜ እስከ መጨረሻው ድረስ ለመከተል የነበራቸ ውን ቁርጥ የመንፈስ ጥንካሬና ታማኝነታቸውን ከፍጻሜ ለማድረስ እስከ መስቀል ሞት ተከሉት።

ጠላቶቹ አይሁድ በርባን ይፈታ ክርስቶስ ይሰ ቀል እያሉ ሲጯጯሁ "መድኃኒታችውን የጠሉት አይሁድ የሰላምን አምላክ ሰቀሉት" እያሉ በመዘ መር በዚያ መከራ ሰዓት መታሰርንም ሞትን ይፈሩ እስከ ቀራንዮ ድረስ አብረው ተጓዙ ። የጭፍሮችን ስልፍና ቁጣ ከምንም ባለመቁጠር እንባቸውን እያ ፈሰሱ ደረታቸውን እየደቁ ሙሾ እያወረዱ ዋይ ዋይ በማለትና ከኋላው በመከተል የመከራው ተሳ ታፊ ሆነዋል ።

በዚያም ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች ስለ እኔ አታልቅሱ ዳሩ ግን መካኖችና ያልወለዱ ማኅ ጸኖች ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓን ናቸው ። የሚባ ልበት እነሆ ይመጣልና ለራሳችሁ ለልጆቻችሁ አልቅሱ ሲል ወደፊት ታላቅ መከራ እንደሚመጣ ገለጠላቸው ። (ሉቃ ፳፫ ፣ ፳፯-፴) ።

በይበልጥ ቅዱሳት አንስት ክርስቶስ ከተሰቀ ለበት ቀን ጀምሮ እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ በእ ግረ መስቀሉ ቆመው እንባቸውን ከማፍሰስ አል ተገቱም ። በትንሣኤውም ጊዜ ሌሊት ሳይነጋ በአ ይሁድ ልማድ መሠረት ሽቱ አዘጋጅተው ወደ መቃብሩ ሲሄዱ ደንጋዩን ማን ያንከባልልናል እያሉ ሲጨነቁ ክርስቶስ መነሳቱን መላእክት አበሠሩ አቸው ትንሣኤውንም ለደቀመዛሙርቱ እንዲገልጹ ነገሯቸው ።

ከእነርሱም መካከል ግንባር ቀደም በመሆን ክርስቶስን እስከ መጨረሻው ድረስ በመከተል የመ ጀመሪያው የትንሣኤ አብሳሪ ለመሆን የበቃች ማር ያም መግደላዊት ናት ። ይህች ሴት ክርስቶስ ያደረ ገላትን ምሕረት በማስታወስ በመከራውም ጊዜ ማንንም ሳትፈራ በጭፍች መቃብር ጥብቃ ሳት ገታ ከደቀ መዛሙርቱ ቀድማ የክርስቶስን ሥጋ ሽቱ ለመቀባት ሳይነጋ ወደ መቃብሩ ስትሄድ ክርስቶስን ከሞት ተነሥቶ ሳታገኘው በመቅረቷ ታለቅስ ጀመር ከሙታን ይነሳ ዘንድ አለው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል አላወቀችም ነበርና ነው ። በመቃብሩ ራስጌና ግርጌ የተቀመጡት ሁለት መላእክትም አንቺ ሴት ስለምን ታለቅሻለሽ አሏት ? ርስዋም ጌታዬን ወስደውታል ወሩትም እንዳኖሩት አላውቅም እያ ለች ከነሱ ጋር ስትነጋገር ዘወርስትልም ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን ክርስቶስን አየችው ፣ እርሱም ክርስቶስ መሆኑን ገለጸላት ከሞት መነሳቱን ሄደሽ ለወንድሞቼ ንገሪአቸው አላት ማርያም መግደላ ዊት ጌታን እንዳየችውና ትንሣኤውንም ንገሪአ ቸው እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ አበሰረቻቸው ።

በዚህም ሁኔታ ሴቶች የመከራውና የደስታው ተሳታፊ በመሆናቸው ፍቅሩም ስለአደረባቸው ከማ ንኛውም ሰው ይልቅ በመጀመሪያ ጊዜ ከሞት መነ ሣቱን እየተዘዋወሩ ላላወቁ እንዲያሳውቁ እድል አግኝተዋል ።

እንግዲህ በአሁኑ ዘመንም የሚገኙ ሴቶች የክርስቶስን ፍቅር መከራና ሞት ትንሣኤውን ጭምር ለማያውቁ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል ። ከላይ የጠቀስናቸው ሴቶች ቅዱስ ሥጋውን ሽቱ ለመቀ ባት ሲኼዱ የመቃብሩ ድንጋይ ከባድ ስለሆነ ማን ያንሳልናል እያሉ በየመንገዱ ይጨነቁ ነበር እንዳ ሉት ሳይሆን ደንጋዩን ግን ተነሥቶ ነው ያገኙት አሁንም ቢሆን አንዳንድ ሴቶች የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ቅዳሴውን መስማት የጸሎትና የቅዳ ሴው ተካፋይ መሆን ቢገባቸው በቤተ ክርስቲያን አጠገበ የመቃብር ደንጊያ ያለ እየመሰላቸው ማን ያነሳልናል እያሉ ይጨነቃሉ ከዚህም ጭንቀት የተ ነሣ እምነታቸውንና ምግባራቸውን በኀላላት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣት ይልቅ ወደ አስማተኞ ችና ወደ ባለ ውቃቢዎች ዘንድ መሄድ ደስ ይላቸ ዋል።ማንሳት የማይቻለው ከባድ ደንጊያ ግን እንደ ደንጊያየከበደውን ኃጢአታቸው በደላቸውን እንዲነ ሳላቸውወደ ቤቤተ ክርስቲያን መምጣት አለባቸው ።

# ዕረፍቱ ለጊዮርጊስ ሰማእት

ዕረፍት ሲባል ብዙ ሥራ ሠርቶና ብዙ መን ገድ ተጉዞ ሰውነትን ድካም ሲሰማው ለማንም የሚ ደረግ ጊዜያዊ ዕረፍት ነው ። እንዲሁም በዓላትን ለማክበር የሚደረግ ዕረፍት አለ ሞትም ዕረፍት ይባላል ሞት ለክፉዎች ብቻ ሲሆን ፣ ለደገኞች ዕረፍት ነው ።

ምክንያቱም ቅዱሳን ስለጽድቅ ሲሉ በዚህ ዓለም ከሚደርስባቸው ሥቃይና መከራ ተላቅቀው ዘለዓለማዊ ሕይወት አግኝተው በደስታ ስለሚኖሩ ሞታቸው እረፍት ስለሆነ ነው ።

በዘመነ ሰማዕታት ወንጌልን ሲያስተምሩ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ በመገኘታቸውም እንደነዲዮቅ ልጥያኖስና እንደነ መክሰምያኖስ ባሉ አላውያን ነገ ሥታት አንገታቸውን ለሰለት ፣ ሥጋቸውን ለእ ሳት እየሰጡ በሰማዕትነት ያረፉ ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው ከነዚህም አንደኛው ብዙውን መከራ የተቀ



ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ

በለው ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዘሮንቶስ (አንስጣስ ዮስ) እንደሆነና እናቱም ቴዎብስታ ትባል እንደ ነበረ ገድሉ ይናገራል የተወለደውም በ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀጳዶቅያ በምትባለው ቦታ ነው ይህችም ቦታ የምትገኘው ፋርስ በሚባልው (አሁን የመካ ከለኛው ምሥራቅ) ሲሆን የእናቱ አገር ዶግሞ በፍልስጥኤም ውስጥ የምትገኝ አገር ናት ። በእነ ዚህም አገሮች እየተዘዋወረ የወንጌልን ብርሃን (ት ምህርት) በማዳረሱ ሐየ ልዳ ኮከበ ፋርስ" የልደ ዐሐይ የፋርስ ኮከብ በማለት ቅዱስ ያሬድ ዘምሮ ለታል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሃያ ዓመት ሲሞላው አባቱ ስለሞተ ዱዲያኖስ ወደሚባለው ንጉሥ ሄዶ የአ ባቱን ሹመት ጠየቀ በዚያም ዘመን አምልኮተ ጣኦት የተስፋፋበት ክርስቲያኖች በከሃድያን እጅ የሚሠቃዩበት ወቅት ነበር ንጉሡም የሚያ መልከው በጣኦት ስለነበረ ቅዱስ ጊዮርጊስ አምልኮተ ጣኦትን እየተቃወመ ፣ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ አንድ አምላክ እንደሆነና ያለ እርሱም ሌላ አምላክ እንደሌለ ስግደትም አምልኮትም የሚ ገባው ለእርሱ ብቻ መሆኑን እያስተማረ ብዙዎችን ወደ ክርስትና እምነት ስለመለሰ ንጉሡ ተቆጥቶ ለእርሱ ጣኦት እንዲሰግድ ፈጣሪውን እንዲክድ አዘዘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ትእዛዙን ሳይቀበል ስለክርስቶስ ወንጌል ማስተማሩን ቀጠለ ።

ንጉሡም በዘዴ ለማስካድ ሹመት እሰጥኃ ለሁ ልጄንም እድርልሃለሁ በማለት ወደ ቤተ መን ግሥት እንዲገባ አደረገው ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ይህ ቀና ሆኖለት በቤተ መንግሥቱ ያሉትን የን ጉሡን ቤተሰብና ሠራዊቱን አስተምሮና አሳምኖ አጥምቋል ይልቁንም የንጉሡን ሚስት ወንጌልን አስተምሮና አጥምቆ እስከ መጨረሻው ድረስ በእ ምነቷ ፀንታ ሕይወቷን በሰማዕትነት አሳልፋ ለማ ያልፈው መንግሥት እንድትበቃ አድርጓታል ።

ከዚያም ቤሩት ወደምትባል አገር ሄዶ በሚ ያስተምርበት ጊዜ የዚያችአገር ሕዝብ ዶራጎን የሚ ባለውን ዘንዶ (አውሬ) እያመለከ አንዳንድ ልጃገ ረድ በተራ እየገበረ ሲኖር ቤሩታዊት የምትባል ልጃገረድ ተራዋ ደርሶ ለዘንዶው ልትሠዋ እንደቀ ረበች ፈጣኑ ሰማዕት በነጭ ፈረስ ደርሶ ዘንዶውን በጦር ወግቶ በመግደል ልጅቷን እንዳዳናትና አገ ሩንም ለዘንዶ ከመገበር እንዳዳናቸው ገድሉ በሰ ፊው ያብራራል ። ስለዚህ ይህ ታዳጊ ሰማዕት ለሚ ወዳቸው ሁሉ በችግራቸውና መከራ በደረሰባቸው ጊዜ ፈጥኖ የሚደርስላቸው በመሆኑ "ፍጡነ ረድ ኤት" ተብሏል ።

ንጉሡ ዱዲያኖስ የቅዱስ ጊዮርጊስን ትምህ ርትና የተከታዩን ብዛት ሲያይ እጅግ በመቆጣት ፸ የፋርስ ነገሥታትንሰብስቦ በቅ ጊዮርጊስ ላይ ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚወሰድበት ጠየቃቸው እነዚህም ነገሥታት ጠርተው ለጣዖታቸው እንዲ ሰግድና አምላኩን እንዲክድ ጠየቁት እሱም ሳይ ፈራና ሳያፍር "ዕውነተኛው አምላክ ፈጣሬ ሰማ ያት ወምድር ነው የእናንተ ጣዖታት የማይሰሙ የማ ይለሙ የሰው የእጅ ሥራ የኢጋንንት ማደሪያ ናቸው በማለት የጣዖታትን ከንቱነት በመዘርዘር በሰፊው አስረዳቸው ።

እነሱም በመገረም "እስቲ ዕውነተኛ ከሆ ንክ ምልክት አሳየን" አሉት እሱም ወደ ፈጣ ሪው በመጸለይ ሰባው ነገሥታት የተቀመጡባቸ ውን ወንበሮች አለምልሞ አሳይቷቸዋል ይህንንም ባዩ ጊዜ ኦልቁንም በተአምራቱ ሕዝቡን በሙሉ ወደ ክርስትና እምነት የሚመልስ ጣዖቶቻቸውንም የሚያረክስ ክብራቸውን የሚቀንስ ፣ ሆኖ ስላዩት በመጋዝ ተሰንጥቆ በወፍጮ ተፈጭቶ በእሳት ተቃጥሎ በነፋስ እንዲበተን አድርገው ፈርደው በታል ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ረቂቅ ኃይል ከእርሱ ስላልተለየ እንደገና በመነሣት በብዙ ሀገር እየተ ተዘዋወረ ወንጌልን አስተምሯል ። ያልተጠመቁ ትንም አጥምቋል ። በዚህምክንያት በአላውያን ብዙ ጊዜ ስቃይ ቢጠናበትም አስቀድሞ ነቢዩ "ስለአንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታ ረዱ በጎችም ተቆጠርን" መዝ ፵፫-፳፪ ያለውን መሠረት በማድረግ ሰባት ዓመት ሙሉ ተጋድሎ ውን በመቀጠል አማኞችንና ተከታዮቹን በማብ ዛቱና የወንጌልን ትምህርት በማስፋፋቱ ያልተፈ ጸመበት መከራና ስቃይ የለም ። መርዝ አጠጡት ፣ በሰንሰለት አሥረው በመሬት ላይ ጐተቱት ፣ እንደ እህል አውድማ ላይ በኩብት አበራዩት ፣ እንደ እንጨት በመጋዝ ሰነጠቁት ፣ በመንኮራኩር (በሞ ተር) ፈጩት ፣ በእሳት አቃጠሉት ይህ ሁሉ ሲሆን ፍርሃት አላደረበትም ፣ ስለ ክርስቶስ ከመመስከር ወደኋላ አላለም ። "ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም





www.ethiopianorthodox.org

በመንገላታትም በስደትም ፣ በጭንቀትም ደስ ይለኛል ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና'' በማለት ቅዱስ ጳውሎስ በ፪ኛ ቆር መልእክቱ ምዕ ፲፩-፩ እንደጻፈው ኃያሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዚህ ሁሉ ሥቃይ በረታ እንጂ አልደከመም ።

በመጨረሻም ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ በስምህ መታሰቢያህን ያደረገ ፣ ቤተ ክርስቲያንህን ያሳነፀ በስምህ መልካም የሠራውን ሁሉ ኃጢአቱን እደመስስለታለሁ ቢታመም እፈውሰዋለሁ በሚደርስበትም ችግር ሁሉ እረዳዋለሁ የሚል ቃል ኪዳን ከፈጣሪው ተቀብሎ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ልዳ በምትባለዋ ሀገር አንገቱን ተሰይፎ አርፏል ። በዚህም ጊዜ ከአንገቱ ደም ፣ ውሃ ፣ ወተት ፈስሶዋል፣ እንደዚሁም የሰባት ዓመቱን ተጋድሎ የሚያሳስቡ ሰባት አክሊላት ከሰማይ ወርደውለታል ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኑ በታነፀበት (ጽላቱ ታቦቱ) ባለበት ቦታ ሁሉ በዚህ ዕለት በታላቅ ድምቀት በየዓመቱ ሲከበር ይኖራል ። የእርሱ ተከታይ የሆኑ አበው ቅዱሳንም የእርሱን ፍለጋ በመከተል ቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ ሃይማኖት እንዲጠነከር ምእመናን እንዲበዙ አርአያ ሆነው አልፈዋል ።

እኛም ክርስቲያኖች የሆን ሁሉ ዕውነተኛ የእግዚአብሔር ወዳጆች ፣ የሰማዕቱ ተከታዮች መሆናችን የሚታወቀው በየጊዜው የሚደርሱብንን ልዩ ልዩ ፈተናዎች በትእግሥት ተቀብለን ስናሳልፋቸውና ለትውልድ አርአያ የሚሆን መልካም ሥራን ማትረፍ ስንችል ነው ።

መ/ መንክር ዋሴ

# ከረጅም ፎቅ ላይ የወደቀው በመድኃኔ ዓለም ቸርነት ከሞት ዳነ

ይህ አስደናቂ የሆነ የጌታችን የመድኃኒታችን የመድኃኔ ዓለም ቸርነት የተፈጸመው በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ቅጽረ ግቢ ነው ይህ ገዳም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአሉት ታላላቅ ገዳማት አንዱ ሲሆን በዚህ ገዳም ስፍር ቁጥር የሌላቸው የልማት ሥራዎች ይከናወኑበታል ፣

በዚህ ገዳም ታላላቅ አበው መነኮሳት ያሉ ሲሆን እነዚህ አበው መነኮሳት የእርስ በርስ ፍቅርን መሠረት በማድረግ በሥም በጸሎት ተወስነው ተፋፋት እየሠሩ በመኖር ያገኙትንም በአንድነት ይመገባሉ ይህ ገዳም ከሌሎች አያሌ ገዳማት ልዩ የሚሆንበት ማታ ማታ በየዕለቱ መሠረታዊ የሆነ የወንጌል ትምህርት ለምዕመናን ያለማቋረጥ የሚሰጥበት መሆኑ ነው።በዚሁ ገዳም አስተዳዳሪ በመምህር ተስፋ ሥላሴ ጥገስ ሥራ መሪነት ከሚከናወኑት ዕፁብ ድንቅ የሆኑ ሥራዎች አንዱ አሁን በመሠራት ላይ ያለው ብዙ ፎቆች ያሉት ሕንፃ ነው ይህ ሕንፃ ሥራው ሲጠናቀቅ በገዳሙ ሥር ለሚገኘው ት ቤት ተጨማሪ አገልግሎት የሚሰጥ ነው ።



ከረጅም ፎቅ ወድቆ ጉዳት ላይደርስበት የተገኘው አምሳሉ ደምሴ

በዚህ ሕንፃ ሥራ በቀን ሠራተኛነት ተቀጥሮ የሚሠራ አንድ አምሳሉ ደምሴ የሚባል ወጣት የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ከቀኑ በ፰ ፣ ፴ ፣ በስምንት ሰዓት ተኩል ላይ እጅግ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ከአራተኛ ፎቅ ላይ ተወርውሮ ወድቆ በመድኃኔ ዓለም ቸርነት ምንም ዐይነት ጉዳት ሳይደርስበት መቅረቱን የገዳሙ አስተዳዳሪ ገልጸዋል ።

መምህር ተስፋ ሥላሴ ጥገስ የምስካየ ኅዙናን ገዳም ዋና አስተዳዳሪ በጽ/ቤታቸው ዘወትር የምናመልከው አምልኮትና ስግደት የባሕርዩ የሆነ ሕያው አምላካችን መድኃኔ ዓለም ለክፉ ሞት የተጋለጠ ምስኪን ሠራተኛ ሕይወቱ በአጭር እንዲቀጭ አልፈቀደም ።

ሠራተኛው አደጋ እንደ ደረሰበት ወደ ሐኪም ቤት ተወስዶ ራጅ ከተነሣ በኋላ ሲመረመር ምንም ዓይነት ስብራትም ሆነ ውልቃት እንዳልተገኘበት የሕክምና ባለሙያዎች አረጋግጠዋል ሲሉ የገዳሙ አስተዳዳሪ ተናግረዋል ።

የሕይወት ምንጭ የሆነው ሕያው አምላካችን መድኃኔ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ የኃጢአት መርገም የነበረበትን መላውን የሰው ዘር ከዘለዓለማዊ ሞት ያዳነ እርሱ ነው ።

ስለዚህ እርሱን አምነው በሕጉ የሚመሩትን ሥርዓቱን የሚጠብቁትን ትእዛዙን የሚአከብሩትን ሁሉ ምን ጊዜም ከድንገተኛ አደጋ ይሠውራቸዋል ፣ ከሞት ወደ ሕይወት ይመራቸዋል ።

በኃላም በዘመናት መለዋወጥ የማታልፈውን ሕማምና ሞት የሌለባትን ዘለዓማዊ ክብርና ደስታ የመላበትን ሰማያዊ ዓለም መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳቸዋል ።

ኤፍሬም በየነ



# ወንጌላዊው ማርቆስ ፤

ቅዱስ ማርቆስ የመጀመሪያ ስሙ ዮሐንስ ነበር ፤ እየዞረ በማስተማሩ ፣ በሐብል ታሥሮ መሬት ለመሬት እየተጐተተ ሥጋው ተቆራርጦ በመሞቱ ሰማዕት ፣ ከአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ በመሆኑ በእስክንድርያ ለተሾሙ ሊቀ ጳጳሳት የሚል ሥያሜ ተሰጥቶታል ።

የአባቱ ስም አርስጦሶሎስ ሲሆን እናቱ ማርያም ትባላለች ፣ ኢየሩሳሌም ውስጥ ክርስቲያኖች ለጸሎት የሚሰበሰቡት በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ነበር ለዚህ ወንጌላዊ በርናባስ አጎቱ ነበር ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር አብሮ አስተምሯል በተለይ ግን የጴጥሮስ ተከታይና ተማሪ ስለነበር ልጄ ይለዋል ፩ኛ ጴጥ ፭ ፣ ፲፬ በስሙ የሚጠራውን ወንጌል የጻፈውም እርሱ ነው ።

እናቱ ማርያም ባለጸጋ ስለነበረች ለልጅዋ ለማርቆስ የዮናናውያን ፣ የአፍርጅና የእብራይስጥ ቋንቋ እንዲማር አድርጋዋለች ወንጌላዊው ማርቆስ እየተዘዋወረ ወንጌልን ሲያስተምር በተአምራት የዕውራንን ዓይን አብርቷል ለምፃሞችን ከለምፃቸው አንጽቷል ሕሙማንን ፈውሷል አንካሶች ቀንተው እንዲራመዱ ዲዳዎች እንዲናገሩ ደንቆሮዎች እንዲሰሙ አድርጓል ።

እንዲያስተምር በዕፃ የደረሰችው ግብፃ ነበረች ቅዱስ ማርቆስ ወደ እስክንድርያ ከተማ ለመግባት ከከተማው በር ሲደርስ የጫማው ማዘቢያ (ማሠሪያ) ተበጠሰበተ አጠገቡ ጫማ ሰፊ ስለተመለከተ ወደዚያ ቀረብ ብሎ ለማስፋት እንደቆመ ጫማ ሰፊው ጫማውን በሚሰፋበት መሳፍቻ የገዛ ጣቱን ቢወጋው ኤስታኮ ! አለ በየናኒ ቋንቋ አሐዱ አምላክ አንድ አምላክ አንድ እግዚአብሔር ማለት ነው ፣ ሐዋርያው ማርቆስ ፈገግ አለና ለመሆኑ የጠራኸውን እግዚአብሔርን ታውቀዋለህ ን ? ቢለው ስሙን ሲጠሩት እሰማለሁ እንጂ አላውቀውም ስለአለው ማርቆስ ይህንን ጫማ ሰፊ ያስተምረው ጀመር ስለ አዳምና ሔዋን ፣ ስለ ጽኤል ከግብፃውያን ባርነት ነፃ መውጣት ስለእምላክ ሰው መሆን ነቢያት ስለጌታ መወለድ ቀደም አድርገው ትንቢት እንደተናገሩ ካስተማረው በኋላ አፈሩን በምራቁ ለውሶ የጫማ ሰፊውን ቁስል ቢቀባው ወዲያውኑ ዳነ ።

የጫማ ሰፊውም ስም አናንያኖስ ይባላል ። ከቁስሉ በመዳኑና በትምህርቱ ደስ ስላለው ወደ ቤቱ እንሂድ ብሎ ለመነው ሐዋርያው ማርቆስም ከአናንያኖስ ጋር ሄዶ ሚስቱን ልጆቹን ቤተሰቡንና ጎረቤቶቹን ሰብስቦ ካስተማራቸው በኋላ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቃቸው ።

ከዚያ ራቅ ብለው የሚኖሩ ሰዎችም ወሬውን ሰምተው እየገሰገሱ ስለመጡ እያስተማረ በሥላሴ ስም አጥምቋቸዋል ። ቅዱስ ማርቆስ በእስክንድርያ ከተማ እያስተማረ ብዙ ጊዜ ከኖረ በኋላ አናንያኖስን ኤጲስ ቆጶስ ልጆቹን ቀሳውስትና ዲያቆናት አድርጎ ሾሞአቸዋል ። ከዚያም ወጣ ብሎ አምስት አውራጃዎችን ለሁለት ዓመታት እየተዘዋወረካስተማረ በኋላ የሚያስተምሩ መምህራንን ሹሞላቸው ወደ እስክንድርያ ተመልሷል ።

ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ የማስተማር ኃይል ከእግዚአብርሔር የተሰጠው ታላቅ ሐዋርያ በመሆኑ በትምህርቱ በምድረ ግብጽ ተቋቁመው የነበሩት የጣዖት ቤቶች እንዲዘጉ አድርጓል ። ስለዚህም ዘአንበሳ ማርቆስ እስመ ከመ አንበሳ ይጥኅር አድያመ ግብጽ ዘአድመጸ እንዘ ይሰብክ ወንጌለ ሲል አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገልጾታል ። ወደ አማርኛ ሲተረጎም ኃይሉና ብርታቱ እንደ አንበሳ የሚጠነክር ወንጌላዊው ማርቆስ ወንጌልን በማስተማር እንደ አንበሳ ይጮኽል በትምህርተወንጌል በምድረ ግብፅ ያሉትን የጣዖት ማምለኪያ ቤቶች እንዲዘጉ እስከሚያደርግ ድረስ ማለት ነው ።

የቅዱስ ማርቆስ ማስተማር ለተንኰለኞችና የእግዚአብሔርን ቃል ለማይቀበሉ ሰዎች ደስ አላላቸውም ወንጌልን እንዳያስተምር ለመከልከል በጥላቻ ተነሣሡበት ።

ስለዚህ ሐዋርያው ማርቆስ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ቤተ መቅደስ ገብቶ ሳለ ምእመናን በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ከበው ቆመው ሲጸልዩ ከሃድያን ተሰብስበው ገብተው በአንገቱ ገመድ አስገብተው እየጎተቱ ሲያስወጡት ደሙ በመሬት ላይ ፈስሶ ሥጋው ሁሉ ተቆራረጠ ፣ በዚሁ ሌሊት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሊት በራዕይ ተገልጾ አጽናናው በክብር ከሐዋርያት ጋርም እንደሚስተካከልና በስሙ ለተራበ የበላውን ለተጠማ ያጠጣውን ለታረዘ ያለበሰውን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚያስገባለት ቃል ኪዳን ገባለት ፣

በማግሥቱም የቅዱስ ማርቆስ ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ከሐድያን መሞቱን አይተው እሳት አንድደው ሥጋውን ወደዚያው ጣሉት ግን እሳቱ በድኑን አላቃጠለውም ዝናም ውርጭ ጨለማ መብረቅ ነጐድጓድ ስለሆነ ከሐድያን ደንግጠው በየፊናቸው ተበታተኑ ፣ ምእመናን መጥተው ሥጋውን አንሥተው በክብር አስቀመጡት ፤

ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የዚህን ታላቅ ሐዋርያ ቅዱስ ማርቆስ መታሰቢያ በዓል ሚያዝያ ፴ ቀን ጽላቱ በሚገኝባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲከበር አድርጋለች በተጠቀሰው ዕለት በእግዚአብሔር ስም አምኖ በቅዱስ ማርቆስ ስም የተራበ የሚያበላ የተጠማ የሚያጠጣ የታረዘ የሚያለብስ ሐዋርያው የሚያስጠውን ዋጋ ያገኛል ጻድቁን በጻድቁ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል ተብሎ ተጽፎአልና ።

ቀ ሲ ጎ ልሣኑ በዛብኅ



www.ethiopianorthodox.org

# በጠበል ፮ ጠጠር የወጣላቸው አባ አሥራተ ገብርኤል ተሰማ

አባ አሥራተ ገብርኤል ተሰማ የተወለዱት ጐንደር ከተማ አባ ጃሌ ተ/ሃይማኖት ልዩ ስሙ አንኮይ መስክ ሲሆን በሕመም ሲሰቃዩ መቆየታቸውንና እንዴት መዳን እንደቻሉ ከዚህ የሚከተለውን ቃል አስፍረዋል ።

«የሽንት ማውረጃ ቧንቧዬ ትክክለኛ ሥራውን ማስተላለፍ ትቶ ይህ ነው በማልለው ሁኔታ እጅግ በጣም ተሰቃየሁ ፣ ሰው በመሆኔም ስቃዩ ሲበዛብኝ በጎንደር ቸቸላ ሆስፒታል ተመርምሬ የኩላሊት ጠጠር እንዳለብኝ በሐኪም ተነገሮኝ ሐኪሙ ወደ ከፍተኛ ሐኪም ቤት እንድሸጋገርአደረገ በዚህም መሠረት በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተመረመርኩ ሐኪሙም ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልገኝ ነግሮኝ መተኛት አለብህ አለኝ ። በታኅሳስ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ወ.ሮ ለተ ብርሃን (ዓጸደ ማርያም) የተባሉ ሴት ዋልድባ የአባ ሣሙኤልን በዓል ለማክበር ከአዲስ አበባ ሲመጡ በሸንኮራ የመጥምቁ ቅ/ዮሐንስን ጠበል ይዘው ስለነበር በጭንቀት ላይ እንዳለሁ ስለሰሙ በትንሽ እቃ ሰጡኝ እኔም ወዲያውኑ ጠጣሁት ተጨንቄ ነበርና ሌሊቱን ሲያፈተስትለኝ አድሮ ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ገደማ ጠጠር ወጣ በመቀጠልም ደም በኃይል ፈሰሰኝ የደሙን መፍሰስ ሲያዩ ይተርፋል ያለ አንድም ሰው አልነበረም እግዚአብሔር ግን ከእኔ ጋር ስለነበረ ከሞት ተረፍኩ የተዘጋውን የሽንት ቧንቧ እንዲከፈት ፈቅዶአልና ። ይህንንም የእግዚአብሔር ፈቃድ እስከ መጨረሻው ስጠብቅ ቆየሁ ።

በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለሁለተኛ ጊዜ ሐኪሙ መረመረኝ አሁንም ጠጠር እንዳለብኝ አስረድቶ መተኛት እንዳለብኝ ነገረኝ እኔም በነገሩ ሳልስማማ በኀዘን ላይ እንዳለሁ ስለሸንኮራው ዮሐንስ ጠበል ታሪክ የታተመ መጽሐፍ አነበብኩ በጣም ደስ አለኝ ወደ ጠበሉ ቦታ ለመሔድ ወሰንኩ ።

የተዘጋው የሽንት መውረጃ ቧንቧ አንድ ጠጠር ብቻ በመውጣት የነበረብኝ ችግር አልተወገደም ነበርና ከዚህም ጋር ምላሴ ወይም አንደበቴ ርቱዕ ሆኖ መናገር ተስኖት ስለነበር በሁለቱም በኩል ችግር ነበረብኝ ስለሆነም በሸንኮራው ቅ ዮሐንስ ጠበል በየካቲት ወር ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ተገኘሁ ተአምረኛውን ጠበል ጠጣሁት በመደጋገም ፭ ጠጠር በጠበሉ ኃይል ወጣልኝ ሽንቴም ደም እየቀላቀለ ፈሰሰ በመቀጠልም እንደዘንጋዳ ጥቃቅን ነገር ወጣልኝ በዚህም ጊዜ ጠበልተኛውን ሁሉ አስደነቀው በተለይም አባ ተ/ዮሐንስ ተ/ጻድቅ ከማዘን ጋር ነገሩን ተመልከቱ በአጠቃላይ ሙሉ ጤንነትን አግኝቼ ያለምንም ችግር ንጹሕ ሽንት በማፍሰሴ ተደሰትኩ ።

ስለዚህ የተአምረኛውን ቅ.ዮሐንስን አማላጅነት ተራዳኢነቱንም ላላወቁና ላላመኑ ሁሉ በዚህ ተአምር እንዲያምኑ ይህን መልእክት አስተላልፋለሁ «ቃል ኪዳኔን ለጠበቁ የማይጠፋ የዘለዓለም ስም እ ሰ ጣ ቸ ዋ ለ ሁ ከ ተ ባ ሉ ት አ ን ዱ ቅዱስ ዮሐንስ ነውና እመኑበት ሞት የሚጠብቃችሁ ሕምምተኞች ሁሉ ወደ ጠበሉ ሒዱና ከሥጋዊ ሞት ዳኑ እኔን ከሞት እንዳዳነኝም ተረዱ ። ቅዱስ ዮሐንስ ከጌታ ኢየሱስ በተሰጠው ቃል ኪዳን በአማላጅነቱ ለአመኑ የዘመናችን ሕምምተኞች የሚያድን ፍቱን መድኃኒት ነውና

አባ አሥራተ ገብርኤል ተሰማ ፮ ጠጠር በጠበል ወጣልኝ በማለት ያቀረቡልንን የምስክርነት ቃል አንብበናል ፮ ጠጠር ወጣልኝ ሲሉ ጠጠሩ ከመውጣቱ በፊት የሕመሙ ሁኔታ እንዴት ነበር?

ሕመሙ ሽንቴን እንደተለመደው ለመሽናት ባለመቻሌ ብዙ ስቃይ ነበረብኝ ከዚህም ጋር በእግር ለመጓዝ አልችልም ነበር በዚህ ዓይነት ከ፮ ዓመታት በላይ ተሰቃየሁ ።

ወ.ሮ ለተብርሃን ጠበል አመጡልኝ ብለዋል እርስዎ በመጀመሪያ አድራሻዎ የት ነበር ? እኔ አድራሻዬ ዋልድባ ነበር በየዓመቱ ታኅሳስ ፲፪ ቀን ዋልድባ የአባ ሣሙኤል በዓል ይከበር ስለነበር በዚያ በዓል ላይ ተገኝተው ከያዙት ጠበል ሰጡኝ በዚያኑ ዕለት አንድ ጠጠር በማውጣትና ደሙን በኃይል በማፍሰስ ምልክት አሳየኝ ።

ከዋልድባ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት እንዴት ቻሉ ? መንቀሳቀስ አልችልም ነበር ብለዋልና እኔ መቼም ሞት እንደሚጠብቀኝ አምኜ ነበር የተቀመጥኩት ይሁን እንጂ በመኪና ወደ አዲስ አበባ መጣሁ ስቃዩን በዚህ አጋጣሚ ለመዘርዘር ያስቸግራል ሆኖም እየተሰቃየሁ ደረስኩ ሐኪሙም የኩላሊት ውስጥጠጠርያለብኝ መሆኔንገልጾ አሁኑኑ ቀዶ ጥገና መደረግ እንደሚገባኝ ነገረኝ እኔ ግን መቀደዱን ጠላሁት አምላኪዬ ይጠባበቀኝ ስለነበር ከሐኪም ቤት ወጥቼ ወደ ሸንኮራ ሔድኩ ይህንኑም ባቀረብኩት መግለጫ አብራርቼ ዋለሁ ባጭሩ ግን እግዚአብሔር ፈጥሮኝ ያልረሳኝ በመሆኑ በዮሐንስ ጠበል እንደገና ፭ ጠጠሮች ወጡልኝ ።

እንኳንም እግዚአብሔር ማረዎት ለመሆኑ ጠጠሮችን ለማስረጃነት በክብር ይዘዋቸዋል ? ጠጠሮቹን ይገቡአቸዋለሁ ፪ት ያህሉን ጠጠሮች ሸንኮራ ሳለሁ ለሐኪም እና ሳየውና እንመልስልሃለን በማለት ወስደው አልመለሱልኝም ሌሉ ቹ በእጄ ይገኛሉ ።

ከኩላሊት በጠበል ጠጠር ወጣልኝ ማለት ቀላል ምስክርነት አይደለም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ይህን በዓይን እንድናይ በጆሮም እንድንሰማ ላደረገን አምላክ ምስጋናችንን እናቀርብለታለን ። ይህ ጠጠር ከወጣ በኋላ ምርመራ አደረጉ?

ከበሽታው ሙሉ በሙሉ ነጻ ስለሆንሁ መመርመር አስፈላጊዬ አልሆነም ምክንያቱም ሽንቴን



አባ አሥራተ ገብርኤል ተሰማ

ያለምንም ችግር እሸናለሁ ሙሉ ቀን በእግሬ ብጓዝ የሚሰማኝ ነገር የለም ስለሆነም ምርመራ አላስፈለገኝም ።

በሌላ በኩል ባቀረቡት ምስክርነት አንደበቴ ርቱዕ አልነበረም ብለዋል ይህስ ለምን አስቸጋሪ ሆነ?

እኔ እንደሚሰማኝ ሽንቴን በትክክል እንዳልሸና ከተከለከልኩበት ጊዜ ጀምሮ ምላሴ መቦላተፍ ጀመረ አንደበቴም በቀጥታ ከመናገር ተገታ እኔ የማውቀው ይህንኑ ነው በሐኪም በኩል ግን ቀዶ ጥገና ያስፈልገሃል ከመባሉ በቀር የተነገረኝ ነገር የለም ።

በመጨረሻ የሚሰጡት አሳብ አለ?

እኔ የምስክርነት ቃሌን በቂ ነው ብዬ አቅርቤ አለሁ ያው እንዳለ ይቅረብልኝ አሁን በቃል ስጠየቅ የሰ ጠሁት ቃል ደግሞ በጣም ጠቃሚ አሳብ እንዳቀርብ በመሆኑ የጋዜጠኞች አሠራር ጠቃሚ መሆኑን እንድረዳ አብቅቶኛል ለሁሉም የሸንኮራው መጥምቁ ቅ ዮሐንስ ጠበል ከዚህም የበለጠ ተአምር እንደሚሠራ ፍጹም እምነቴ መሆኑን አሁንም አረጋግጣለሁ ።

አባ አሥራተ ገብርኤል ተሰማ በሰጡት የምስክርነት ቃልና በዚህም አጋጣሚ ላቀረብንልዎት ጥያቄ የሰጡት መልስ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ የሚያረጋግጥነው እኛም በቦታው ላይ ተገኝተን ፮ቱ ጠጠሮች እና በጣም ትንንሽ የሆኑ ጠጠሮች በጠበሉ መውጣታቸውን ተመልክተን ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለና መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስም በተሰጠው ቃል ኪዳን ሕሙማንን የማዳን ኃይሉ እጅግ በጣም እየተጠናከረ መምጣቱን አረጋግጠናል ።በመሆኑም ከዚህ የበለጠ ተአምር እየሠራ መሆኑንም ለአንባብያን ጨምረን እናረጋግጣለን ።

ሊቀ ካህናት በለጠ አበበ

# እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም

«እምይእዜሰ ኢኮንክሙ ነግደ ወፈላሴ አላ አንትሙ ሰብአሀገሪቶሙ ለቅዱሳን ወሰብአ ቤቱ ለእግዚአብሔር ፡ -

እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም ።» (ኤፌ ፪፡ ፲፱)

ይህን ቃል የጻፈልን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን የጻፈውም በኤፌሶን ለሚገኙ ክርስቲያኖች ነው ። ይህች ኤፌሶን በዚያን ጊዜ በእስያ ውስጥ በኤጂያን ባሕር አጠገብ የምትገኝ ወደብ ነበረች ። ወደ ፫፻፳ ሺህ ሰዎች የነበሩባት ታላቅ ከተማ ነበረች ። ፴ ሺህ ሕዝብ መያዝ የሚችል የጨዋታ ስፍራ (እስታዲየም) ነበረ ። አርጤምስ በምትባል ሴት ስም የተቀረጸ ጣዖት በሕዝቡ ትመለክ ስለነበር ታላቅ ቤተጣዖት ታንጾ ነበረ ። አምልኮቱም ፍጹም ከእግዚአብሔር የራቀ ነበር ከዚህ አኳያ የኤፌሶን ከተማ በጣም አረማዊ ወይም እግዚአብሔርን የማያውቅ ሕዝብ ነበረ ። ይሁን እንጂ የኤፌሶን ሰዎች በቅዱስ ጳውሎ ስ ትምህርት የወንጌል መልእክት ስለደረሳቸው ቤተ ክርስቲያን በኤፌሶን ልትመሠረት ችላለች ።

ቅዱስ ጳውሎ ስ የኤፌሶን ክርስቲያኖችን ሁዙ ጊዜ እየተመላለ ሰ አስተምሯቸዋል ። (የሐዋ ፳ ፣ ፲፯ ፣ ፴፩) ከዚህም ሌላ ጢሞቴዎስና ወንጌላዊው ዮሐንስ ክርስቶስን በሚገባ ስላስተዋወቁአቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት እንግዶችና መፃተኞች አልነበሩም (፩ ጢሞ ፩ ፣ ፫ ፣ ፬) ይሁን እንጂ በዮሐንስ ራእይ እንደተገለጸው ወደኋላ ጊዜ የቀደመ ፍቅራቸውን ትተው ነበር ። (ራእይ ፪ ፡ ፬) በዚህ ምክንያት ቅዱስ ጳውሎ ስ በሮም እሥር ቤት ሆኖ በዚህ ቃል «ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋራ ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም» በማለት ያነቃቃቸው ነበር ከሕፃንነትና ከእንግድነት ሕይወት በእውነትና በእምነት ወደ ክርስቶስ እንዲቀርቡ ፣ ወደ እግዚአብሔር ፍጹም የጸጋሙላትም እንዲደርሱ ጽፎላቸዋል ። (ኤፌ ፪ ፣ ፲፱ ፣ ፫ ፣ ፲፰ ፣ ፬ ፣ ፲፭)

ይህ መልእክት ዛሬም ቢሆን ከቤተ ክርስቲያን የራቁ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ከኃጢአት ዓለም የመጣሁ መጻተኛና እንግዳ ነኝ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ ። ይሁን እንጂ ከጻድቃን ሰማዕታት ከመላዕክትም ማኅበር ከእውነተኛ ክርስቲያኖች ፣ ጉባኤ በክርስቶስ ፍቅር ስለተቀላቀሉ የቅዱሳን ሀገር ሰዎች ናቸው እንጂ እንግዶችና መጻተኞች





www.ethiopianorthodox.org

እይደሉም ። በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆኑ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናቸው እንጂ

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ኤፌሶን ክርስቲያኖች የብዙ የወንጌል አስተማሪዎች ብዙ ተደክሞልን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራዎች አይተን ሳለ ዛሬም ገና ለክርስቲያናዊ ሕይወት እንግዶችና መጻተኞች የምንሆን ሰዎች እንኖራለን የእግዚአብሔርን ቃል ስንሰማ ጆሮአችንን ከመፍዘዝና አእምሮአችንንም ከመደንዘዝ በቀር በመንፈሳዊ ዕውቀት አናድግም ። በነገር ሁሉ ወደ ርሱ ራስ ወደ ወደሚሆነው ወደ ክርስቶስ ማደግ ሲገባን ዛሬም በአእምሮ ሕፃናትና ለ.ቃለ እግዚአብሔር እንግዳ የሆንን ጥቂቶች አይደለንም ። ይህ መልእክት ግን እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም ይለናል ። በቅዱሳን ሀገርና በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሆኖ የቀደመ ፍቅራቸውን ፣ ትተው ፣ እውነትና ፍቅርን አለመያዝ ፣ በክርስቲያናዊ ሕይወትና በእግዚአብሔር ቃል አለማደግ ፣ ከሥጋዊ ምኞት አለመራቅ ፣ እንግዳና መጻተኛ መሆን ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን «ወዳጆች ሆይ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደመሆናችሁ እለምናችኋለሁ ።» ይላል (፩ ጴጥሮ ፥ ፪ ፥ ፲፩)

ሰው ሲፈጠርም ሆነ በገነት ሲኖር በቅዱሳን ሀገር የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆኖ ይኖር ነበር እንጂ እንግዳና መጻተኛ አልነበረም ። በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ግን ከቅዱሳን ሀገርና ከእግዚአብሔር ቤት ተባርሮ በዚህ ዓለም በሀዘንና በሥቃይ ሲኖር እግዚአብሔር አሰበው ። ወደቀደመ ሀገሩና ወደቀደመ ቤቱ ሊመልሰው ስለወደደ አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከለት ። አምላክ ሰው ሆኖ በምድር ላይ ከተመላለሰ በኋላ የተዋሐደውን ትስብእት ከሙታን ለይቶ በሥልጣኑ በማስነሣት ወደ ሰማያት ዐረገ ። በእግዚአብሔር ቀኝም ተቀመጠ እርሱ ባለበት እኛንም ደግሞ እንደሚያኖረን ወይም እንደሚያስገባን ቃል ገብቶልናል ። (ዮሐ ፲፬ ፥ ፫) በብኪ - የነበሩ የቀደሙት የእምነት ሰዎች ይህችን ሰማያዊት ሀገር ይናፍቁ ነበር ። (ዕብ ፲፩ ፥ ፲፫-፲፮) በክርስቶስም ሥራ የእምነት ሰዎች ሁሉ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች እንዲሆኑ ተደረገ ።

የቅዱሳን ሀገር የተባለችው ምድራዊት ሳትሆን ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ናት - - «ወለነሰ ዘውስተ ሰማያት ሀገርነ ፣ እኛስ ሀገራችን በሰማያት ነው» በማለት ተገልጧል ። (ፊልጵ - ፫ ፥ ፳ ። ) በዚያች ሀገርም ጸሎትና ምስጋና እንጂ ሌላ ነገር የለም ። ስለዚህ በክርስቶስ አምነን ወደ ዚህች ሀገር የምንገባ ሁሉ ለጸሎትና ለምስጋና እንግዳ መሆን የለብንም ። በምድር ላይ ያለችው ሰማያዊቷ ሀገራችንም ቤተ-ክ-ናት ። ወደ ቤ-ክርስቲያን በእምነት የገባ ሁሉ ቅዳሴውንና ውዳሴውን ማንኛውንም አምልኮተ እግዚአብሔር መማተፍ አለበት ።

ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን የምናምነውንና የምንወደውን ደግሞም የምንታዘዘውን ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች አድርጐናል ። ይህንንም ሲገልጥ « ናሁ እምየወአኃውየ ፣ ዘይገብር ፈቃዶ ለአቡየ ዘበሰማያት ውእቱ እኁየ ወእኅትየ ወእምየኒ ውእቱ ፣ ማለት - - - እነሆ እናቴና ወንድሞቼ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና» ብሎናል ። (ማቴ ፲፪ ፥ ፵፱-፶)የጌታችን የኢግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉትን ሁሉ ወንድሜ እኅቴ ብሎ ሲጠራቸው አላፈረም ። (ዕብ ፪ ፥ ፲፫) ቤተሰብ የሚባሉትም ወንድም እኅት አባት እናት እንደመሆናቸው መጠን ፣ በጌታም ቃል ለእርሱ መሠረት ለእኛም ወንድም እኅት እናት ተብለን ከተጠራን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ነን ማለት ነው ። ይህም የሚሆነው የአባታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ የፈጸምን እንደሆነ ብቻ መሆኑን ጌታ አስተምሮናል ። በሌላ በኩል ደግሞ «ወእለሰ ተወክፍዎ ወሀቦሙ ሥልጣነ ወሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ ለእለ አምኑ በስሙ» ይላል ። ይህም ማለት «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ማለት ሲሆን ወልደ እግዚአብሔርን በእምነት የተቀበልነውና በኢየሱስ ስም የምናምን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ነን ልጆችም ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን (ዮሐ ፩ ፥ ፲፪ ። ገላ ፬ ፥ ፯) የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንም የአባታችን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ለመሆናችን የመጨረሻው ማስረጃ ነው ። ስለዚህ እንግዶችና መጻተኞች አይደለንም ።

የቅዱሳን ሀገር እና የእግዚአብሔር ቤት ዋና መታወቂያ ፍቅር ነው ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ። ስለዚህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የሆንን ሁሉ በፍቅርና በእምነት ጸንተን ለመኖር የእግዚአብሔር ቅዱስ ቅ/ፈቃድ ይሁን ።

ዲ-ግርማ በቀለ ከቅ/ጳውሎስ ከ መ/ት ቤት

## የጭንቅ አማላጅ

ርኋን ላመናት ሰው ለሆነ ወዳጅ
ሁሉን ላወያያት በመድረስ ከደጅ
ትዳብሰዋለች በሚያድነው እጅ
እምየ ማርያም የጭንቅ አማላጅ ፣

የፍቁረ እግዚእ ማርያም እናቱ
ለታመመ ሁሉ ፍቱን መድኃኒቱ
ላጣ ችግረኛም ሀብትና ንብረቱ
ምሥጋና ይድረስሽ ጭንቅ አማላጅቱ ፣

ሰይጣን በሰዎች ላይ ድር እንዳያደራ
ጥላቻ በዓለም ላይ እንዳያንሠራራ
የሰው ልጅ ከሰው ልጅ እንዳይፈራራ
የክርስቶስ እናት አማላጅን አደራ ፣

የማያምን ሁሉ በአማላጅነትሽ
በአንዱ አምላካችን በእናትነትሽ
በርህሩህ ልቦናሽ በብፅዕትነትሽ
ለምን አይማርም ከዕለት ተግባርሽ ፣

ምሕረቱ እንዳይቀር በእኛ ኃጢአት ብዛት
ሰው በመሆናችን በምንሠራው ስህተት
ለነፍሳችን ትተን ለሥጋ ማዳላት
አማልጅን አትርሺን ኪዳነ ምሕረት ፣

ምንም አይጐዳ አንቺን ያመነ ሰው
እህሉም አይርበው ውሃውም አይጠማው
ድካም አይሰማው ብርድም አይበርደው
በኪዳነ ቃልሽ ስለምጠብቂው ።

ማርያም እያልን ስንጠራው ስምሽን
የዓለም ጠበቃ እመ አምላካችን
አደራ አደራ ከልጅሽ አማልጅን ።
የመ.አ ሰሎሞን መኮንን ተወልደ



www.ethiopianorthodox.org